
# ኢፕድ አዲስ ዘመን

እሁድ 83 ዓመት ቁጥር 363 ጳጉሜን 3 ቀን 2016 ዓ.ም ዋጋ 10:00 ብዕራችን ለኢትዮጵያ ህዳሴ ይተጋል!

# የኢትዮጵያ ኢኮኖሚ ሉዓላዊነት ከየት ወዴት?

**አዲሱ ገረመው**

ዓለም አቀፉ የገንዘብ ተቋም በቅርብ ጊዜ ባወጣው ሪፖርት በአፍሪካ ግዙፍ ኢኮኖሚ ካላቸው ሀገራት መካከል ኢትዮጵያን በአምስተኛ ደረጃ ላይ ማስቀመጡ ይታወቃል፡፡ በተለያዩ ጊዜያት እየወጡ ያሉ መረጃዎች እንደሚያመላክቱትም የኢትዮጵያ ኢኮኖሚ ከጊዜ ወደ ጊዜ እያደገ መምጣቱን ነው፡፡ ይህ የኢኮኖሚ ሉዓላዊነት ጉዞ መነሻው፣ አሁናዊው ሁኔታና መጻዒ ዕድሉ ምን ይሆን?

የፐብሊክ ፖሊሲና ምጣኔ ሀብት ምሑሩ ቆስጠንጢኖስ በርኸተስፋ (ዶ/ር) እንዳብራሩት፤ የኢትዮጵያ ኢኮኖሚ በከፍተኛ ለውጥ ታጅቦ የመጣ ነው፡፡ በደርግ ዘመን ኢትዮጵያ በአሰቃቂ ረሀብ በዓለም አቀፍ ደረጃ ስሟ ሲጠቀስ ነበር፡፡ ስሟም በኦክስፎርድ መዝገበ ቃላት ውስጥ እንኳን ተመዝግቧል። ነገር ግን ይህ ምስል ከጊዜ ወደ ጊዜ እየተቀየረ ሲሆን፤ በተለይም በዲያስፖራው ያላሰለሰ ጥረት

የኢትዮጵያ ኢኮኖሚ... ወደ ገጽ 5 ዞሯል

# ወታደር ያቆየው ታሪክ-ሉዓላዊነት

**አዲሱ ገረመው**

መከላከያ ሠራዊቱ በተለያዩ ጊዜያት የተሰጡትን ተልዕኮዎች በብቃት በመፈጸም አንጸባራቂ ድል ሲያስመዘግብ እንደቆ ሰሞኑን የኢ.ፌ.ዴ.ሪ ሀገር መከላከያ ሠራዊት የምሥራቅ እዝ 74ኛ ዓመት የምስረታ በዓል በተከበረበት ወቅት መገለጹ ይታወቃል፡፡ የሀገርን ሉዓላዊነት ለማስጠበቅ የህይወት ዋጋ ጭምር እየከፈለ ያለው ይህ ሠራዊት ታሪኩ እንደምን ይገለጻል?

ኢትዮጵያ ለቀጣናዊ መረጋጋት ያላትን ቁርጠኝነት

ወታደር ያቆየው... ወደ ገጽ 5 ዞሯል







# “ቅድመ አያቶቻችን በከፈሉት መስዋዕትነት ያላስደፈሩትን የሀገር ነፃነት የእኛ ትውልድ ጠብቆ ለትውልድ ማስተላለፍ አለበት”

## - ኢንጂነር አይሻ መሀመድ የመከላከያ ሚኒስትር

**ሳሙኤል ወንደሰን**

<u>አዲስ አበባ</u>፡- ቅድመ አያቶቻችንና አያቶቻችን በከፈሉት መስዋዕትነት ያላስደፈሩትን የሀገር ነፃነት የእኛ ትውልድ ጠብቆ ለትውልድ ማስተላለፍ አለበት ሲሉ የመከላከያ ሚኒስትር ኢንጂነር አይሻ መሀመድ ገለጹ። የሉዓላዊነት ቀን “ህብር ለሁለንተናዊ ሉዓላዊነት” በሚል መሪ ቃል ዛሬ በተለያዩ ዝግጅቶች ይከበራል።

የመከላከያ ሚኒስትር ኢንጂነር አይሻ ዕለቱን በማስመልከት

“ቅድመ አያቶቻችን... ወደ ገጽ 5 ዞሯል
















ዜና



አምባሳደር ደግፌ ቡላ

## የመጀመሪያው የአማርኛ የሕግ መዝገበ ቃላት ተዘጋጀ

**ዘላለም ግዛው**

አዲስ አበባ፡- በፍርድ ቤቶችና ሌሎችም የፍትህ አካላት ሥራዎቻቸውን በሚያከናውኑበት ጊዜ በቃላት አተረጓጎም የሚያጋጥማቸውን ችግሮች ሊፈታ የሚችል የአማርኛ የሕግ መዝገበ ቃላት መዘጋጀቱን የፌዴራል ሕግና ፍትህ ኢንስቲትዩት ገለጸ፡፡ የኦሮሚኛ የሕግ መዝገበ ቃላት 25 በመቶ ተጠናቅቋል፡፡

የኢንስቲትዩት ዋና ዳይሬክተር አምባሳደር ደግፌ ቡላ፤ በፍትህ ሂደት በቃላት አተረጓጎም ችግሮች እንደነበሩ እና የፍርድን ሂደት የሚያዛቡ አጋጣሚዎች መስተዋላቸውን ጠቁመዋል፡፡

ፍርድ ቤቶች፣ በሌሎች የፍትህ አካላት እና ክልሎችም ሕጉን መሰረት አድርገው በሚሰሩበት ሂደት በቃላት አተረጓጎም ችግሮች መኖራቸውን በተደረገው ግምገማ ግንዛቤ መኖሩንም ተናግረዋል፡፡

ከሦስት ዓመታት በፊት ሥራው የተጀመረው የአማርኛው መዝገበ ቃላት ኢንስቲትዩቱ ከአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ ከጄስቲስ ፎር ኦል ፕሪዝን ፌሎሽፕ ጋር በጋራ የተከናወነ መሆኑን ተናግረዋል፡፡ በቅርቡ እንደሚመረቅም ተናግረዋል፡፡

አሁን የተዘጋጀው ‹‹ኢንሳይክሎፒዲክ ሎው›› ከብላክ ሎው፣ ከኦክስፎርድ መዝገበ ቃላት ጋር በተቻለ መጠን ተቀራራቢነት ያለው እና በአማርኛ፣ በኦሮሚኛና በሌሎቹም ቋንቋዎች እንዲዘጋጅ ከሦስት ዓመታት በፊት ሥራው የተጀመረ መሆኑን ገልጸዋል፡፡

የፍትህ አካላት ሥራዎቻቸውን በሚሰሩበት ጊዜ ለምሳሌ የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ፣ የፍትሐ ብሔር ሕግ፣ በከፍተኛ ትምህርት ተቋማትም የሕግ ትምህርት ቤቶች ያጋጥማቸው የነበሩ የአተረጓጎም ችግሮችን የሚፈታ መሆኑንም ነው የተናገሩት፡፡

የሕግ መዝገበ ቃላቶች ተዘጋጅተው ሊሆን ይችላል ያሉት አምባሳደር ደግፌ፤ አሁን በተዘጋጀው ልክ በኢትዮጵያ የተዘጋጀ የሕግ መዝገበ ቃላት የለም፤ የመጀመሪያው ነው ማለት ይቻላል ብለዋል፡፡

የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ቋንቋዎችና ባህል ጥናት ክፍል ለስራው ትኩረት በመስጠት በጋራ ስንሠራ ቆይተናል፣ ለዳኞች፣ ለዐቃቤ ሕጎች ፣ ለጠበቆች፣ ለሕግ ትምህርት ቤቶችና ለአጠቃላይ ለፍትህ ዘርፉ የሚጠቅም ነው ብለዋል፡፡

የኦሮሚኛ የሕግ መዝገበ ቃላት ዘግይቶ በመጀመሩ እስካሁን ባለው ሂደት ቃላት ተለይተው ትርጉም እየተሠራ ሲሆን፤ አፈጻጸሙም 25 በመቶ መድረሱን አመልክተው፤ በሁለት ዓመት ውስጥ ይጠናቀቃል ተብሎ እንደሚጠበቅም ተናግረዋል፡፡

ዳኞች፣ ዐቃቤ ሕጎችና ሌሎች የፍትህ አካላት ፍርድ የሚሰጡት የሚያሳልፉት በሰው ንብረት እና ሕይወት ላይ ነው፡፡ ነገር ግን በአንድ ቃል ልዩነት እና ግድፈት ምክንያት ያልሆነ ውሳኔ ወይንም ፍርድ ሊያስተላልፉ ይችላል፡፡

በመሆኑም በሁኔታው ላይ በሀገር አቀፍ ደረጃ ተግባራዊ የሚሆን አንድ የሕግ መዝገበ ቃላት መዘጋጀት እንደሚገባው በመስማማት ወደ ሥራ መገባቱን አውስተዋል፡፡

በዝግጅቱ የሕግ ምሁራን፣ በቋንቋ (ሊንጉዊስቲክ) የተሻለ ብቃት እና ችሎታ ያላቸው ሰዎች እንዲሳተፉ መደረጉንም አመልክተዋል፡፡

# ከ47 ነጥብ አምስት ሚሊዮን ብር በላይ ዋጋ ያላቸው መድኃኒቶች ተወገዱ

**ሳሙኤል ወንደሰን**

አዲስ አበባ፡- በ2016 በጀት ዓመት ከ47 ነጥብ አምስት ሚሊዮን ብር በላይ ዋጋ ያላቸው መድኃኒቶች እንዲወገዱ ማድረጉን የአዲስ አበባ ከተማ የምግብና መድኃኒት አስተዳደርና ቁጥጥር ባለስልጣን አስታወቀ።

የባለስልጣኑ ምክትል ዋና ሥራ አስኪያጅ አቶ አሰፋ ተሬሳ እንደተናገሩት፤ በበጀት ዓመቱ ክትትል እና ቁጥጥር ከተደረገባቸው የጤና ተቋማት ውስጥ 109 ተቋማት ጉድለት የተገኘባቸው ሲሆን 87 ተቋማት የጽሑፍ ማስጠንቀቂያ፣ 21 ተቋማት ጊዜያዊ እሽጋ እና የአንድ ተቋም ፍቃድ የመሰረዝ እርምጃ ተወስዶባቸዋል።

ክትትል እና ቁጥጥር ከተደረገባቸው የመድኃኒት ተቋማት ውስጥ 16 ተቋማት ላይ ችግር የተገኘባቸው ሲሆን 77 ተቋማት የጽሑፍ ማስጠንቀቂያ፣ 38 ተቋማት ላይ ጊዜያዊ እሽጋ እና አንድ ተቋም ፍቃድ የመሰረዝ እርምጃ የተወሰደ መሆኑን ጠቅሰው፤ 90 ሺ 584 ኪሎ ግራም የሚመዝንና ብር ከ47 ነጥብ አምስት ሚሊዮን ብር በላይ ዋጋ ያላቸው መድኃኒቶች ተወግዷል ብለዋል።



አቶ አሰፋ ተሬሳ

ክትትል እና ቁጥጥር ከተደረገባቸው የምግብ እና ጤና ነክ ተቋማት ውስጥ 941 ተቋማት ላይ ችግር እንደተገኘባቸው ገልጸው፤ 855 ተቋማት የጽሑፍ ማስጠንቀቂያ፣ 83 ተቋማት ላይ ጊዜያዊ እሽጋ እና የሶስት ተቋማት ፍቃድ የመሰረዝ እርምጃ መወሰዱን ተናግረዋል።

አጠቃላይ በዓመቱ የተወገዱ፣ ጊዜ ያለፈባቸውና የተበላሹ ምግቦች 132 ሺህ 250 ኪሎ ግራም በቁጥጥርና የኦፕሬሽን ሥራ በመሥራት 13 ሚሊዮን 345 ሺህ 270 ብር ዋጋ ያላቸውና ጊዜ ያለፈባቸውን ምርቶች እንዲወገዱ ተደርጓል ነው ያሉት አቶ አሰፋ ተሬሳ።

ብር 6 ሚሊዮን የሚገመት 109 ማዳበሪያ (6500 ኪሎ ግራም) የሚሆን ቅቤ የናሙና ምርመራ በማድረግ በውጤቱም መሠረት ከባዕድ ጋር የተቀላቀለ መሆኑ የተረጋገጠ ስለሆነና ለጤና አስጊ በመሆኑ እንዲወገድ ተደርጓል ያሉት አቶ አሰፋ፤ 59 ሺህ 936 ኪሎ ግራም የሚመዝን የጤና ነክ ምርቶች (የፅዳትና የንፅህና መጠበቂያ) ግምታዊ ዋጋቸው ከሶስት ሚሊዮን ብር በላይ የሆኑ ምርቶች የመጠቀሚያቸው ጊዜ በማለፉ እንዲወገድ መደረጉን ተናግረዋል።

103 ሺህ 500 ብር ዋጋ ያለው 345 ኪ.ግ የበሰበሰና ከባዕድ ነገር ጋር ተቀላቅሎ ሲፈጭ የተገኘ በርበሬ እንዲወገድ ተደርጎ ተቋሙም የእገዳ እርምጃ እንደተወሰደበት ተናግረዋል።

# ዐውደ ዓመትና ገበያ

**መስከረም ሰይፉ**

ዓውደ ዓመት ሲመጣ ሳቢ ከሆኑ ጉዳዮች መካከል አንዱ የበዓል ምግብ ዝግጅት ነው፡፡ በተለይም አዲስ ዓመት ሲጠባ ዶሮው፣ጠጁ ፣ጠላው፣ ድፎ ዳቦ አዘጋጅቶ ዘመድ አዝማድ ተሰባስቦ ማክበር ድባቡን ልዩ ያደርገዋል።



ለዶሮ፣ ለቅቤ፣ ለቅመማ ቅመምና ለተለያዩ ግብዓቶች የተለዩ የገበያ ስፍራዎች ማጀትን ሞልቶ የተለያዩ ምግቦች ለማዘጋጀትደግሞ የገበያ ሁኔታ ወሳኝ መሆኑ አያጠያይቅም፤ የበዓል ገበያው በተመለከተ ምን ይመስላል የሚለውን ለመታዘብ በአዲስ አበባ ሾላ ገበያ ቅኝት አድርገናል።

ወይዘሮ አቦነሽ ደምሴ ለአዲስ ዓመት ሰፋ ያለ የሸመታ ልምድ እንዳላቸው ለኢፕድ ገልጸው፤ የዘንድሮ የበዓል ገበያ ላይ የዋጋ ጭማሪ በመኖሩ ወሳኝ የሚሏቸውን ግብዓቶች ብቻ መሸመታቸውን ተናግረዋል፡፡

ሽንኩርት በኪሎ በ120 ብር ፣ ነጭ ሽንኩርት በኪሎ 350 ብር እንዲሁም ቡና በኪሎ በ480 ብር መግዛታቸውን አስረድተው፤ ገበያው አምና ከገዙበት ጋር ሲያነጻጽሩት ጭማሪ ቢያሳይም ከጥቂት ሳምንት በፊት አስቤዛ ሲገዙ ከነበረው ዋጋ ግን ብዙም ልዩነት እንደሌለው ያነሳሉ፡፡

በሾላ ገበያ የቅመማ ቅመም ነጋዴ የሆኑት ወይዘሮ ዙፋን ወሳኝ በበኩላቸው፤ የዘንድሮው የአዲስ ዓመት ገበያ የደራ ነው ባይባልም የተቀዛቀዘ እንዳልሆነ ይገልጻሉ፡፡

ኮረሪማ በኪሎ አንድ ሺ 100፣ ጥቁር አዝሙድ 350 ፣ነጭ አዝሙድ ደግሞ 400 ፣በርበሬ በ450 ፣ሚጥሚጣ 350 ብር እየሸጡ መሆኑን ጠቁመው፤ ዋጋው በዓል ከመድረሱ በፊት ቢጨምርም በዓልን ምክንያት አድርጎ የተለየ ጭማሪ እንዳላሳየ ተናግረዋል፡፡

ሌላኛው ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ሃሳቡን የሰጠው የዶሮ ነጋዴ ትንሳኤ ብርሀኑ በበኩሉ፤ ዶሮ መነገድ ከጀመረ አራት ዓመታት ማስቆጠሩንና የዘንድሮ አዲስ ዓመት ገበያ ካለፉት ዓመታት ጋር ሲነጻጸር የደራ አለመሆኑን ያስረዳል።

የፈረንጅ ሴት ዶሮ ከ500 ብር ጀምሮ እየሸጥኩ ነው። የሀበሻ ዶሮ ደግሞ እንደየ መጠኑ ከ800 እስከ 1300 ብር እየሸጥኩ እገኛለሁ፤ አብዛኛው ሰው አንድ ዶሮ እየገዛኝ ይሄዳል ይላል።

ሸማች ሲመጣ ዋጋው ተወደደ የሚለው ብዙ እንደሆነ የሚናገረው ትንሳኤ፤ ነገር ግን ገበያው ላይ የዶሮ አቅርቦት በቂ በመኖሩና ዋጋው በፊት ከነበረው ጭማሪ ያልታየበትና ተመጣጣኝ መሆኑን ይገልጻል፡፡

ሌላኛው በሾላ ገበያ ቅቤ፣ አይብ ፣ቡላና መሰል ምርቶችን የሚሸጡት ወይዘሮ አየለች ካሳ እንደሚሉት ለበዓል ለብዙ ደንበኞቻቸው ቅቤ እያቀረቡ ይገኛሉ፡፡



እንደ ወይዘሮ አየለች ገለጻ፤ የቅቤ ዋጋው እንደየአይነቱ ይለያያል። በሳል የሚባለው ቅቤ በ750 ብር ፣መካከለኛው 850 ብርና ለጋ ቅቤ ደግሞ በ900 ብር እየተሸጠ ነው። ከቅቤ ውጪ አንድ ኪሎ አይብ በ350 ብር እያቀረቡ መሆኑን ያስረዳሉ።

በአጠቃላይ የገበያ ሁኔታው ብዙ የሰዎች ጋጋታ የማይታይበት ቢሆንም ለነጋዴውም ሆነ ለሸማቹ ገበያተኛ አስፈላጊ የሚባሉ የበዓል ግብይቶችን ለመፈጸም አስፈላጊ መሆኑን ያስረዳሉ።

# ርዕሰ አንቀፅ

## ፈተናዎቻችን ትውልዱ ከአባቶቹ ከወረሰው ጀግንነት እና ለሀገር ክብር ካለው ቀናኢነት አይበልጡም!

ሉዓላዊነታቸውን በከፍተኛ ተጋድሎ ለዘመናት አስጠብቀው ከቆዩ ጥቂት የዓለም ሀገራት መካከል አንዷ ሀገራችን ኢትዮጵያ ነች። በየዘመኑ ሉዓላዊነቷን የሚፈታተኑ ተግዳሮቶች ቢያጋጥሟትም፤ ሕዝቦቿ ለነጻነታቸው እና ለብሄራዊ ክብራቸው ከነበራቸውና ካላቸው ቀናኢነት አኳያ ሉዓላዊነታቸውን አስጠብቀው መቆየት ችለዋል።

የሀገረ መንግሥት ግንባታ ታሪክ በኢትዮጵያ ረጅም ዘመናትን ማስቆጠሩ ፤ ሀገሪቱ በነዚህ ሁሉ ዘመናት ሉዓላዊነቷን አስከብራ መኖሯ፤ ለአንዳንዶች የመገረም እና የመደነቅ ፤ ለሌሎች ደግሞ የነጻነት ፤ የአልገዛም ባይነት እና የይቻላል መንፈስ መነቃቃት ምንጭ ሆኗል።

ይህ ከትውልድ ወደ ትውልድ እየተላለፈ የመጣ ሉዓላዊነትን አስጠብቆ የመሄድ ማህበረሰባዊ እሴት በየዘመኑ የሀገሪቱን ሉዓላዊነት ለመገዳደር የተነሱ ሃይሎች ከፍ ባለ ውርደት አንገታቸውን ደፍተው እንዲመለሱ፤ ከዚህ ባለፈ በዓለም የሃይል አሰላለፍ ላይ የነበረውን የተዛባ አመለካከት መግራት አስችሏል።

ሀገራችን ካለችበት ቀጣና ስትራቴጂክ ጠቀሜታ አኳያ በየዘመኑ የተነሱ ሃያላን መንግሥታት የትኩረት ማእከል ሆና ቆይታለች፤ በዚህም ሀገሪቱን በሃይል በማንበርከክ ለዓላማቸው ተገዥ ለማድረግ ረጅም ርቀቶችን ሄደዋል። በብዙ ዝግጅት የጦርነት ነጋሪት አስጎስመው ባህር ተሻግረው መጥተዋል።

በተሳሳተ ስሌት በተለያዩ የጦር ግንባሮች የሀገሪቱን ሕዝቦች ገጥመው፤ የሕዝቡን የነጻነት እና የአልገዛም ባይነት መንፈስ መቋቋም አቅቷቸው ፤ በመጡበት መንገድ በተሰበረ ልብ፣ በሽንፈት አንገታቸውን ደፍተው ለመመለስ ተገድደዋል። ይህም በብዙ የአሸናፊነት ገድል ለደመቀ የቀደመ ታሪካቸው ስብራት ሆኗል።

የቀደሙት አባቶቻችን ለሀገር ሉዓላዊነት የከፈሉት ውድ ዋጋ ከነሱ አልፎ፣ ዘመን ተሻግሮ የዚህ ትውልድ የብሄራዊ ክብር እና የማንነት ምንጭ ሆኗል። እንደ ሀገር በዓለም አቀፍ ደረጃ አንገታችንን ቀና አድርገን የምንሄድበትን የአኩሪ ታሪክ እና የከበረ የማህበረሰባዊ ማንነት ትርክት ባለቤት አድርጎናል።

የቅርቦቹ ትውልዶችም የቀደሙ አባቶችን የተጋድሎ ታሪክ ከመተረክ እና ትርክቱ በሚፈጥረው የማንነት ከፍታ ውስጥ ከመኖር ባለፈ፣ ሀገሪቱ የህልውና አደጋ ውስጥ በገባችባቸው ወቅቶች ሁሉ እንደ አባቶቻቸው በሀገር ህልውና እና ሉዓላዊነት ጉዳይ ጨርቄን ማቄን ሳይሉ ከፍ ባለ የሀገር ፍቅር እና የተጋድሎ ትርክት የራሳቸውን ታሪክ መሥራት ችለዋል።

ለዚህም ባለፉት ስድስት አስርት ዓመታት እንደሀገር በሉዓላዊነታችን እና በህልውናችን ላይ የተቃጡ ጥቃቶችን በብዙ መስዋእትነት እና ከፍ ባለ ጀግንነት በአሸናፊነት መወጣት ችለዋል። በዚህም የአባቶቻቸው ልጆች መሆናቸውን፤ የሀገሪቱ ማሕጸን ጀግኖች ማፍራቱን እንዳላቆመ ለጠላትም ለወዳጅም በተጨባጭ አስመስክረዋል።

የዛሬውም ትውልድም ቢሆን በብዙ ፈተናዎች ውስጥ ሆኖ፤ የትኛውም ፈተና ከሀገሩ ሉዓላዊነት በልጦ ሊፈትነው እንደማይችል ባለፉት ሶስት ዓመታት በተጨባጭ አሳይቷል። ስለ ሀገሩ ሆ ብሎ በአንድነት በመነሳት፤ ከፍ ባለ መስዋእትነት የሀገርን ህልውና ከስጋት መታደግ ችሏል።

የሀገሪቱን ሉዓላዊ ክብር ሙሉ ለማድረግ በሀገራዊ ትርክታችን ላይ መጥፎ ጥላ ያጠላውን ድህነት እና ኋላቀርነትን ታሪክ ማድረግ በሚያስችል አዲስ የታሪክ ምእራፍ ውስጥ ይገኛል። አዲሱ የታሪክ ምእራፍ በብዙ ፈተናዎች የሚናጥ ቢሆንም ትውልዱ ለብሄራዊ ክብሩ ካለው ቀናኢነት፤ ተግዳሮቶችን ተሻግሮ ሀገርን የተሟላ ክብር ባለቤት እንደሚያደርግ ይታመናል።

ትውልዱ የሀገርን ሉዓላዊነት የማስጠበቅ ኃላፊነቱን መወጣት ብቻ ሳይሆን፤ የሀገርን ክብር ሙሉ ለማድረግ በጀመርነው ሀገራዊ ንቅናቄ ላይ በውስጥም በውጪም እያጋጠሙን ያሉ ፈተናዎች የሚጠበቁ፤ በዘመናት እንደ ጥላ ሲከተሉን የኖሩ፤ ዛሬ ላይ ላለንበት ድህነት እና ኋላቀርነት በአንድም በሌላም ተጠቃሽ የሆኑ ምክንያቶች መሆናቸውን ይገነዘባል።

እነዚህ ፈተናዎች ትናንት ግልጽ በሆኑ የተለያዩ የጦርነት ግንባሮች ገጥመን በሽንፈት የመለስናቸው ጠላቶቻችን ሴራ አካል ናቸው። ፈተናዎቹ አሁን ያለው ትውልድ ከአባቶቹ ከወረሰው ጀግንነት እና ለሀገሩ ክብር ካለው ቀናኢነት፤ ከዛም ባለፈ ከድህነት ጋር አብሮ ላለመኖር ከፈጠረው ቁርጠኝነት አንጻር በየትኛውም መመዘኛ ከአቅሙ በላይ ሊሆኑ የሚችሉ አይደሉም።

እነዚህ ፈተናዎች አሁን ላይ የገዘፈ አቅም ተላብሰው በትውልዱ ፊት ቢቆሙም፤ ትውልዱ ዘመኑን እና በዘመን ውስጥ የተገነባ አሁናዊ ማንነቱን የሚመጥን የራሱን ታሪክ ሰርቶ እንዲያልፍ በታሪክ ሄደት ውስጥ የተፈጠሩ ክስተቶች ተደርገው የሚወሰዱ፤ ሊሠራው ላለው ታሪክም «እንደ መልካም አጋጣሚ» የሚታዩ ናቸው።

**አዲስ ዘመን**
ኢፕድ
ግንቦት 30 ቀን 1933 ዓ.ም ተቋቋመ

**የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ስራ አስፈጻሚ**
ስልክ ቁጥር - 011-126-42-22
ኢሜል ፡- epa@press.et

**ዋና አዘጋጅ**
አንተነህ ኃ/ብርሃን ወ/መድህን

**አድራሻ**
ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከ
ወረዳ 06
የቤት ቁጥር 319
ኢሜይል - anteneh.hailebirhan@press.et
ስልክ ቁጥር - 011-1-26-42-40

**የገበያ ልማትና ፕሮሞሽን ዘርፍ**
ኢሜይል - etpresspromotion@gmail.com
ስልክ - 011-126-43-41
ፋክስ - 011-811-13-15
የዝግጅት ክፍል ፋክስ - 251-011-1-56-98-62

**የአዲስ ዘመን ማኔጂንግ ኤዲተር**
ወንድወሰን ሽመልስ ታደሰ
ስልክ፡- 011 126 4200
Email:- wendweson.shimelis@press.et
wendwesonshimelis@gmail.com

**የዜና ማዕከል ዋና አዘጋጅ**
ወርቁ ማሩ
Email:- workumaru2@gmail.com

**የአዲስ ዘመን ምክትል ዋና አዘጋጆች**
- ኃይሉ ሣህለድንግል
- እስማኤል አረቦ
- ቦጋለ አበበ

**የማስታወቂያ መቀበያ ክፍል**
ስልክ ቁጥር - 011-156-98-73
ፋክስ - 011-126-58-12
ቴሌግራም - 097- 608-47-07 - Press

**የማስታወቂያ ሽያጭ ማስተባበሪያ**
ስልክ - 011-1-26-43-39

**ማከፋፈያ** ፡- ስልክ ቁጥር - 011-157-02-70

# ነፃ ሃሳብ

ይህ ዓምድ በተለያዩ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ዜጎች ነፃ ሀሳባቸውን የሚሰጡበት ነው፡፡ በዓምዱ ላይ የሚወጡ ጽሁፎች የዝግጅት ክፍሉን አቋም አያመለክቱም፡፡

## ሉዓላዊነት ለሁለንተናዊነት

ቴልጌልቴልፌልሶር (የኩሽ አሽክታብ)

‹ህብር ለሁለንተናዊ ሉዓላዊነት› የጳጉሜን 3 አንቂ ሃሳብ ሆኖ ሲመጣ በብዙ ምክንያት ነው። ሉዓላዊነት የአንድ ሀገርና ሕዝብ የመኖር፣ የመሥራት፣ እንደሀገር የመቆጠር፣ የመበልጸግ እንዲሁም የደህንነት መሠረት ነው። ቤት በምሰሶ እንደሚጸና ሁሉ የሀገር የጽናቷ ማረጋገጫም ሉዓላዊነት ነው። ትውልድ ብለን ወደራቀ ነገ የምናሻቅበው፣ እድገት ብለን ወደሚመጣው የምናየው በሉዓላዊነት በኩል ነው።

ካለው ሀገራዊ ፋይዳ አንጻር የሉዓላዊነት ቀን ደግሞ ደጋግሞ ቢከበር መልካም ነው። ሉዓላዊነት የማንነት ትልቅ ስም ነው። ታሪክ፣ ባህልና ሥርዓት በዚህ እውነታ በኩል ሲንጸባረቁ ነው ዋጋ የሚያወጡት። ኪሳችን እንደያዝነው የዜግነት መታወቂያ ሉዓላዊነትም ብሄራዊ ክብራችን፣ ብሄራዊ መታበያችን ነው። ጳጉሜን 3 በዚህ ታላቅ ቀለም ተሰይሞ መምጣቱ እንዳለፈው ጊዜ መጪውንም በዚህ መንፈስ ለመቃኘት እድል የሚሰጥ ነው ።

አንድነትና አብሮነት በሚያስፈልገን ማግስት ላይ ሥለሉዓላዊነት መነጋገር እጅግ ጠቃሚ ነው። በእርግጥ እኛ ኢትዮጵያውያን ከማንም ቀድሞ ሥለሉዓላዊነት የተረዳን ሕዝቦች ነን። በዓድዋ፣ በካራማራ፣ በአንባላጌ፣ በኡጋዴን ሉዓላዊነታችንን አስጠብቀናል። ሀገር ማለት፣ ክብር ማለት ምን ማለት እንደሆነ ለዓለም ያሳየንበት በርካታ በጎ አጋጣሚዎች አሉን።

ሁለንተናዊነትን ያቀፈ የሉዓላዊነት እሳቤ ሀገርን ከኢኮኖሚ ጥገኝነት፣ ከተረጂነትና ከደህንነት ስጋት ነጻ የሚያወጣ እሳቤ ነው። ሁለንተናዊነት ብሄርብሄረሰባዊነትን ያቀፈ፣ ብዙሃነትን የዋጀ የኢትዮጵያዊነት ዘውግ ነው። ኢትዮጵያዊነትን የምናቀነቅንበት የትውልዱ አይን ገላጭ እውቀት ነው።

በርካታ ችግሮች አንቀው በያዙን ሰሞን ሉዓላዊነት ብለን መነሳታችን እጅግ በጎ ነገር ነው። በተለይ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ እየታዩ ላሉ ችግሮች መልስ የሚሰጥ በመሆኑ ሀገር ወዳድ ለሆኑ ሁሉ በአዲስ ዓመት ዋዜማ ላይ የተበረከተ ስጦታ እንደሆነ የሚቆጠር ነው ።

ሉዓላዊነት ዋጋ የሚኖረው ሁለንተናዊነት ውስጥ ስለመሆኑ ታሪኮቻችን ምስክሮቻችን ናቸው። የተነሳንበት የማንነት ነቁጥ ከአብሮነት የጀመረ፣ በአብሮነት የቀጠለ ነው። በታሪክና በሀገር ፍቅር ዳብረን ወደዛሬ ስንመጣም በእንዲህ መሳዩ ድንበር የለሽ የሉዓላዊነት ቀለም ነው።

ነጻነትና ሚዛናዊነት የእትብታቸውን ሰፈር ከጥቋቁሮቹ ርስት ስር የተዉት ለምን ሆነና? ሡብዓዊነትና ጀግንነት በረዘመ እንዥርግ የሀበሻነት ወግ ስር ማድፈጣቸው በእንዲሁ አይደለም። በሀገሩ ቀልድ በማያውቀውና ብዙሃነትን በኢትዮጵያዊነት በመሰለ ሰውነት ነው።

‹ህብር ለሁለንተናዊ ሉዓላዊነት› መነሻው ሰውነት መድረሻው ኢትዮጵያ ናት። ህብር ውህድ ነው፣ ትስስር ድብልቅም ነው። ከብዙሀነት ውስጥ አንድነትን መውለድ፣ በአንድነት ብዙሀነትን መግለጥም ነው። ህብር ደማቅ ቀለም ነው..በአረንጓዴ ቢጫና ቀይ የደመቀ ማንነት። ህብር ብሄር ብሄረሰቦች ወደኢትዮጵያዊነት የሚያደርጉት የህብረት ዘመቻ ነው።

በጋራ ባህልና ታሪክ፣ በህብር ወግና ሥርዓት ኢትዮጵያ የሚለውን ትልቁን ስም ማጽናትም ነው። ይሄ ህብረ ቀለም ሉዓላዊነትና ሁለንተናዊነት ሲታከሉበት ሀገር የሚለውን ሙሉ ስም ይይዛል። ለዚህም ነው ጳጉሜን በሉዓላዊነት የምንዘክረው።

**በጋራ ባህልና ታሪክ፣ በህብር ወግና ሥርዓት ኢትዮጵያ የሚለውን ትልቁን ስም ማጽናትም ነው። ይሄ ህብረ ቀለም ሉዓላዊነትና ሁለንተናዊነት ሲታከሉበት ሀገር የሚለውን ሙሉ ስም ይይዛል። ለዚህም ነው ጳጉሜን በሉዓላዊነት የምንዘክረው**

ሉዓላዊነት ሀገር ተኮር በጎ አስተሳሰቦች የሚንጸባረቁበት ቢሆንም ከዛ ትይዩ በተለያየ መንገድም ሊገለጽ የሚገባው ነው። የኢኮኖሚ ፣ የፖለቲካ ...ወዘተ ሉአላዊነት በአንድ ሀገር ላይ እጅግ ወሳኝ ነገሮች ናቸው። አሁን ባለው ወቅታዊ የሀገራችን ሁኔታ ከዋናው እና ከማዕከሉ ሀገራዊ ሉዓላዊነት ጎን ለጎን የነዚህም ፋይዳ አስፈላጊ ነው።

ድሃ ሀገርና ሕዝብ የሚለውን የቆየ ስም ራሱን በምግብ በቻለ እና መካከለኛ ገቢ ያለው በሚል ስም መቀየር በኢኮኖሚ ሉዓላዊነት የሚገለጽ በጎ ገጽታ ነው። በበቃና በበለጸገ ተፈጥሮ መሃል ጸድቀን ድህነትን ታግሎ መጣል ሳንችል ድሃ በሚለው አስጸያፊ ስም ስር በዙ ዘመናትን ከርመናል። የኢኮኖሚ ሉዓላዊነት ደግሞ ለዚህ መሳዩ ሀገራዊ ውጥንቅጥ ምላሽ የሚሰጥ ነው።

ፖለቲካዊ ሉዓላዊነትም ከዚህ ጋር አብሮ የሚጠራ ጉዳይ ነው። ባልዘመነና ሃሳብ ተኮር ባልሆነ የፖለቲካ ምህዳር በርካታ ዋጋዎችን ከፍለናል በመክፈል ላይም እንገኛለን። ወደ አንድ ወገን ባጋደለ፣ የጥላቻና የዘረኝነት ትርክትን ለመፍጠር በተመቻቸ ሥርዓት ሰላም አጥተን፣ አንድነት ርቆን በብዙ ችግር ውስጥ ሰንብተናል።

ከሰላም ፈጣሪነት ወደሰላም ናፋቂነት፣ ወደጦርነትና የእርስ በርስ ግጭት ከገባን ሰነባብተናል። የፖለቲካ ሉዓላዊነት ሀገራዊ ጥያቄ ሆኖ የሚነሳው እዚህ ጋ ነው። ለዚህ አይነቱ ሀገራዊ ችግር በፖለቲካ መሠልጠንና የነቃ የውይይት መድረኮችን መፍጠር የፖለቲካ ሥልጣኔውን ከማዘመን ጎን ለጎን ወደ አዲስ የፖለቲካ ሉዓላዊነት የሚያሸጋግረን ነው።

ልክ እንደዚሁ ሁሉ የዲፕሎማሲ ሉዓላዊነትም ስለሰላምና ደህንነት፣ ስለበጎ ግንኙነት የሚተጋ እሳቤ ነው። ለይተን አየናቸው እንጂ ሁሉም የሀገር ክብር ሉዓላዊነት ቅርንጫፎች በመሆን ሲጠሩ የከረሙ ናቸው። በየትኛውም ዘርፍ ላይ ሀገርና ሕዝብን የሚጠቅም ሥራን ከሠራን ይሄ በራሱ የሉዓላዊነት መገለጫ ምልክት ነው።

አሁን ባለው ነባራዊ ሁኔታ ትግላችን ከድህነት ጋር፣ ከኋላቀርነት ጋር ነው። ስለሰላም፣ ስለልማት፣ ስለአብሮነት እየታገልን እንገኛለን። እነዚህ ሁሉ መልስ የሚያገኙት በሁለንተናዊ ሉዓላዊነት አብረን ስንቆም ነው። አዲሱን ዓመት በሀገር ፍቅር የሉዓላዊነት ስሜት መቀበላችን ያለፈውን በይቅርታ መጪውን በእርቅና በፍቅር እንድንቀበለው የሚያደርግም ነው። ከውስጥም ከውጪም የተቃጡብንን ችግሮች በድል እንድንወጣ ከማድረጉም ባለፈ ስለብሄራዊ ጥቅምም ዋጋ ያለው ነገር ነው።

# የኢትዮጵያ ኢኮኖሚ ሉዓላዊነት...

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

ስሙ ከመዝገበ ቃላቱ ላይ ከተወገደ በኋላ ኢትዮጵያ ከረሃብ ውጪ ረዥም ጊዜ አሳልፋለች:: ከደርግ የመጨረሻዎቹ ዘመናት ጀምሮ ኢኮኖሚዋ እያንሰራራ መጥቷል::

ኢትዮጵያ የኢኮኖሚ ዕድገት እያሳየች የቆየች ሀገር ናት የሚሉት ዶክተር ቆስጠንጢኖስ፤ በርካታ የዓለም የኢኮኖሚ ባለሙያዎች፣ የልማት ተንታኞች እና ዓለም አቀፍ የፋይናንስ ተቋማት የኢትዮጵያን ኢኮኖሚ እድገት በአርአያነት በማሳየት አንዳንዶች "የአፍሪካ ቻይና" የሚል ስያሜ ሲሰጡ እንደቆየ ጠቅሰዋል። ይህ ፈጣን እድገት በተለይ እ.ኤ.አ. በ2010 እና 2020 መካከል ጎልቶ የታየ ሲሆን፤ ኢትዮጵያ በዓለም አቀፍ ደረጃ በከፍተኛ ፍጥነት እያስመዘገበች ያለች ሀገር መሆኗን በዋና ዋና ዓለም አቀፍ ሚዲያዎች በተከታታይ ሪፖርት መደረጉን አንስተዋል፡፡

ይሁንና ከቅርብ ጊዜ ወዲህ የተከሰቱት ዓለም አቀፍና የሀገር ውስጥ ተግዳሮቶች በኢትዮጵያ ኢኮኖሚ ላይ ትልቅ እንቅፋት መፍጠራቸውን ምሁሩ ተናግረዋል:: የኮቪድ19 ወረርሽኝ፣ የውስጥ ግጭቶች፣ ዓለም አቀፍ አለመረጋጋት እና በሩሲያ እና በዩክሬን መካከል ያለው ጦርነት የአቅርቦት ሰንሰለቶችን በማስተጓጎል ከፍተኛ ኢኮኖሚያዊ መዘናጋት ማስከተሉንም ጠቅሰዋል:: ይህ ሁኔታ በዓለም አቀፍ ደረጃ የዋጋ ንረት ሲጨምር በኢትዮጵያ እስከ 30 በመቶ ከፍ ብሎ እንደነበር አስታውሰዋል:: ይህ አሁን ላይ ወደ ታች በመውረድ ላይ ይገኛልም ነው ያሉት።

አሁንም በኢትዮጵያ ውስጥ በከፍተኛ ሁኔታ የኢኮኖሚ ዕድገት እየታየ መሆኑን ጠቅሰው፤ባለፉት ሶስት ዓመታት ጦርነት ያስከተለው የኢኮኖሚ ውድቀት እንዳለ ሆኖ ኢትዮጵያ እስከ 7 በመቶ የኢኮኖሚ እድገት ማስመዝገብ መቻሏ ከፍተኛ ለውጥ ነው ብለዋል::

የሀገሪቱን የመሠረተ ልማት ኢንቨስትመንቶች ማለትም እንደ መንገድ ግንባታ፣ ግድቦች፣ የኃይል ማመንጫዎች እና የኢንዱስትሪ ፓርኮች ግንባታዎች ለዚህ ዕድገት ወሳኝ አንቀሳቃሾች መሆናቸውንም ነው ዶክተር ቆስጠንጢኖስ ያብራሩት:: እነዚህ እድገቶች በተለይ ለወጣቶች የሥራ እድል የፈጠሩ እና ለኢትዮጵያ ቀጣይ የኢኮኖሚ ጉዞ መሰረት የጣሉ መሆናቸውንም ያስረዳሉ::

ምሁሩ የኢትዮጵያን ኢኮኖሚያዊ ሉዓላዊነት የበለጠ ማጠናከር የሚቻለው የዋጋ ንረትን፣ የሕዝብ ጥያቄዎችን እና የጸጥታ ችግሮችን ጨምሮ የተለያዩ የውስጥ ጉዳዮችን በመፍታት እንደሆነ ይናገራሉ::

አንዳንዶች "አሁን ላይ በከፍተኛ ደረጃ በአይ ኤም ኤፍ፣ በዓለም ባንክና ሌሎች የውጭ አበዳሪዎች ጫና እየተፈጠረብን ነው ያለው:: ጫናው እየተፈጠረ ያለው በአብዛኛው የኢኮኖሚ ሉዓላዊነትን ስላጣች ነው" የሚል ፕሮፖጋንዳ ያናፍሳሉ በማለት፤ እንደ አይኤምኤፍ እና የዓለም ባንክ ያሉ ዓለም አቀፍ የፋይናንስ ተቋማት ጫና ለኢትዮጵያን ኢኮኖሚ ሉዓላዊነት የሚያሰጋ እንዳልሆነ አስምረውበታል። ይልቁንም እነዚህ በአባል ሀገራት የተመሰረቱት ተቋማት ሀገሪቱ የኢኮኖሚ ማሻሻያ ፖሊሲዋን በብቃት መተግበሯን ከቀጠለች ለኢትዮጵያ ኢኮኖሚ ልማት ጠቃሚ አጋሮች ሊሆኑ እንደሚችሉ ያመለክታሉ፡፡

"ዋናው ነገር ኢትዮጵያ ራሷን ችላ ወደፊት የኢኮኖሚ ጉዞ እድገቷን የምታስቀጥልበት፤ የንግድ ሚዛኑ ተስተካክሎ ከፍታ ላይ ሊደርስ የሚችልበት መሆን አለበት:: ለዚህ ደግሞ ዋና ዋና የሚባሉ የኢኮኖሚ ማሻሻያ ፖሊሲዎች መሬት ላይ ወርደዋል:: ይህንን በአግባቡ መተግበር ይገባል" ሲሉ ያስገነዝባሉ፡፡

ዶክተር ቆስጠንጢኖስ፤ የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ በቅርቡ የወሰደው የፖሊሲ እርምጃዎች፣ የውጭ ባንኮች እንዲገቡ መፍቀድ፣ የካፒታል ገበያ መመሥረት፣ በገበያ ዋጋ ላይ የመገበያያ ገንዘብ አወሳሰን አዎንታዊ የኢኮኖሚ ዕድገት ማሳያዎች መሆናቸውን አስረድተዋል።

ሀገሪቷ ውስጥ ከተሰሩ ከፍተኛ መሰረተ ልማቶች ውስጥ ከ100ሺህ ኪሎ ሜትር በላይ መንገዶች መሰራታቸውን፤ ይህ ደግሞ የገበያ ትስስሩን በመፍጠር ጉልህ ድርሻ እንደነበረው አስታውቀዋል:: በሀገሪቱ የሀይል ማመንጫና ግድቦች መሰራታቸውን፤ በንፋስ የሚሰሩ የኃይል ማመንጫዎችንም በሙከራ ላይ እንዳሉና ኃይል ደግሞ ለኢንዱስትሪውም ሆነ ለእርሻ እድገት ወሳኝ መሆኑን ያብራራሉ፡፡

በሌላ በኩል የንግድ ሁኔታውም መስፋፋቱን፤ የአገልግሎት ሴክተሩ በከፍተኛ ደረጃ ማድግ እንደቻለ፤ ይህም ሰዎች ሥራ ላይ በሰፊው መሰማራታቸውን አመላካች መሆኑንና እነዚህ መሠረተ ልማቶች በሙሉ ለሀገሪቱ የኢኮኖሚ እድገት ጉልህ አስተዋጽኦ ማበርከታቸውን ዶክተር ቆስጠንጢኖስ አብራርተዋል::

እንደ እርሳቸው ማብራሪያ፤ አንድ እድገት በአንድ ዓመት እና በሁለት ዓመት የሚመጣ አይደለም:: ኢትዮጵያ የጀመረችው የኢኮኖሚ እድገት ጉዞ፤ ድህነት ቅነሳና ዘላቂ የልማት ግብ ፕሮግራም ተብሎ በተቀመጠው የአምስት ዓመት አቅድ፤ በሁለት ምዕራፍ በተተገበረው የእድገትና ትራንስሮርሜሽን እቅድ፣ እንዲሁም የለውጡ መንግሥት ከመጣ በኋላ ተግባራዊ ባደረጋቸው ሀገር በቀል የኢኮኖሚ ማሻሻያ ፖሊሲዎች አማካኝነት የተመዘገበ ነው ይላሉ::

በኢትዮጵያ ባለፉት 20 ዓመታት ውስጥ ከፍተኛ የመሠረተ ልማት ሥራዎች ተሰርተዋል:: ዩኒቨርሲቲዎች ተገንብተዋል:: በርካቶች የትምህርት እድል አግኝተዋል:: የትምህርትና የጤና ተደራሽነት ተስፋፍቷል:: የምዕተ ዓመቱ ግቦች የሚባሉትን በዓለም አቀፍ ደረጃ የተተገበረውን ኢትዮጵያ ሙሉ በሙሉ አሟልታለች ነው ያሉት::

ሆኖም በተለያዩ የሀገሪቱ ክፍሎች እየተከሰቱ ያሉ የጸጥታ ችግሮች በፍጥነት ካልተፈቱ እነዚህን ጥረቶች ሊያበላሹ እንደሚችሉም አስጠንቅቀዋል:: ምሁሩ በተለይ በፕሪቶሪያ የሰላም ስምምነት ከተጠናቀቀው የሰሜኑ ጦርነት በኋላ ለመልሶ ግንባታው ከወጣው ከፍተኛ ሀብት አንፃር ኢኮኖሚያዊ እድገትን ለማስቀጠል ሰላም ወሳኝ መሆኑን አፅንዖት ሰጥተዋል።

የፕላንና ልማት ኮሚሽን እስከ 2013 ዓ.ም ድረስ ያለውን የልማት አፈጻጸም አስመልክቶ ባወጣው ሪፖርት ላይ እንዳመላከተው፤ ኢትዮጵያ ባለፉት አስር ዓመታት በኢኮኖሚ እድገት ከፍተኛ እመርታ በማስመዝገብ በመንግሥት የሚመራ የልማት እቅድ እና በቁልፍ ዘርፎች ስትራቴጂካዊ ኢንቨስትመንቶች ተንቀሳቅሳለች። ሀገሪቱ ተከታታይ እና ፈጣን የኢኮኖሚ መስፋፋት ያስገኙ ታላላቅ የልማት ስትራቴጂዎችን በመተግበር ኢትዮጵያን በአፍሪካ የዕድገት ተምሳሌት አድርጓታል። ይሁን እንጂ ጉዞው ያለ ተግዳሮቶች አልነበረም፣ እናም የኢትዮጵያ ኢኮኖሚ የወደፊት ጉዞ እነዚህን መሰናክሎች በመቅረፍ እና ፍጥነትን በማስቀጠል ላይ የተመሰረተ ነው ይላል።

እንደ ሪፖርቱ ገለጻ፤ የኢትዮጵያ ኢኮኖሚ እድገት አስደናቂ ቢሆንም ለውስጣዊም ሆነ ውጫዊ ጫናዎች የተጋለጠ ነው። ለወደፊት የዕድገት ስኬት የሚወሰነው መንግሥት እነዚህን ተግዳሮቶች የሚቀርፉ ማሻሻያዎችን በመተግበር፣ ሰፊ የሥራ ዕድል በመፍጠርና የዕድገት ጥቅማ ጥቅሞች በሕዝብ መካከል በስፋት እንዲካፈሉ ማድረግ ነው። በትክክለኛ ፖሊሲዎች ኢትዮጵያ በመጪዎቹ ዓመታት ወደ በለፀገ እና የማይበገር ኢኮኖሚ የምታደርገውን ለውጥ የማስቀጠል አቅም አላት።

ግዙፍ ኢኮኖሚ ካላቸው ሀገራት መካከል ኢትዮጵያን በአምስተኛ ደረጃ ላይ ያስቀመጠው አይ ኤም ኤፍ 205 ነጥብ1 ቢሊዮን ዶላር ጠቅላላ የሀገር ውስጥ ምርት በማስመዝገቧ እንደሆነ አመልክቷል። ይህ የኢኮኖሚ እድገቷ ከዓለም በ57ኛ ደረጃ ላይ መቀመጧን ያሳያል።

በአፍሪካ በኢኮኖሚ ግዝፈት ከ1ኛ እስከ 4ኛ ያለውን ደረጃ የያዙት ሀገራት ደቡብ አፍሪካ፣ ግብፅ፣ አልጄሪያ እና ናይጄሪያ መሆናቸውን መረጃው ጠቅሷል።

ሀገሪቱ ሰላሟን ማስጠበቅ እና የዕድገት ጉዞዋን ማስቀጠል ከቻለች የወደፊት ኢኮኖሚያዊ ተስፋዋ ብሩህ ነው ያሉት ዶክተር ቆስጠንጢኖስ፤ የአካባቢ አስተዳደር አካላት በተለይም በወረዳ ደረጃ ያሉት የልማት አንቀሳቃሾች ማብቃት እንደሚያስፈልግ አሳስበዋል። ከዚህ ባለፈም ስር የሰደደ እና የኢትዮጵያን የኢኮኖሚ እድገት እንዳያደናቅፍ ሙስና እና ሌብነትን ለማጥፋት የተቀናጀ ጥረት እንዲደረግ አሳስበዋል፡፡

# “ቅድመ አያቶቻችን ...

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

ለጋዜጠኞች በሰጡት መግለጫ እንደተናገሩት፤ የጳጉሜን ወር ስናስብ ከቅርብ ዓመታት ወዲህ ቀናቱን በተለያዩ ሀገራዊ ጉዳዮች በመሰየም እያከበርን እንገኛለን:: ዕለቶቹ ሀገር ለመገንባት፣ ትውልድ ለማፅናት የምንጓዝበትን መንገድ የምንፈትሽባቸው እና ለሀገር ሲሉ ዋጋ የከፈሉ ዜጎቻችንን በክብር የምናስብባቸው ናቸው።

ዘንድሮም በጳጉሜን ቀናት ከሚታሰቡ አበይት ጉዳዮች መካከል አንዱ የሉዓላዊነት ቀን ነው ያሉት ኢንጂነር አይሻ፤ ቅድመ አያቶቻችን በከፈሉት መስዋዕትነት ያላስደፈሩትን የሀገር ነፃነት የእኛ ትውልድ ጠብቆ ለትውልድ ማስተላለፍ አለበት ብለዋል።

ጳጉሜን 3 የሉዓላዊነት ቀን ተብሎ "ህብር ለሁለንተናዊ ሉዓላዊነት" በሚል መሪ በተለያዩ ዝግጅቶች ይከበራል ያሉት ኢንጂነር አይሻ፤ የበዓሉ ዋና ዓላማ ፈተናዎችን ወደ መልካም እድል በመለወጥ ነፃነቷ የተጠበቀ፣ እድገቷ የተረጋገጠና ሉዓላዊነቷ የተጠበቀ ኢትዮጵያን ለትውልድ ማውረስን በተመለከተ መልዕክት ለማስተላለፍ መሆኑን ገልጸዋል።

የሉዓላዊነት ቀን ሲከበርም ዛሬ ማለዳ በመከላከያ ጠቅላይ መምሪያ በክብር የሰንደቅ ዓላማ የመስቀል ሥነ-ሥርዓት እንደሚከናወን ነው የተናገሩት።

በተጨማሪም ለኢትዮጵያ ሉዓላዊነት ውድ ዋጋ ለከፈሉ ጀግኖች የጧፍ ማብራት፣ ምስጋና፣ መልዕክት፣ የሕሊና ጸሎት እና ቃል-ኪዳን የመግባት ሥነ-ሥርዓት እንደሚካሄድ ጠቁመዋል።

እነዚህ ሥነ-ሥርዓቶች እንደተጠናቀቁም በሳይንስ ሙዚየም የአውደ-ርዕይ ዝግጅት፣ የሉዓላዊነት የሕፃናት መዝሙር ይፋ የማድረግና የፓናል ውይይት እንደሚካሄድም አብራርተዋል።

ከቀኑ 6 ሰዓትም በመላ ኢትዮጵያ ለሁለት ደቂቃ ኢትዮጵያውያን ባሉበት በመቆም ለሉዓላዊነት ለተከፈለው ዋጋ ክብር የመስጠት ሥነ-ሥርዓት በማካሄድ ዝግጅቱ እንደሚጠናቀቅ ገልጸዋል።

የበዓሉ አዘጋጆች የኢፌዴሪ መከላከያ ሚኒስቴር፣ ግብርና ሚኒስቴር፣ የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ፣ ብሔራዊ መረጃና ደህንነት አገልግሎት፣ የኢንፎርሜሽን መረብ ደህንነት አገልግሎት፣ ፌዴራል ፖሊስ ኮሚሽን እና የአደጋ ሥጋት ሥራ አመራር ኮሚሽን መሆናቸው ታውቋል፡፡

# ወታደር ያቆየው ታሪክ-...

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

የራስን ሉዓላዊነት ከማስጠበቅ ባሻገር በሰላም ማስከበር ተልዕኮዎች ውስጥ በመሳተፍ ከፍተኛ ድል ማስመዝገብ መቻሏን ዓለም አቀፍ ተቋማትና የታሪክ ድርሳናት ይመሰክራሉ:: እንደ ደቡብ ሱዳን፣ ሶማሊያ እና ዳርፉር ባሉ አካባቢዎች ከፍተኛ ተሳትፎ አድርጋለች:: በተባበሩት መንግሥታት ድርጅት የሰላም ማስከበር ሥራዎች በዓለም አቀፍ ደረጃ ከፍተኛ አስተዋፅዖ ከሚያደርጉት ውስጥ አንዱ የኢትዮጵያ መከላከያ ሠራዊት መሆኑም የሚታወቅ ነው:: በተለይም በሶማሊያ የአፍሪካ ህብረት ተልዕኮ (አሚሶም) ውስጥ የአልሸባብ አማፂያንን በመዋጋት እና የአፍሪካ ቀንድን በማረጋጋት ረገድ ሚናው ከፍተኛ ነው።

በተለያዩ ፈተናዎችና ስኬቶች ያለፈው የመከላከያ ሰራዊት ተቋሙ በለውጥ ንቅናቄ ሂደት የተጓዘባቸው መንገዶች ላይ ከከፍተኛ የመንግሥት አመራሮች ጋር የጋራ አረዳድ ለመፍጠር መድረክ በቅርቡ ሲካሄድ ፤ የኢፌዴሪ ጦር ኃይሎች ጠቅላይ አዛዥ እና ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ የኢትዮጵያ ታሪክ ዋነኛ መሠረት ወታደር እንደሆነ ተናግረዋል:: ወታደር ሆኖ ማገልገል ትልቅ ክብር መሆኑን የተናገሩት ጠቅላይ ሚኒስትሩ፤ ብቸኛ ህይወትን በመስጠት የሚከፈል መስዋዕትነት መሆኑንም አብራርተዋል::

"የሀገራችን ኢትዮጵያ ታሪክ መሠረቱ ወታደር ነው:: ኢትዮጵያ ስለምትባል ሀገር ደርዝ ያለው ታሪክ አንስተን የምንናገር ከሆነ ከውትድርና ታሪክ ብዙ አንርቅም" ነው ያሉት::

"ሀገር የሚባል ነጻነት ያለው፤ ድንበር ያለው በቅኝ ያልተገዛ ቢባል አሁን የምናውቀው ቅጥር የተፈጠረው በወታደር ነው:: ሉዓላዊነት የምንለው ወታደር ያቆየው ታሪክ ነው:: ነጻነት የምንለው ወታደር ያቆየው ታሪክ ነው:: ይህ በብዙ ዘርፍ ቢታይ የኢትዮጵያ ታሪክ ሲቀዳ ዋናው የሚገኘው ጉዳይ የወታደር ታሪክ ነው" ሲሉ ሠራዊቱ ያለውን የሀገር ወዳድነት ሞራል አብራርተዋል::

ኢትዮጵያ ስንል በውስጡ የምናየው ሀገሩን የሚወድ፤ ስለ ሰፈሩ ሳይሆን ስለ ሀገሩ የሚያስብ የሀገሩን ክብር በጥልቀት የሚያየ የወታድር ታሪክ ነው በማለት፤ ይህ ታሪክ ብቻ ሳይሆን በሌላ በኩል ደግሞ የሲቪል አመራሮችም ለኢትዮጵያ ጊዜያቸውን እየሰጡ ስለመሆናቸው ጠቅሰዋል::

አይተኬ የሆነው የህይወት መስዋዕትነት ነው ያሉት ጠቅላይ ሚኒስትሩ፤ አንዴ ብቻ የሚገኝና ዳግም በእውቀትና በገንዘብ አቅም ማደስ የማይቻለውን ህይወት የሚገብረው ወታደር መሆኑን አንስተዋል:: ይህንን ወታደር የመውደድና የማክበር የሀገር ታሪክ አካል የማድረጉ ጉዳይ ይበልጥ እየሰፋ ልማድ እንዲሆን ወታደር ምንድነው የሚለውን ማወቅ አስፈላጊ መሆኑን ገልጸዋል፡፡

ወታደር የላቀ ዓላማ ሊኖረው እንደሚገባ በመግለጽ፤ ከሰፈር የዘለለ የላቀ ዓላማ ከሌለውና ለመስዋዕትነትም ዝግጁ ካልሆነ ወታደር ሊባል አይችልም ነው ያሉት::

የትኛውንም ተስፋፊ ኃይል የሚመክት ሠራዊት ተገንብቷል ሲሉ የገለጹት ደግሞ የጦር ኃይሎች ጠቅላይ ኤታማዦር ሹም ፊልድ ማርሻል ብርሀኑ ጁላ ናቸው:: እርሳቸው ይህንን ያሉት በ47ኛው የምሥራቅ ዕዝ ምስረታ በዓል ላይ ያስተላለፉት መልዕክት ነው፡፡

ተስፋፊነት የጦርነት ነጋሪት መሆኑን የገለጹት ጠቅላይ ኤታማዦር ሹም ፊልድ ማርሻል ብርሀኑ፤ ሠራዊቱ ኢትዮጵያን ለመውረር የሞከሩ ኃይሎች ለመመከት የሚያስችል ቁመና ላይ እንደሚገኝ ገልጸዋል:: "ሀገራችንን ለመውረር ግፊት ሲያደርጉና ግጭት ሲያባብሱ የነበሩ የሀገራችን ታሪካዊ ጠላቶች አብረው የቆሙ ቢመስሉም በሽንፈት ጊዜ እንደማይገኙ ከታሪክ መማር ይገባል" ነው ያሉት፡፡

ሠራዊቱ በቀጣናው ያለውን የተስፋፊዎች የጦርነት ነጋሪት ጉሰማ ለመመከት የሚያስችል የተሟላ ወታደራዊ ቁመና ላይ እንደሚገኝና ሕዝቡ ላይ ስጋት ለመፍጠር የሚሞከሩ ተላላኪዎችን መስማት እንደሌለበት ገልጸዋል፡፡

ውስጣዊ ችግሮች ቢኖሩም ሀገርን ከጥቃት ለመከላከል ብቻ ሳይሆን ከሞከሩ ዳግመኛ እንዳያስቡት አድርጎ ለመመከት የሚያስችል ዝግጁነት መኖሩን የተናገሩት ፊልድ ማርሻል ብርሃኑ፤ በጦርና በጋሻ ታንክ በመመከት በነፃነት የቆየን የጀግኖች መገኛ መሆናችንን የምሥራቁ የሀገራችንን ድንበር ለመመከት ለዕዙ የሚደረግ ማንኛውንም ድጋፍ መከላከያ እንደሚያደርግ መላው የሀገራችንና የክልሉ ማህበረሰብ ለዕዙና ለሠራዊታችን የሚያደርጉትን ድጋፍ አጠናክረው እንዲቀጥሉ ጠይቀዋል፡፡

በዓሉን አስመልክተው መልእክት ያስተላለፉት ጀኔራል አምባሳደር ባጫ ደበሌ፤ የምሥራቅ እዝ የሀገርን አንድነት ሰላምና ሉዓላዊነት ለማረጋገጥ ከፍተኛ መስዋዕትነት መክፈሉን ገልጸዋል:: ለሀገር ሉዓላዊነት መከበር ህይወታቸውን ጭምር መስዋዕት ለማድረግ ወደ ኋላ የማይሉ የሠራዊት አባላት መኖራቸውንም ነው የጠቀሱት::

በተለይም ምሥራቅ ዕዝ የተቋቋመው የሶማሊያን ወረራ ለመከላከልና የሀገር ሉዓላዊነትን ለማስከበር እንደሆነ የጠቀሱት ጀኔራል አምባሳደር ባጫ፤ ዕዙ የተሰጠውን ሀገርን የማስከበር ተልዕኮ በታላቅ ጀግንነትና በትጋት በከፈለው መስዋዕትነት ከሌሎች አሃዶችና ከመላው የኢትዮጵያ ሕዝብ ጋር በመሆን ወራሪውን ኃይል አሳፍሮ መመለስ እንደቻለ አብራርተዋል:: ምሥራቅ እዝ በሀገር ውስጥ በተለይም በምሥራቅ ኢትዮጵያ በሐረሪ፣ ሱማሌ፣ አጋዴን እንዲሁም በምሥራቅና ምዕራብ ሀረርጌ ዞኖች፣ አርሲና ባሌ አካባቢዎች ላይ ይፈጠሩ የነበሩ ከፍተኛ የጸጥታ ችግሮችን በወሰደው ተከታታይና እልህ አስጨራሽ የጸረ ሽምቅ ተጋድሎ አካባቢዎቹ አሁን ላይ ለሚገኙበት ሰላምና ዕድገት የራሱን አስተዋጽኦ የተወጣ መሆኑን አንስተዋል::

የኤርትራን ወረራ ተከትሎ ወደ ቡሬ የተንቀሳቀሰው ምሥራቅ ዕዝ ከሌሎች አጋር እዞችና ክፍሎች ጋር ተሳስሮ የተቃጣውን ወረራ ድል በማድረግ ወደ ሰላም ስምምነት እንዲመጣ ያደረገ የሀገር ዋልታና ማገር መሆኑን ጀኔራል አምባሳደር ባጫ ተናግረዋል:: የሀገርን ሰላምና ሉዓላዊነት ከማስከበሩም ባሻገር በጎረቤት ሀገር ሶማሊያ ተሰማርቶ የሶማሊያን ሕዝብና መንግሥት ከአልሻባብና ከሌሎች ጥቃቶች በመከላከል ከፍተኛ የሆነ መስዋዕትነት በመክፈል ድል ያስመዘገበ ነው ያሉት::

ማህበራዊ

# የሕይወት ገጽታ

## ‹‹ኢትዮጵያ በሉዓላዊነቷ የሚደራደር ትውልድ ኖሯት አያውቅም››

ሻምበል ዋኘው ዓባይ ወልደ ማርያም
(የኢትዮጵያ ጀግኖች አርበኞች ማህበር አባል)

**ራስወርቅ ሙሉጌታ**



ፎቶ- ዳኜ አበራ

ሻምበል ዋኘው ዓባይ ወልደ ማርያም ይባላሉ። የተወለዱት በ1449 ዓ.ም መስከረም አንድ ቀን በጎንደር ከተማ ጨዋ ሰፈር በሚባለው አካባቢ ቆብ አስጥል በምትባል ቦታ ነው። አባታቸው የወገራ አውራጃና አካባቢው የነጭ ለባሽ ጦር አዛዥ፤ የበየዳ፤ የአርማጭሆ፤ የጠለምት፤ የሰሜን ደባርቅ ወረዳዎች ገዢ እንዲሁም የአውራጃው ረዳት ገዢ ሆነውም ለዓመታት አገልግለዋል።

በእነዚህ ጊዜያትም ሻምበል ዋኘው ከአራት ዓመታቸው ጀምሮ አባታቸው በአስተዳደር በተመደቡባቸው ቦታዎች ሁሉ እየተዘዋወሩ የልጅነት ጊዜያቸውን የቤተክህነት ትምህርት በመማርና በድቁና በቤተክርስቲያን በማገልገል አሳልፈዋል። ዘመናዊ ትምህርት ቤትን ሲቀላቀሉም በቤተክርስቲያን የቀደመ ትምህርት ስለነበራቸው የጀመሩት ከአራተኛ ክፍል ነበር።

በዚህ ሁኔታ ከቆዩ በኋላ በ1967 ዓ.ም የሰባተኛ ክፍል ትምህርታቸውን አቋርጠው ኢህአፓን በመቀላቀል በርሃ ገብተው በወቅቱ የነበረውን የደርግ መንግሥት በመቃወም ለሶስት ዓመት ተኩል በታጋይነት ቆይተዋል። ከዚህ በኋላ ግን በአባታቸው ጥያቄና ትእዛዝ መሠረት መንግሥትን ምህረት ጠይቀው ሰላማዊ ኑሮ ለመጀመር በቁ።

በዚህ ሁኔታ እስከ 1972 ዓ.ም ከቆዩ በኋላ የኢትዮጵያን ሠራዊት በመቀላቀል በአስራ ስምንተኛው ተራራ ክፍለ ጦር ሰላሳ አምስተኛ ብርጌድ በመመደብ አገልግሎት የጀመሩ ሲሆን በታጠቅ እና በሀረር ሁርሶ ማሠልጠኛዎች በመግባት ወታደራዊ እና የፖለቲካ ትምህርት ሥልጠናዎችን ተከታትለዋል። ከዚህ በኋላ በወቅቱ በትግራይና ኤርትራ ክፍለ ሀገራት በተለያዩ ቦታዎች በአውደ ውጊያዎች እስከ 1976 ዓ.ም ተሰልፈዋል። በ1976 ዓ.ም ወደ ሀረር ጦር ትምህርት ቤት በመመለስ የመቶ አለቅነት ኮርስ ካዴት በመውሰድ በምክትል መቶ አለቅነት ተመርቀው እስከ ሻምበል ማዕረግ በመድረስ በተለያዩ የሀገሪቱ ክፍሎች በውትድርና ሳይንስና በፖለቲካ ትምህርት አሠልጣኝነት ለማገልገል በቅተዋል።

ከዚህ በኋላም ወደ ሩስያ ለከፍተኛ ትምህርት የተላኩ ቢሆንም ከአስር ወራት ቆይታ በኋላ የእናት ሀገር ጥሪ በመደረጉ ትምህርታቸውን አቋርጠው ወደ ሀገር ቤት በመመለስ በውትድርናው ቀጥለዋል። ከመንግሥት ለውጥ በኋላም ወደ ላይቤሪያ በመሄድ ለጥቂት ወራት በምግብ ቤት ሠራተኝነት ሲሠሩ ቆይተው ሁኔታዎች ስላልተመቿቸው ወደ ሀገር ቤት ተመልሰዋል። ከዚህ በኋላ በሀገር ቤት በነበራቸውም ቆይታ የተለያዩ ሥራዎችን ከመሥራት በተጓዳኝ ያቋረጡትን ትምህርት በመከታተል በማኔጅመንት የመጀመሪያና የሁለተኛ ዲግሪያቸውን ለመያዝ፤ ትዳር በመመስረትም የአራት ልጆች አባት ለመሆን በቅተዋል።

የሻምበል ዋኘው አባት የኢትዮጵያ ጀግኖች አርበኞች ማህበር ሲመሠረት ተመራጭ በመሆን የሥራ አስፈጻሚ ሆነው አገልግለው ነበር ። በዚህም ምክንያት በ2006 ዓ.ም የአርበኛ ልጆች ማህበሩን እንዲቀላቀሉ መወሰኑን ተከትሎ ሻምበል ዋኘው በጊዜያዊ ዋና ጸሀፊነትና ሥራ አስፈጻሚ በመሆን ለሰባት ዓመታት አገልግለዋል።

ከ2013 ዓ.ም ጀምሮም በማህበሩ የበጎ ፈቃደኛ የነጻ አገልግሎት ሰጪ በመሆን እያገለገሉ ይገኛሉ። እኛም ለዛሬው የሕይወት አምድ እትማችን ከሀገር ሉዓላዊነት መጠበቅ ጋር ያላቸውን ተሞክሮ እንዲያጋሩን እንግዳችን አድርገን አቅርበናቸዋል።

**አዲስ ዘመን፡- ኢትዮጵያ ሉዓላዊነቷን አስጠብቃ የኖረች ሀገር ናት ። ኢትዮጵያውያንም በሀገራቸው ሉዓላዊነት አይደራደሩም ይባላል ይህንን እንዴት ያዩታል ?**

**ሻምበል ዋኘው፡-** ኢትዮጵያ ሉዓላዊነታቸውን አስጠብቀው ዘመናትን ከተሻገሩ ጥቂት ሀገራት መካከል አንዷ ናት። ሉዓላዊነቷ ተጠብቆ ኖሯል ስንል ግን አንድነቷን ለማፍረስ ሕዝቦቿን ለመበታተን በርካታ የተሸረቡ ሴራዎችና ሳይሳኩ የቀሩ ሙከራዎች እንደነበሩ ሳንዘነጋ ማለት ነው። እነዚህ ዛሬም ድረስ ተሻግረው ስጋት እየሆኑ ያሉ ሀገር የማፍረስ እና ሕዝብን የመበታተን ሙከራዎች ሳይሳኩ የቀሩት ደግሞ በእድል ወይንም በአጋጣሚ አልነበረም። ይልቁንም ቀደምት ኢትዮጵያውያን አባቶች በከፈሉት ዘመን ተሻጋሪ የጀግንነት መስዋእትነት ነው። እነዚህ ቀደምት ኢትዮጵያውያን በየዘመናቱ የውጭ ወራሪዎችና ሀገር በታኞችን ሲመክቱ የነበሩት የኢትዮጵያን ሉዓላዊነትና ጥቅም በማስቀደም የጠነከረ አንድነት በመፍጠር ነበር። የሀገርን ዳር ድንበር የሀገርን ሉዓላዊነት የሚነካ ጉዳይ ሲፈጠር የውስጥ ችግርን ቅሬታና ግጭትን ወደጎን በመተው በአንድ መሰባሰብ ለኢትዮጵያውያን የተለመደና ሀገር ያቆየ መለያቸው ነው። ይህንን የተረዱ ኢትዮጵያን ለማፍረስ የማይተኙ ሀገራትም ምንም እንኳን ባይሳካላቸውም ዛሬም ድረስ እየሞከሩ ያሉት የውስጥ አንድነትን በመረበሽ ዓላማቸውን ለማሳካት ነው።

> **የሀገርን ዳር ድንበር የሀገርን ሉዓላዊነት የሚነካ ጉዳይ ሲፈጠር የውስጥ ችግርን ቅሬታና ግጭትን ወደጎን በመተው በአንድ መሰባሰብ ለኢትዮጵያውያን የተለመደና ሀገር ያቆየ መለያቸው ነው**

ይህም ሆኖ ዛሬም ድረስ ኢትዮጵያ በሉዓላዊነቷ የሚደራደር ትውልድ ኖሯት አያውቅም። ለዚህ ጥሩ ማሳያ እንዲሆን የቅርብ ጊዜውን ታሪክ ማነሳት እንችላለን። ይህም ኤርትራ አንደ ሀገር ከቆመች በኋላ ከኢትዮጵያ ጋር አድርጋው የነበረው ጦርነት ነው። በወቅቱ ኢትዮጵያ የነበራት የአስተዳደር ሥርዓት ብሄር ተኮር ማለትም ቋንቋን መሠረት ያደረገ አደረጃጀት በመሆኑ በውጭ ሃይሎች ዘንድ ከፍተኛ መከፋፈል እንዳለ ተደርጎ ይወራ ነበር። በእርግጥም እስከ ጦርነቱ መጀመር ድረስ በሀገር ውስጥም ሆነ በውጭ የነበረው ኢትዮጵያዊ ኢትዮጵያ ከሚለው መገለጫ ይልቅ ቋንቋን መሠረት ያደረገውን ማንሳት ተስፋፍቶ ነበር። ይህንን ያስተዋሉ አንዳንዶች ኢትዮጵያ ከኤርትራ ጋር ጦርነት ውስጥ ከገባች ቀሪው የሀገሪቱ ክፍልም የመበታተን የመገነጣጠልና የእርስ በእርስ ጦርነትም ይፈጠራል የሚል ስጋት ነበራቸው።

ይህ ስጋት ደግሞ በውጭ ሃይሎች ብቻ ሳይሆን ኢትዮጵያንና ኢትዮጵያውያንን በቅጡ ባልተረዱ ሀገር እንድትፈርስ በሚፈልጉ ጥቂት የሀገር ልጆችም ውስጥ የነበረ ነው። ነገሩ ግን እንደተጠበቀውም እንደተፈራውም ሳይሆን ቀርቶ በኢትዮጵያ አሸናፊነት ጦርነቱ ተጠናቆ ሀገሪቷም ዛሬ ለይ ለመድረስ በቅታለች። ዛሬም አሁን ያለውን መንግሥት የሚቃወሙ አካላት እንዳሉ ይታወቃል። ነገር ግን በኢትዮጵያ ሉዓላዊነት ረገድ ማንም ጥያቄ ሲያነሳ ሰምተን አናውቅም። ይህ ደግሞ ከውጭም ሆነ ከሀገር ውስጥ በኢትዮጵያ ሉዓላዊነት ጉዳይ ገብተው ለመፈትፈት ለሚያስቡ አካላት ጥሩ መልእክት የሚያስተላልፍ ነው።

**አዲስ ዘመን፡- ኢትዮጵያውያን ለሉዓላዊነታቸው ያላቸውን ቀናኢነት እንዴት ይመለከቱታል ?**

**ሻምበል ዋኘው፡-** የሉዓላዊነት ጥያቄ የሀገርና የሕዝብን ጥያቄ መሠረት ያደረገ ነው። ዛሬ ላይ ኢትዮጵያ ሁለት ጉዳዮችን ቅድሚያ ትኩረት ሰጥታ እየሠራች እንደሆነ እረዳለሁ። እነዚህ ጉዳዮች ደግሞ ከተለያዩ ሀገራት ጋር ጥርስ ያጋቡንም ናቸው። አንደኛው የህዳሴው ግድብ ነው። በዓባይ ወንዝ ላይ ግድብ ለማቆም በኢትዮጵያ የነበሩ መንግሥታት በሙሉ ሃሳብም ጅምርም የነበራቸው ቢሆንም ዛሬ የደረስንበትን ያሳዩን ግን የቀድሞው ጠቅላይ ሚኒስትር አቶ መለስ ዜናዊ ናቸው።

እሳቸው ግድቡን በጀመሩበት ወቅትም በርካታ የሀገሪቷን ሉዓላዊነት የሚፈታተኑ ነገሮች ከግድቡ ጋር በተያየዘ ገጥመው ነበር፡፡ ነገር ግን አንዳቸውም አልተሳኩም። በቅርቡም ሃያል የተባለችው ሀገር አሜሪካ መሪ ሳይቀሩ የህዳሴው ግድብ በግብጻውያን በቦምብ ለሚታ እንደሚችል ነግረውን ነበር። ግን እውን የሆነ ነገር የለም። የህዳሴው ግድብ እዚህ መድረስ ለሀገሪቱ የልማት ጅማሮ መሠረት የጣለ ነው። ከዚህ በኋላ የሚሠሩ በርካታ ሥራዎችም እንደሚኖሩ ተስፋ አለኝ ። እኛ አንድ ሆነን ትልቅ ሥራ ሥንሰራ ጠላቶቻችን ከሴራ መታቀባቸው አይቀርም።

ሁለተኛው ኢትዮጵያን የባሕር በር እንድታገኝ መንግሥት የጀመረው ሰላማዊ እንቅስቃሴ ነው። ይህ ብዙዎችን ያስደነገጠ ሃሳብ ነው፡፡ ኢትዮጵያ የጠየቀችው የባህር በር ጥያቄ የማንንም ሉዓላዊ ሀገር በጉልበት ለመጠቅለል የሚደረግ ሙከራ አይደለም። በዚህ ረገድ አሁን ጣልቃ እየገቡ ያሉት ሀገራት የሚሠሩት ሥራ ግን የኢትዮጵያን ተጠቃሚነት ብቻ ሳይሆን ሉዓላዊነትም የሚገዳደር ነው። በዚህ ረገድ እኔ የምለው ነገር ቢኖር በመንግሥት በኩል እየተሠሩ ያሉ ሥራዎችን መላው ኢትዮጵያዊ መደገፍ እንዳለበት ነው። የውጭ ጉዳይ ሚኒስትሩ አምባሳደር ታዬ አጽቀ ስላሴ በዲፕሎማሲው መስክ እየሠሩ ያሉትን አኩሪ ሥራዎች እየተመለከትን ነው። በመንግሥት በኩል ይህ ሥራ ተጠናክሮ ሊቀጥል ይገባል። እንደ ዜጋም ይህ ጅማሮ ውጤት እንዲያመጣ በያለንበት ከመንግሥት ጎን ልንቆም ይገባል። ይህንን የምለው ለግለሰቦች ብቻ አይደለም። በፖለቲካ አመለካከት ልዩነት በተቃውሞ ጎራ ለተሰለፉትና የትጥቅ ትግል ለሚያደርጉትም ነው። በኢትዮጵያ ሉዓላዊነት ጉዳይ የሀገርን ጥቅም ማስጠበቅ ብቻ ሳይሆን ሆደ ሰፊ ሆኖ ነገሮችን መቻልም ይጠበቃል። ያለንን ልዩነት ወይንም ግጭት የሀገርን አንድነትና ሉዓላዊነት እስከሚፈታተን ልናደርስ አይገባም።

**አዲስ ዘመን፡- እስካሁን የቆየውን የኢትዮጵያ ሉዓላዊነት አስጠብቆ ለመቀጠል ከማን ምን ይጠበቃል ?**

**ሻምበል ዋኘው፡-** የሉዓላዊነት ጉዳይ ሲነሳ ከድንበር ጋር ብቻ መያያዝ የለበትም ። በእርግጥ በዋናነት የሀገርን ድንበር መጠበቅ ወራሪዎችን ሸንፈት አከናንቦ መመለስ የግድ የሚል ቢሆንም ሉዓላዊነት ግን ከዚህም በዘለለ በኢኮኖሚውና በውስጣዊ አንድነት በማጠናከሩም ረገድ ብዙ መሥራት ይጠበቃል። ይህ ማለት ደግሞ የሀገር ሉዓላዊነት ለማስጠበቅ ሁሉም ዜጋ በየደረጃው በያለበት ሃላፊነት አለበት ማለት ነው።

የአንድ ሀገር ሉዓላዊነት ጥያቄ ውስጥ የሚገባው ጠመንጃ ይዞ የመጣ ወራሪ ሲከሰት ብቻ ሳይሆን በድህነት እጅን ለልመና መዘርጋት ሲጀመርም ነው። ወጣቶች ሥራ አጥ ሆነው ከሀገር ሀገር መሰደድ ሲጀምሩ ሉዓላዊነት ጥያቄ ምልክት ውስጥ መግባቱ አይቀርም። ባጠቃላይ ኢኮኖሚው ሲዳከምና የውስጥ አንድነት ሲናጋ ሉዓላዊነትን በሚጋፋ መልኩ የውጭ ሃይሎች ጣልቃ ገብነት መከሰቱ አይቀሬ ነው።

በመሆኑም ስለ ሉዓላዊነት ስናነሳ ስለ እድገት ስለ ብልጽግና ማሰብ የግድ የሚል ይሆናል። በሌሎች ሀገራት እንደምናየው ሉዓላዊነታቸውን አስከብሮ ለመኖር ከሌሎች የሚጠይቁት የሚለምኑት ነገር እንዳይኖር ጠንክረው ይሠራሉ። እኛ ሀገር ያለውም ሁኔታ ከዚህ

ወደ ገጽ 7 ዞሯል

ማህበራዊ

# የሕይወት ገጽታ

## ‹‹ኢትዮጵያ በሉዓላዊነቷ…

ከገጽ 6 የዞረ

ጋር የሚመሳሰል ሊሆን ይገባል። ብዙ ጊዜ የሌሎች ሀገራት ጣልቃ ገብነት ሲከሰትብን የምናየው አንድም በመሀከላችን ያለ ክፍተትን አለ ብለው ሲያምኑ ያንን በመጠቀም ነው። አልያም ያለብንን የኢኮኖሚ ችግር መነሾ በማድረግ የርዳታ እጃቸውን በመዘርጋት ነው።

በመሆኑም ሥራ በመሥራት ራስን መቻልና ሀገርን ማልማት በሌላ በኩል ሉዓላዊነትን ማስጠበቅ መሆኑን ልናውቅ ይገባል። ዛሬ ላይ በተለያዩ አካባቢዎች ችግር እያለም እየተሠሩ ያሉ የልማት ሥራዎች የሉዓላዊነታችን ማስጠበቂያ አንድ መንገድ መሆናቸውን መገንዘብ ያስፈልጋል። በአዲስ አበባ በስፋት እየተሠራ ያለው የኮሪዶር ልማት ለዚህ አንዱ ማሳያ ነው። እኔ በአዲስ አበባ ከአርባ ዓመት በላይ ስቆይ ሁሉም መንግሥታት በየዘመናቸው የሠሯቸውን የተለያዩ የከተማ ልማት ሥራዎች አይቻለሁ ። በዚህ ፍጥነት በዚህ ያህል መጠነ ሰፊ ደረጃ ልማት ሲካሄድ ግን አይቼ አላውቅም ። ልማቱ የከተማዋን ነዋሪ አልያም ቀሪውን ኢትዮጵያዊ ብቻ ሳይሆን አፍሪካውያንና ሌሎችንም የሚያስደንቅ እንደሚሆን እገምታለሁ። ይህ ዐሻራ የዚህ ትውልድ አንድ ክፍል ነው ።

የኮሪዶር ልማቱ ሲሠራ የተፈናቀሉ እና ለተለያዩ ማህበራዊ ችግሮች የሚዳረጉ ዜጎች እንደሚኖሩ ግልጽ ነው። ይህም ቢሆን ግን የትም ሊከሰት የሚችልና ለሀገርና ለሕዝብ ሲባል የሚደረግ መስዋእትነት እንደሆነ ሊታሰብ ይገባል።

ከዚህ ጋር በተያያዘ ኢትዮጵያ አዲስ አበባ ብቻ አለመሆኗን በመገንዘብ ሌሎች ክልሎችም ተመሳሳይ ማህበረሰብን ተጠቃሚ የሚያደርጉ ሥራዎችን መሥራት ይጠበቅባቸዋል። ከላይ እንደጠቀስኩት የሀገር ሉዓላዊነት ከሀገር ልማት ጋር በቀጥታ ይገናኛል። ብዙ የልማት ሥራዎችን ስናከናውን ብዙ የሥራ እድል የመፈጠር አጋጣሚ ይኖራል። በዚህ ሂደት ተጠቃሚ የሚሆን ማህበረሰብ ደግሞ ሀገሩን የሚወድና የሚጠበቅ መሆኑ አይቀርም። ይሄ ማለት የሀገር ሉዓላዊነትን የሚነካ አጋጣሚ ሲፈጠር መከታ የሚሆን ሕዝብ እና ትውልድ አለ ማለት ነው።

**አዲስ ዘመን፡- ሉዓላዊነትን በማስጠበቅ ረገድ በውጭ ሀገራት ከሚኖሩ ኢትዮጵያውያን (ዳያስፖራ) ምን ይጠበቃል?**

**ሻምበል ዋኘው፡-** የኢትዮጵያ ሕዝብ ማለት በሀገር ውስጥ የሚኖረው ብቻ አይደለም። ኢትዮጵያዊ የሆነ ሁሉ ማለት ነው። በዚህ መሠረት በውጪው ዓለም ከሚኖሩ ኢትዮጵያውያን ብዙ ይጠበቃል። በአንድ በኩል ጠላቶቻችን የሀገር ሉዓላዊነትን ለማደፍረስ ብዙ ጊዜ እንደ መልእክተኛ የሚጠቀሙት በየሀገራቸው በስደት በትምህርትና በሌሎች ምክንያቶች ያሉ ኢትዮጵያውያንን ነው። አንዳንዶቹ ለውጭ ጠላቶች የመረጃ ምንጭ ሲሆኑ አይተናል። ከቅርብ ጊዜ ወዲህ በሀገር ውስጥ ያሉ ጉዳዮችን በአውሮፓና አሜሪካ ሆኖ መቃወም የተለመደ ተግባር እየሆነ መጥቷል።

በሀገር ውስጥ የተለየ ሃሳብንና የራስ የሆነ የፖለቲካ አመለካከትን ለማራመድ ምቹ ሁኔታ አለ እያልኩ አይደለም። ችግሮች እንዳሉ ይታወቃል። እነዚህ ችግሮች ደግሞ ዛሬ የተፈጠሩና አዲስ አይደሉም። ከንጉሡ ዘመን ጀምሮ በሀገር ውስጥ ያሉ ችግሮችን እንፈታለን ያሉ አካላት በአውሮፓና አሜሪካ ፓርቲ ሲመሠርቱ በስፋት ሲንቀሳቀሱም ነበር። በተመሳሳይ በደርግም በቀደመው የኢህአዴግ ዘመንም በመንግሥት ላይ የሚደረጉ ተቃውሞዎች ከሀገር ውስጥ ይልቅ በእነዚህ ሀገራት የበረቱ ናቸው። በግልጽም ማእቀብ በማስጣል የመንግሥትን ሃሳብ ለማስቀየር የሚሠሩት ሥራዎች ዛሬም ድረስ አሉ።

ምንም ይሁን ምን ግን የሀገር ሉዓላዊነትን ለአደጋ በሚያጋልጥ መልኩ የትኛውም ኢትዮጵያዊ ከባእድ ጋር ሊመክር አይገባም። የሀገር ሉዓላዊነት ለችግር በመጋለጡ የትኛውም ኢትዮጵያዊ ተጎጂ እንጂ ተጠቃሚ አይሆንም። አነሰም በዛ በታቃውሞ ጎራ የተሰለፉትም እንታገልለታለን የሚሉት ማህበረሰብ የገፈቱ ቀማሽ መሆኑ አይቀርም።

ስለዚህ የሀገር ሉዓላዊነት ጉዳይ ኢትዮጵያዊ የሆነን ሁሉ የሚመለከት ነው። ለምሳሌ የህዳሴው ግድብ ሲገነባ ከተፋሰሱ እና ከአንዳንድ የአውሮፓ ሀገራት ጋር በነበረው ግንኙነት የሀገር ሉዓላዊነትን የሚነኩ አጋጣሚዎች ተፈጥረው ነበር ። በወቅቱ በዚህ ጉዳይ የመንግሥትና የሕዝቡ አንድነት ጠንካራ ስለነበር ሁሉም ነገር አልፎ ግድቡ ዛሬ እዚህ ደረጃ ላይ ለመድረስ በቅቷል። በዛን ጊዜ ብዙ ተቃውሞ ሲቀርብበት የነበረው የኢህአዴግ መንግሥት ዛሬ በሥልጣን ላይ የለም፡፡ በአንጻሩ የኢትዮጵያ ሕዝብና የህዳሴው ግድብ ጥቅም ግን አሉ፤ ወደፊትም ይቀጥላሉ።



በአሁኑ ወቅትም ከባህር በር ጋር በተያያዘ በመንግሥት በኩል የተጀመረው ሥራ ተመሳሳይ ውጤት የሚኖረው ይሆናል። አንድነታችንን አጠናክረን የባህር በር ባለቤት ለመሆን ከበቃን መንግሥት ቢቀያየርም የኢትዮጵያ ሕዝብ በተለይም የመጪው ትውልድ ተጠቃሚነት የተረጋገጠ ይሆናል። በመሆኑም በውጭ ያሉ ኢትዮጵያውያን ምንም ያህል ችግር ገጥሟቸው ተቃውሞ ቢያሰሙም በሀገር ሉዓላዊነት ጉዳይ መደራደር የለባቸውም።

**አዲስ ዘመን፡- የኢትዮጵያን ሉዓላዊነት በማስጠበቅ ሂደት የውስጥ ችግሮች መሰናክል እንዳይሆኑ ምን ሲሠራ ይገባል ?**

**ሻምበል ዋኘው ፤** በመጀመሪያ ደረጃ የውስጥ አለመግባባቶች ለሀገር አንድነት መጠበቅ እና ለሉዓላዊነት እንቅፋት እንዳይሆኑ መፍትሄው ተቅራርቦ መነጋገር ብቻ ነው። በንግግር የማይፈታ ጉዳይ የለም። በውስጥ ችግራቸው እርስ በእርስም ሆነ ከሌሎች ሀገራት ጋር እሰጥ አገባ ገብተው ጦርነት የገጠሙ ሀገራት መጨረሻቸው የሚሆነው ድርድር እና ውይይት አድርጎ መስማማት ነው። እኛም ጋር ሊሆን የሚገባው ጥፋት ከመፈጸሙ በፊት ተቀራርቦ መነጋገር ነው።

በዚህ በኩል በታሪካችን ለመጀመሪያ ጊዜ ከተቋቋመው የምክክር ኮሚሽን ብዙ የሚጠበቅ ይሆናል። የምክክር ኮሚሽኑ በመላው ሀገሪቱ እየተንቀሳቀሰ እንደሆነ እናውቃለን። ለዚህ ውጤታማነት ሁላችንም ሃሳባችንን ልንሰጥ፤ የሌሎችንም ልንሰማ ይገባል።

የምክክር ኮሚሽኑን እየመሩ ያሉ አካላትም ተስፋ የሚጣልባቸው ናቸው። እኛ ባለን አቅም አብረናቸው ከሆንን በተለይም የተለያዩ አመለካከቶችን የሚያራምዱ አካላት ራሳቸውን ለድርድር ለውይይት ዝግጁ ካደረጉ ነገሮች ሁሉ በቀላሉ ሊፈቱ ይችላሉ። የኢትዮጵያ ሕዝቦች ከሚለያያቸውና ከሚያቃቅራቸው በላይ በህብረት በአንድነት ያሳለፉት ጊዜና የሠሩት ሥራ ትልቁን ድርሻ የሚይዝ ነው። የምክክር ኮሚሽኑ ውጤታማ መሆን ይህን አብሮነት አንድነትና መተሳሰብ ሊያስቀጥል የሚያስችል ነው። እኛ ኢትዮጵያውያን ልዩነቶቻችንን እየፈታን ህብረታችንን ማጠናከር ከቻልን የሀገራችንን ሉዓላዊነት ለማስጠበቅ ትልቁን ድርሻ ወሰድን ለማለት ይቻላል።

በሁለተኛ ደረጃ ወጣቱ ትውልድ ለሰላም ያለው ምልከታ የተስተካከለ ሊሆን የገባል። ሰላም የሁሉም ነገር መሠረት ነው። ሰላም ከሌለ ምንም ጥሩ ነገር ሊኖር አይችልም። የሀገር ሉዓላዊነት ብቻ ሳይሆን የእያንዳንዱ ግለሰብ የእያንዳደንዱ ቤተሰብ ደህንነት አደጋ ለይ መውደቁ አይቀርም። ይህ እንዲሆን የሚፈልግ ደግሞ ይኖራል ብዬ አላስብም። በወጣቶች በኩል የተለያዩ ጥያቄዎችና ፍላጎቶች ሊኖሩ ይችላሉ። የሚታገሉለት ማህበረሰብም ሊኖር ይችላል። ሁሉንም ነገር ግን በሰላም ጥላ ስር ሆነው ማካሄድ እንዳለባቸው ሊገነዘቡ ይገባል። ብዙ ጊዜ የሰላም መደፍረስ ለችግርና ለስቃይ የሚዳርገው መብቱን እናስከብርለታለን ፤ ፍላጎቱን እናሳካለታለን፤ ጥያቄውን እንመልስለታለን ብለው የተነሱለትን ሕዝብ ነው።

ይህንን እውነታ የፖለቲካ ልሂቃን ነን፤ የተወሰነን ማህበረሰብ እንወክላለን የሚሉ ግለሰቦችና ቡድኖች ሊገነዘቡትና ትኩረት ሊሰጡት ይገባል። በመሠረቱ እንደ ሀገር ሁለንተናዊ ሉዓላዊነት ሳይከበር በተናጥል መብትና ጥቅሙን ሊያስከብር የሚችል ማህበረሰብ በኢትዮጵያ ጥላ ስር ሊኖር አይችልም። በመሆኑም በአንድ ሀገር ጥላ ስር እስካለን ድረስ ጥያቄዎች ሁሉ መቅረብ ያለባቸው በሰላማዊ መንገድ በንግግር ብቻ መሆን አለበት። ኢትዮጵያ ጠንካራ ሀገር መሆኗን የሚያውቁ ፤ ነገር ግን በጠላትነት የፈረጇት ሀገራት ባይሳካላቸውም ሉዓላዊነቷን ለመፈታተን የሚሞክሩት የውስጥ ልዩነቶችን በማጋነንና በማጋጋል ነው። በመሆኑም በዚህ ረገድ የመላው ዜጋ በተለይም የወጣቶች ምላሽ ሊሆን የሚገባው ከሀገር ሰላምና የሀገርን ሉዓላዊነት በማስጠበቅ ረገድ ልዩነት እንደማይኖር አሳይቶ አሳፍሮ መመለስ ነው።

**አዲስ ዘመን፡- በቀጣይ የኢትዮጵያ ሉዓላዊነት መከበር መጠበቅ የትውልዱ ድርሻ ምን ሊሆን ይገባል ?**

**ሻምበል ዋኘው ፤** በአንድ በኩል አሁን ያለው ወጣት ትውልድ የራሱ ግል ሕይወት ብቻ ሳይሆን የነገዋ ኢትዮጵያ እጣ ፈንታ በእጁ መሆኑን መረዳት አለበት። ምንም ይሁን ምን የሉዓላዊነት ጉዳይ ለድርድር የሚቀርብ ሊሆን አይገባም። በኢትዮጵያ ሕዝቦች መካከል የተለያዩ ልዩነቶች እንዳሉን ይታወቃል። ልዩነቶች ድሮም አባቶቻችን ዳር ድንበር አስከብረው ኖረዋል በምንልበት ዘመንም ነበሩ። ነግር ግን እነሱ ልዩነታቸውን ጉዳታቸውንም ሆነ ጥያቄያቸውን ከኢትዮጵያ ሉዓላዊነት አስቀድመው አያውቁም። የዘመነ መሳፍንት የእርስ በእርስ ግጭት ለዚህ ጥሩ ማሳያ ነው። ይህም በመሆኑ አባቶቻችን ዛሬ ድረስ የተሻገረ ሀገርም ታሪክም ለማስቀጠል በቅተዋል። የአሁኑ ትውልድም ምንም የውስጥ ልዩነት ቢኖር ዛሬ እሱ ስለሚኖርባት ብቻ ሳይሆን ለቀጣዩም ትውልድ ኢትዮጵያ የምትባለውን ሀገር ከነሙሉ ክብሯና ሉዓላዊነቷ የማስተላለፍ ሃላፊነት እንዳለበት ሊገነዘብ ይገባል።

በዚህ ረገድ ስለውጪ ጣልቃ ገብነት መታወቅ ያለበት ኢትዮጵያን በጠላትና በስጋትነት ያስቀመጡ ሀገራት አጋጣሚውን ባገኙ ቁጥር መሞከራቸው እንደማይቀር ነው። ውጤታቸው የሚወሰነው ግን በእኛ አንድነትና በምንሰጠው የህብረት ምላሽ ብቻ ይሆናል። በመንግሥትም በኩልም ቢሆን የውስጥ ችግሮችን በሰላማዊ መንገድ ለመፍታት የሚጠበቅበትን ሁሉ ማድረግ አለበት። በተጨማሪ ሥራ የማይሠራ ወጣት ሊኖር አይገባም። የቻለ ራሱ ሥራ እየፈጠረ መሥራት ያልሆነለት ደግሞ በመንግሥትና በሌሎች አካላት የሚፈጠሩ የሥራ እድሎችን እየተጠቀመ ራሱንና ሀገሩንም ሊያሸጋግር ይገባል።

ከዚሁ ጋር በተያያዘ አሁን ስላለው ትውልደ ስናወራ ትውልዱን መቅረጽ ስላለበት ያለፈው ትውልድ ማንሳታችን የግድ ይሆናል። ሀገር የምትጠበቀውም የምትጸናውም በትውልድ ቅብብሎሽ ነው። በዚህ ሂደት ለሀገሩና ለወገኑ የሚያስብ ሀገር ተረካቢ ወጣት እንዲፈጠር ሁሉም የበኩሉን ድርሻ መወጣት ይኖርበታል። ቤተሰብና ማህበረሰብ በየደረጃቸው ከሚኖራቸው ድርሻ በዘለለ የትምህርት ተቋማት ሃላፊነት አለባቸው።

ድሮ የነበረው የትምህርት ሥርዓት ሁሉንም ጥያቄ ከሀገር የሚያስቀድም አልነበረም፡፡ አሁንም ቢሆን ማንኛውም ጥያቄ ከሀገር ሊቀድም አይገባም። ትውልዱ ይህንን ሃሳብ እንዲያውቀውና አምኖ እንዲቀበለው የማድረግ ሥራ ከትምህርት ተቋማትና ከመምህራን ይጠበቃል። ይህንን የሚያደርጉት ደግሞ ተማሪዎችን ስለልዩነታቸው ሳይሆን ስለአንድነታቸውና ስለህብረታቸው፤ ስለመከባበርና መዋደዳቸው ደጋግሞ በማስተማር ነው።

**አዲስ ዘመን፡- ስነበረን ቆይታ እናመሰግናለን።**

**ሻምበል ዋኘው፡-** አመሰግናለሁ ።

**ኢ**ትዮጵያ የጠየቀችው የባሕር በር ጥያቄ የማንንም ሉዓላዊ ሀገር በጉልበት ለመጠቅለል የሚደረግ ሙከራ አይደለም። በዚህ ረገድ አሁን ጣልቃ እየገቡ ያሉት ሀገራት የሚሠሩት ሥራ ግን የኢትዮጵያን ተጠቃሚነት ብቻ ሳይሆን ሉዓላዊነትም የሚገዳደር ነው

# ባህልና ቱሪዝም

## አንድ ዓመት ወደ ኋላ - የቱሪዝም ዘርፍ ስኬቶች

ዳግም ከበደ

ጳጉሜን ሶስት ላይ እንገኛለን። የ2016 ዓ.ም መገባደጃ የአዲስ ዓመት መግቢያ ደጃፍ ላይ ነን። እንደሚታወቀው የ2016 ዓ.ም የመጨረሻው እሁድ ነው። በመሆኑም የዝግጅት ክፍላችን በተጠናቀቀው ዓመት በቱሪዝም ዘርፍ ላይ የተመዘገቡ ውጤታማ ሥራዎች ላይ ትኩረቱን አድርጎ ዓመታዊ ዳሰሳ ለማድረግ ወደደ። መረጃውንም የቱሪዝም ሚኒስቴር የስትራቴጂክ ክፍል ቡድን መሪ የሆኑት አቶ ቴዎድሮስ ደርበው አድርሰውናል።

የኢትዮጵያ መንግሥት ‹‹የሀገሪቱ ኢኮኖሚ የጀርባ አጥንት ናቸው›› በማለት ከለያቸው አምስት ዘርፎች መካከል ቱሪዝምን አንዱ አድርጎታል። በዘርፉም መዋቅራዊ ለውጥ ከማድረግ ጀምሮ በርካታ ማሻሻያዎችን አድርጓል። ይህ ውሳኔ የቱሪዝም ዘርፍን ነፃነት ያወጀና በቀጣይ ለሚካሄዱ የልማት፣ ማስተዋወቅና እንዲሁም የጎብኚዎችን ቁጥር የማሳደግ አቅምን እንደሚጨምር ይጠበቃል።

በአዲስ መልክ ከባህል ዘርፍ ተነጥሎ ለብቻው በሚኒስቴር መሥሪያ ቤት ደረጃ የተዋቀረው ቱሪዝም ሚኒስቴርም ይህንን ሃላፊነት በበላይነት እንዲመራ ይጠበቃል። ተቋሙ እራሱን ከማደራጀት አንስቶ በመዳረሻ ልማት፣ በገበያና ማስታወቂያ፣ በቱሪዝም ዲፕሎማሲ፣ በመረጃ ጥራት እንዲሁም በመሰል የዘርፉ ተግባርና ሃላፊነቶች ላይ ሥራዎችን ሲያከናውን እንደነበር የስትራቴጂክ ክፍሉ የቡድን መሪ የሆኑት አቶ ቴዎድሮስ ደርበው ይናገራሉ። በ2016 ዓ.ም እነዚህን ተግባራት የሚያጎሉ ውጤታማ አፈፃፀሞች መመዝገባቸውን ይገልፃሉ።

ኢትዮጵያ ሉዓላዊ ሀገር ነች። በውስጧ በርካታ ብሄር ብሄረሰቦችን አቅፋ የያዘች የተፈጥሮ፣ የባህል፣ የታሪክና የሰው ልጅ መነሻ የሆኑ የመስህብ ሀብቶች ያላት ሀገር ነች። ይህንን እሴት ለዓለም በማስተዋወቅ ጎብኚዎችን የመሳብ ሥራዎችን መሥራት ያስፈልጋል። በተለይ የቱሪዝም ዲፕሎማሲን ተግባራዊ በማድረግ ከሀገራትና ከሕዝብ ለሕዝብ ጋር ግንኙነት ለማጠናከር ያስችላል። ከዚህ አንፃር ውጤት መመዝገቡን የስትራቴጂክ ቡድን መሪው ይገልፃሉ።

### ቱሪዝም ዲፕሎማሲ

በዋናነትም የቱሪዝም ሚኒስቴር በተጠናቀቀው የ2016 ዓ.ም በቱሪዝም ዲፕሎማሲው በርካታ ተግባራት መፈፀሙን ይናገራሉ። የቱሪዝም ትስስሮችን ከሀገራት፣ ቀጣናዊ እና ዓለም አቀፋዊ ሁነቶች ጋር እንዲሁም ዲፕሎማሲያዊ ግንኙነቶችን በማጠናከር የቱሪስት ፍሰትን ከማሳደግ እና ገፅታን ከመገንባት አኳያ መልካም ውጤቶች መመዝገባቸውን ያስረዳሉ።

እንደ ስትራቴጂክ ቡድን መሪው ገለፃ በ2016 ዓ.ም ከኬንያ፣ ሩዋንዳ፣ ደቡብ አፍሪካ፣ ኳታር፣ ሳውዲ አረቢያ፣ ቻይና፣ ጣሊያን፣ ቱርክ፣ ጆርዳንና ሌሎች ሀገራት ጋር የቱሪዝም ትብብሮችን ለማጠናከር የሚያስችሉ ሥራዎች ተከናውነዋል። ከእነዚህ ሀገራት ጋር በቱሪዝም ማስተዋወቅና ግብይት፣ በአቅም ግንባታ፣ በልምድ ልውውጥ እና በቱሪዝም ኢንቨስትመንት ፍሰት ዙሪያ በትብብር ለመሥራት የሚያስችሉ ስምምነቶች ተደርገዋል።

ኢትዮጵያ የብሪክስ (BRICS) ሀገራት ስብስብ አዲስ አባል መሆኗን ተከትሎ በሰኔ ወር በሩሲያ ሞስኮው በተካሄደው ዓመታዊ የቱሪዝም ፎረም መርሃ ግብር ተሳትፎ ተደርጓል የሚሉት አቶ ቴዎድሮስ ደርበው፤ በሚኒስትሮች ስብሰባ እና በቱሪዝም የከፍተኛ የሥራ ሃላፊዎች ቡድን (Tourism Working Group) ስብሰባ እንዲሁም በንግድ ለንግድ ትስስር መድረኮች አመርቂ ተሳትፎ መከናወኑን ይገልፃሉ። በነባር የቱሪስት አመንጭ ሀገራት የገበያ ድርሻን ለማጠናከር እንዲሁም አዳዲስ የቱሪዝም ገበያዎችን ለማስፋፋት የሚያስችሉ ውጤታማ የግብይትና የማስተዋወቅ ስልት በቱሪዝም አውደ ርዕይ ላይ በመገኘት ተግባራዊ መደረጉን ይገልፃሉ። በዚህም ጠንካራና የተቀናጀ የገፅታ ግንባታ ሥራዎች መከናወናቸውን ይናገራሉ።

እንደ አቶ ቴዎድሮስ ደርበው ገለፃ፤ ከቱሪዝም ዲፕሎማሲው ባሻገር በ2016 ዓ.ም ከተከናወኑ ተግባራት መካከል የቱሪዝም መረጃ አስተዳደርን ማሻሻልን የሚመለከተው በቀዳሚነት ይገኝበታል። በዚህም የቱሪዝም ስታቲስቲክስ ሥርዓትን እና መረጃ አስተዳደርና አሠራርን ለማሻሻል በማሰብ ሁለት ጊዜ የቱሪዝም የዳሰሳ ጥናት (Survey) መከናወኑን ያስረዳሉ። ይህ ተግባር ዘርፉ በመረጃ እንዲደገፍ እና ለሀገራዊ ኢኮኖሚ የሚያበረክተው አስተዋጽኦ እንዲያድግ ያደርጋል ይላሉ።

የዘርፉ ምሁራን እና ባለሙያዎች በተደጋጋሚ እንደሚያነሱት በልዩ ልዩ የዘርፉ ተቋማት የሚወጡት መረጃዎች ተዓማኒነትና ተመሳስሎ የሚጎድለው ነው። ይህንን ተከትሎም ተደጋጋሚ ትችቶች በእነዚሁ አካላት ሲሰነዘር ይሰማል። የቱሪዝም ሚኒስቴር የስትራቴጂክ ቡድን መሪው አቶ ቴዎድሮስ ደርበው ጉዳዩን አስመልክቶ በተጠናቀቀው በጀት ዓመት የቱሪዝም መረጃ ጥራትን ከማሻሻል አኳያ ዓለም አቀፍ ጎብኚዎች ሰርቬይ (International Visitors' Exit Survey) ከጃይካ (JICA) ጋር በተደረገ የሥራ ግንኙነት ተከናውኗል። በዋናነትም በቦሌ ዓለም አቀፍ ኤርፖርት መረጃዎችን ከውጭ ጎብኚዎች የማሰባሰብ ሥራ መጠናቀቁን ያስረዳሉ። መረጃዎችን የማደራጀትና የመተንተን ሥራ መካሄዱንም ይገልፃሉ።

### አጋርነትና ትብብር

የቱሪዝም ሚኒስቴር ተግባርና ሃላፊነቶች ከሆኑት መካከል ትብብርና አጋርነት አንዱ ነው። ከዚህ አኳያ ሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ ከቱሪዝም ተዋናዮች ጋር አጋርነትና ትብብርን በመፍጠር የሕዝብ ግንኙነት አሠራርንና ውጤታማነት ለማሻሻል የተለያዩ ሃላፊነቶችን እንደተወጣ አቶ ቴዎድሮስ ይናገራሉ። ከዚህ መነሻ በመንግሥትና በግል ዘርፉ እንዲሁም አጠቃላይ በቱሪዝም ተዋንያን መካከል አምዳዊና የጎንዮሽ ትስስሮችን ለማጠናከር በማሰብ ከቱሪዝም እና ሆቴል ባለድርሻ አካላት (ከአስጎብኚ ድርጅቶች፣ ከሆቴሎች ማህበራት፣ ከሆቴል ባለቤቶች፣ ከአስጎብኚ ባለሙያዎች፣ ከሆኑት አስተባባሪዎች) ጋር ሰባት የምክክር መድረኮች መከናወናቸውን ይገልፃሉ። በዚህም ጥራት ያለው የቱሪዝም አገልግሎት እና የቱሪስቶችን ደህንነት ለማረጋገጥ ያሉትን ዘርፈ ብዙ ጥረቶች ለማስተባበር በቱሪዝም ዙሪያ የተፈጠረ የጋራ ስምምነት መሆኑን ያስረዳሉ።

### ቅርስ ጥገና የተፈጥሮ ጥበቃ

ኢትዮጵያ የተፈጥሮ፣ የታሪክ፣ የባህል፣ የቅርስ፣ የአርኪዮሎጂና መሰል ሌሎች በርካታ የመስህብ ሀብቶች ባለቤት ነች። በተለይ ጥንታዊ ቅርሶች በስፋት ከሚገኙባቸው ሀገራት ተርታ ትመደባለች። በሰው ልጅ የኪነ ህንፃ ታሪክ ወደር የማይገኝላቸው ሀብቶችን ይዛለች። ከእነዚህ የኪነ ህንፃ ቅርሶች መካከል አብዛኞዎቹ በርካታ ዘመናትን (ምእተ ዓመታትን) የተሻገሩ ናቸው። ከቅርሶቹ ባሻገርም እንክብካቤና ጥበቃ የሚሹ የተፈጥሮ ፓርኮች፣ መልከዓ ምድሮችና የዱር እንስሳት መኖሪያ አካባቢዎች በስፋት ይገኛሉ።

በጊዜ ቆይታቸው የተነሳ ከፍተኛ ጥንቃቄ የተሞላበት ጥገና የሚሹ በርካታ ቅርሶች በኢትዮጵያ ውስጥ ይገኛሉ። ከእነዚህ የኪነ ህንፃ ሀብቶች መካከል የላሊበላ፣ የጅማ አባጅፋ በቀዳሚነት ይጠቀሳሉ። እንደ አቶ ቴዎድሮስ ደርበው ገለፃ እነዚህን ቅርሶች ለመጠበቅ እና ለመንከባከብ በተጠናቀቀው 2016 ዓ.ም ውጤታማ ሥራ ተሠርቷል። ከተግባሮቹ መካከልም ከፈረንሳይ መንግሥት ዘላቂ ላሊበላ ፕሮጀክት እና ቅርስ ባለሥልጣን ጋር በመተባበር በላሊበላ ከተማ ደረጃውን የጠበቀ የባህል/ቱሪዝም ማዕከል ግንባታ በመጠናቀቅ ላይ ነው። በላሊበላ ውቅር አብያተ ክርስቲያናት ሶስቱንም ግሩፕ የጉብኝት ማዕከሎች እርስ በእርስ የሚገናኙ ለጎብኚዎች ምቹ የሆኑ የውስጥ ለውስጥ መንገዶች እና ድልድዮች ከፈረንሳይ መንግሥት ዘላቂ ላሊበላ ፕሮጀክት እና ቅርስ ባለሥልጣን ጋር በመተባበር ተሠርቶ አገልግሎት መስጠት ጀምሯል።

ሌላው የጥገናና ልማት ሥራ የተተገበረው በጅማ አባ ጅፋር መሆኑን አቶ ቴዎድሮስ ይናገራሉ። በዚህም የጅማ አባጅፋር ቤተ መንግሥት ካለው ታሪካዊ ፋይዳ፣ ልዩ የቤተ መንግሥት ኪነ ህንፃ ግንባታና በቤተ መንግሥቱ አቅራቢያ ያሉ ቱሪስቶችን መሳብ የሚችሉ በርካታ መስህቦች ምክንያት ቅጥር ጊቢው እንዲለማና አካባቢው የቱሪዝም መዳረሻ እንዲሆን ሥራዎች እየተከናወኑ መሆኑን ይናገራሉ። ከላሊበላና ከጅማ አባ ጅፋር ቤተመንግሥት እድሳትና የልማት ሥራዎች ባሻገር

**ኢትዮጵያ ሉዓላዊ ሀገር ነች። በውስጧ በርካታ ብሄር ብሄረሰቦችን አቅፋ የያዘች የተፈጥሮ፣ የባህል፣ የታሪክና የሰው ልጅ መነሻ የሆኑ የመስህብ ሀብቶች ያላት ሀገር ነች። ይህንን እሴት ለዓለም በማስተዋወቅ ጎብኚዎችን የመሳብ ሥራዎችን መሥራት ያስፈልጋል**

በኮንሶ የዩኔስኮ አደባባይ ግንባታ ሥራዎች በሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ፣ በተጠሪ ተቋማት፣ በክልሎችና በልማት ትብብር ድርጅቶች መሠራቱን ተናግረዋል።

ሌላው በበጀት ዓመቱ (በ2016 ዓ/ም) ከተተገበሩ ሥራዎች መካከል የተፈጥሮ ጥበቃ እንደሚገኝበት አቶ ቴዎድሮስ ደርበው ይናገራሉ። በዚህም በተፈጥሮ ሀብትን ጥበቃ በኩል የስንቅሌ የቆርኬዎች መጠለያ ከተለያዩ ተቋማት ጋር በመተባበር የእንግዶች ማረፊያ የሚሆን የማህበረሰብ አቀፍ ሎጅ (Community Lodge)፣ መታጠቢያ ቤቶች፣ የካምፒንግ ግራውንድና የስጦታ ዕቃዎች መሸጫ ማዕከል ግንባታ መጠናቀቁን ያስረዳሉ። ከስንቅሌ ባሻገር በአፋር ክልል በኤርታኢሌ የእሳተ-ገሞራ ድንቅ የተፈጥሮ ትዕይንት መመልከቻ ቦታ ላይ ለጎብኚዎች መወጣጫ የሚሆን ደረጃዎች ግንባታ በመከናወን ላይ መሆኑን ይናገራሉ።

### ቱሪዝም ኢንቨስትመንት

አቶ ቴዎድሮስ ደርበው ሚኒስቴር መሥሪያቤቱ በ2016 ስኬታማ አፈፃፀም ካሳየባቸው ተግባራት መካከል የቱሪዝም ኢንቨስትመንት መሆኑን ባደረሱን መረጃ ያመለክታል። በዋናነትም በዘርፉ ምቹ የቱሪዝም ኢንቨስትመንት አሠራሮችን በማጠናከር፣ ውጤታማ የማበረታቻ አሰጣጥ ሥርዓት በመዘርጋት እና የኢንቨስትመንት መረጃዎችን በጥራት ተደራሽ በማድረግ የውጭ እና የሀገር ውስጥ ባለሀብቶችን ቁጥር ማሳደግ ብሎም የግል ዘርፉን ሚና የበለጠ የማጎልበት ሥራ መሠራቱን ይናገራሉ።

የኢንቨስትመንት እድሎችን ለማስተዋወቅና ተግዳሮቶችን ለመቅረፍ ፎረም ተካሂዷል ያሉት የስትራቴጂክ ቡድን መሪው፤ የሀገር ውስጥ ባለሀብቶች ወደ ዘርፉ እንዲሠማሩ ለማድረግ ታቅዶ በተለያዩ የቱሪዝም ኢንቨስትመንት ዘርፎች 132 ባለሀብቶች ሴክተሩን መቀላቀላቸውን ይገልፃሉ። እንዲሁም 16 ባለሀብቶች በሆቴልና መሰል አገልግሎት ንግድ ዘርፎች ኢንዱስትሪውን እንደተቀላቀሉ ይናገራሉ። የኢንቨስትመንት ፈቃድ የወሰዱ (የተመዘገቡ) 148 የውጭና የሀገር ውስጥ ባለሀብቶች በፌዴራል ኢንቨስትመንት ኮሚሽን እና በክልል ኢንቨስትመንት መሥሪያ ቤቶች እንዳሉ ይናገራሉ። ለባለሀብቶች አስፈላጊው የኢንቨስትመንት ድጋፍና ትብብር እንደተደረጋላቸውም ይገልፃሉ።

### ቁጥሮች ምን ይላሉ?

አቶ ቴዎድሮስ ደርበው እንደሚገልፁት በቱሪዝም ዘርፍ ቀጥተኛ የሆነ 117 ሺህ 579 የሥራ እድሎች ተፈጥሯል። ከዚህ መካከል 47 ሺህ 32 ቋሚ የሥራ እድሎች ሲሆኑ 70 ሺህ 547 ደግሞ ግዜያዊ መሆናቸውን ይገልፃሉ። በ2016 ዓ.ም አንድ ሚሊዮን 148 ሺህ 50 የውጭ ጎብኚዎች ኢትዮጵያን መጎብኘታቸውን ተናግረው ከዘርፉ የሚገኘውን የውጭ ምንዛሬ ገቢም አራት ነጥብ ሶስት ቢሊዮን የአሜሪካ ዶላር መድረሱን ያነሳሉ። የሀገር ውስጥ ጎብኚ 40 ነጥብ ሰባት ሚሊዩን ጎብኚዎች እንዲንቀሳቀሱ ተደርጓል። በሀገር ውስጥ ቱሪዝም ገቢም 65 ነጥብ 12 ቢሊዮን ብር መገኘቱን ተናግረዋል።

በ2016 ዓ.ም ሀገርን የማስተዋወቂያ መድረኮች (Trade fairs, Expos & Road Shows) ላይ በእንግሊዝ፣ በጀርመን፣ በፈረንሳይ፣ በቤልጅየም፤ በፓኪስታንና በቻይና በተካሄዱ ስድስት የንግድ ትርዒቶች ላይ ውጤታማ ተሳትፎ ለማድረግ መቻሉን ያስረዱት አቶ ቴዎድሮስ ደርበው፤ በበጀት ዓመቱ ውስጥ 28 ዓለምአቀፍ ኹነቶች በኢትዮጵያ መካሄዳቸውን አንስተዋል።

በተጨማሪ ሀገር አቀፍ የቱሪዝም ሀብቶች ልዩታ (National Tourism Resource Mapping) በማካሄድ ኢትዮጵያ ያላትን እምቅ የቱሪዝም ሀብቶች ዓይነት፣ መጠንና ስብጥር በጥልቀት በመለየት በተቀናጀ መንገድ (Clustering) ለማልማት የሚያስችሉ የመዳረሻ ልማት ፕሮግራሞችንና ፕሮጀክቶችን ቀርፆ ተግባራዊ መደረጉንም አስረድተዋል።

ለዘላቂ ቱሪዝም ልማት መረጋገጥ ወሳኝና ደጋፊ መሠረተ ልማቶች እንዲሟሉ በማድረግ የቱሪዝም መዳረሻዎችን በማስፋፋትና ተወዳዳሪነታቸውን በማሳደግ ኢትዮጵያ ተመራጭ የጎብኚዎች መዳረሻ እንድትሆን ለማስቻል እየተሠራ መሆኑን የሚያነሱት አቶ ቴዎድሮስ በዚህም ዘጠኝ የቱሪስት መደራሻዎች የመሠረተ ልማት ማሻሻያዎች እንደተደረገላቸው ለዝግጅት ክፍላችን ገልፀውልናል።

በመጨረሻም አቶ ቴዎድሮስ በሰጡን መረጃ እንዳመለከቱት፤ ከቪዛ አሰጣጥ ጀምሮ ጎብኚዎች ኢትዮጵያ ገብተው እና ጎብኝተው እስኪመለሱ ድረስ ባለው የቱሪዝም እሴት ሰንሰለት ውስጥ የሚሰጡ አገልግሎቶችን ጥራት ለማሻሻል፣ አሠራሮችን ማዘመንና የአገልግሎት ልህቀትን ለማረጋገጥ የሚያስችሉ የሆቴሎች የጥራትና ደረጃ አሰጣጥ መስፈርቶች ፀድቀው ሥራ ላይ በመዋላቸው የደረጃ አሰጣጥ ሥራ ተጀምሯል። በዚህም ስልሳ አራት (64) የቱሪስት አገልግሎት ሰጪ ተቋማት በደረጃ ተመድበዋል። ለ356 አገልግሎት ሰጪ ድርጅቶች ብቃታቸው ተረጋግጦ እውቅና ተሰጥቷል።

# ሳምንቱን በታሪክ

# በባዶ እግር የተጻፈው የወርቅ ታሪክ

**ዋለልኝ አየለ**

አንድ ለስፖርት ቅርብ ያልሆነ ሰው «አበበ ቢቂላ ምንድነው?» ተብሎ ቢጠየቅ «ሯጭ» ማለቱ ግልጽ ነው። እንዲያውም አንድ ማሳያ እንጥቀስ። እሸቱ መለሰ የሚባለው የ«ዩትዩብ» ፕሮግራሞች አዘጋጅ በአንድ ፕሮግራሙ የገጠር አርሶ አደሮችን ወግ እያሳየ ነበር። በመጨረሻም የታዋቂ ሰዎችን ፎቶ እያሳየ «ይሄ ማነው?» እያለ ይጠይቃል። አንድ አርሶ አደር የአትሌት ኃይሌ ገብረሥላሴን ፎቶ (በሩጫ ድርጊት ላይ እያለ) ሲያሳያቸው ቶሎ ብለው «አበበ ቢቂላ» አሉ። አበበ ቢቂላ እዚህ ድረስ በሰዎች አዕምሮ ውስጥ ተሠርቷል ማለት ነው።

አበበ ቢቂላ ኢትዮጵያ በዓለም ታሪክ ከታወቀችባቸው እንደ ዓድዋ ያሉ ድሎች አንዱ ነው ማለት ይቻላል፤ ምክንያቱም በዓለም አደባባይ ኢትዮጵያ ስሟ የሚጠራበት ታሪክ ያስመዘገበ ጀግናዋ ነው። ይህን ጀግና በዚህ ሳምንት እናስታውሳለን። ከዚያ በፊት ግን እንደተለመደው ሌሎች የሳምንቱ ክስተቶችን እናስታውስ።

ከ52 ዓመታት በፊት በዚህ ሳምንት ጳጉሜ 1 ቀን 1964 ዓ.ም (በአውሮፓውያኑ 1972) በሙኒክ ኦሊምፒክ ለመሳተፍ ወደ ምዕራብ ጀርመን የሄዱት 9 የእስራኤል አትሌቶች በፍልስጤሙ «ጥቁር መስከረም» (Black September) ድርጅት ተገደሉ።

ከዛሬ 556 ዓመታት በፊት በዚህ ሳምንት ልክ በዛሬዋ ቀን ጳጉሜ 3 ቀን 1460 ዓ.ም የኢትዮጵያ ንጉሠ የነበሩት አፄ ዘርዓያዕቆብ አረፉ። የሰለሞናዊ ሥርዎ መንግሥት አካል የሆኑት እኚህ ንጉሥ ባለቤታቸው ንግሥት እሌኒም በኢትዮጵያ ታሪክ ውስጥ ጎልተው ይታወቃሉ።

በዚሁ ሳምንት ከ105 ዓመታት በፊት ጳጉሜ 3 ቀን 1911 ዓ.ም ደግሞ የወሎ ንጉሥ የነበሩት ንጉሥ ሚካኤል አረፉ።

ወደ አበበ ቢቂላ ታሪክ ስንሄድ በዚህ ሳምንት ሁለት ታሪኮች አሉት። አንደኛው በግልጽ በዓለም ሰነድ ላይ የሰፈረው የሮም ኦሎምፒክ ታሪኩ ሲሆን ሁለተኛው ግን የተወለደበት ቀን ነው።

በብዙ የበይነ መረብ መረጃዎች አበበ ቢቂላ የተወለደው በአውሮፓውያኑ የዘመን ቀመር ነሐሴ (August) 7 ቀን 1932 (በኢትዮጵያ አቆጣጠር ነሐሴ 1) ተደርጎ ነው የተጻፈው። አንዳንድ የሀገር ውስጥ ሰነዶች ደግሞ ነሐሴ 30 ቀን 1925 ዓ.ም እንደተወለደ ነው የሚገልጹት። ለዚህ እንደ ማስረጃ የሚጠቀሰው በአንድ የቪዲዮ ምስል ላይ እናቱ ሲናገሩ «የነሐሴ ዓመት ሰላሳ ዕለት ነው የተወለደ» ይላሉ። በልማዳዊ አጠራር ዓመት ሰላሳ ማለት የወሩ የመጨረሻ ቀን (30) ማለት ነው። በዘመኑ የልደት ምስክር ወረቀት ስለሌለ የተራ ሰዎች (አበበ በልጅነቱ ተራ ሰው መሆኑን ልብ ይሏል) ታሪክ የሚሰነድበት ዕድል አልነበረም። ለማንኛውም ይህን በአከራካሪነቱ ክፍት አድርገን እንተወውና በዓለም ሰነድ ላይ የተመዘገበውን ወርቃማ ታሪኩን እናስታውስ።

በአበበ ቢቂላ ሀገር የዘመን አቆጣጠር ጳጉሜ 5 ቀን 1952 ዓ.ም ((በአውሮፓውያኑ 1960) ሻምበል አበበ ቢቂላ በሮም ኦሊምፒክ የማራቶን ሩጫን በባዶ እግሩ ሮጦ በማሸነፍ የወርቅ ታሪክ አስመዘገበ። ይህ የአበበ ታሪክ የኢትዮጵያ ብቻ ሳይሆን የአፍሪካ ታሪክ ነበር፣ የአፍሪካ ብቻም ሳይሆን የዓለም ታሪክ ነበር። አዲስ ክብረ ወሰን ያስመዘገበበት ነበር። ከዚህ ደማቅ ታሪኩ ጋር በባዶ እግሩ መሆኑ ደግሞ ሌላኛው የታሪኩ አካል ነበር።

ቀደም ባሉት ዓመታት ጥቁሮች በስፖርታዊ መድረኮች ለመሳተፍ ከነጮቹ እኩል ዕድል የማግኘታቸው ነገር ቀላል አልነበረም። የ1952 ዓ.ም የሮም ኦሊምፒክ ሲከናወን በርካታ የአፍሪካ ሀገራት ገና በቅኝ ግዛት ቀንበር ስር ነበሩ። አንድ ጥቁር በውድድሩ ተሳትፎ አሸንፎ የወርቅ ሜዳሊያ ሲያጠልቅ፣ ለዚያውም የዓለም ክብረ ወሰንን ሰብሮ ሲሆን ልዩ ክስተት ነበረው።

አበበ ቀደም ሲል በጠቀስናቸው ቀናት (ነሐሴ 1 ወይም 30) ቀን 1925 ዓ.ም በቀድሞው የሸዋ ጠቅላይ ግዛት በደብረ ብርሃን አውራጃ፣ ደነባ አካባቢ፣ ልዩ ስሟ ጃቶ በምትባል ሥፍራ ተወለደ። ወጣቱ አበበ እንደአካባቢው ባህልና ልማድ በእረኝነትና በትምሕርት ተሰማርቶ በአሥራ ሁለት ዓመቱ የቄስ ትምህርቱን አጠናቀቀ።

አበበ ገና በጨቅላ ዕድሜው ስመ ጥር የገና ተጫዋች እንደነበር ይነገርለታል። በ1944 ዓ.ም ወደ አዲስ አበባ በመሄድ በክብር ዘበኛ ሠራዊት በወታደርነት ተቀጥሮ በገና ጨዋታ እና በስፖርት እየዳበረ ቆየ። ክቡር ዘበኛ ሠራዊት ውስጥ ሲገባም፤ ከስፖርት ጋር ይበልጥ ተቀራረበ እንጂ አልተራራቀም። ከውትድርና አገልግሎት ጎን ለጎን፤ በሠራዊቱ የስፖርት እንቅስቃሴ በተለይም በአትሌቲክስና በገና ጨዋታ ጎልቶ ለመታየት ጊዜ አልፈጀበትም።

በኅዳር ወር 1948 ዓ.ም በአሥራ ስድስተኛው የሜልቦርን ኦሊምፒክ ላይ የተሳተፈውን የኢትዮጵያን ቡድን ለመቀበል በተደረገው ሰልፍ ላይ ከለበሱት ልብስ ጀርባ በኩል የሀገራቸው ስም (‹ኢትዮጵያ›) የተጻፈበትን መለያ ልብሳቸውን ለብሰው ሀገራቸውን ወክለው የተወዳደሩትን ወጣቶች ባየ ጊዜ ከፍ ያለ የኩራት ስሜት ተሰማው።

አበበ ሁኔታውን በዝምታ ማለፍ አልቻለም። «እነዚህ




**አበበ ቢቂላ በሮም ኦሊምፒክ በባዶ እግሩ ማራቶን ያሸነፈው ጳጉሜ 5 ቀን 1952 ዓ.ም ነበር፣**

ስፖርተኞች እነማን ናቸው» ብሎ ጠየቀ። ስፖርተኞቹ እነ ማሞ ወልዴና እነ ባሻዬ ፈለቀ ነበሩ። የአትሌቲክስ ፍቅር ወደ አበበ ውስጥ የዘለቀው ከዚያች አጋጣሚ በኋላ እንደሆነ ይነገራል። «ኢትዮጵያ» ተብሎ የተፃፈበት ልብስ ለመልበስና በዓለም አቀፍ ውድድር ሀገሩን ወክሎ ለመሳተፍ ቁርጠኛ ጥረት ጀመረ። በዚሁ ዓመት የጦር ሠራዊት ብሄራዊ ሻምፒዮና የማራቶን ውድድር ተካፈለ። በወቅቱ ታዋቂ ከነበሩት አትሌት ዋሚ ቢራቱና ሌሎች አትሌቶችም ጋር ተወዳደረ።

ዋሚ ቢራቱ የወቅቱ የአምስት ሺህ እና የ 10 ሺህ ሜትር የኢትዮጵያ ክብረወሰን ባለቤት ስለነበሩ፤ በዚሁ የማራቶን ውድድር እንደሚያሸንፉ ቢጠበቅ አይገርምም። ሩጫውን በቀዳሚነት እየመሩ ነበር። ከተወሰኑ ኪሎ ሜትሮች በኋላ ግን ስታዲዬም ውስጥ የነበረው ሕዝብ ውድድሩን ከሚዘግቡ ጋዜጠኞች «አበበ ቢቂላ እየመራ ነው» የሚል ያልተጠበቀ ዜና ሰማ። «ማን ነው አበበ? ይህ አዲስ ባለታሪክ ማነው?» በማለት በአድናቆት ሲጠብቅ የነበረው ሕዝብ መልስ አገኘ። አበበ ቢቂላ ለመጀመርያ ጊዜ በተሳተፈበት የማራቶን ውድድር አሸነፈ።

አበበ ቢቂላ በሌሎች ውድድሮችም አሸነፈ። በአምስት ሺህ እና በ10 ሺህ ሜትር ርቀቶች በአትሌት ዋሚ ቢራቱ ተይዞ የቆየውን ብሔራዊ ሪከርድ ሲሰብር፤ ብዙዎች ኢትዮጵያ አዲስ ጀግና አትሌት ማፍራቷን ተናገሩ። የአበበ የመጀመሪያ ህልምም እውን ሆነ። በውድድሮች ባሳየው ድንቅ ብቃት ለኦሊምፒክ ቡድን ተመረጠ።

በጦር ካምፕ ውስጥ አበበ የሚያደርጋቸውን ልምምዶች እና ውድድሮች በጥሞና ይከታተሉ የነበሩት ስዊድናዊ አሠልጣኝ ኦኒ ኒስካነን፣ የአበበን ችሎታ በመገንዘባቸው ከሌሎቹ አትሌቶች ጋር ተቀላቅሎ እንዲለማመድና፣ የሮም ኦሊምፒክ እስኪቃረብ ድረስም ከሁለት ሺህ ሜትር በላይ ከፍታ ባላቸው ተራራማ ቦታዎች ላይ የመሮጥና የአንድ ሺህ 500 ሜትር ተደጋጋሚ የፍጥነት ሩጫ ልምምዶችን እንዲሠራ አደረጉት። ኢትዮጵያ በታሪኳ ለሁለተኛ ጊዜ በምትሳተፍበት የሮም ኦሊምፒክ ላይ ሲያልመው የነበረውን «ኢትዮጵያ» ተብሎ የተፃፈበት የብሔራዊ ቡድን ትጥቅ በመልበስ በ1952 ዓ.ም ወደ ሮም አመራ።

በሮም ኦሊምፒክ ኢትዮጵያን ወክለው ለመሳተፍ ከአሰልጣኙ ጋር ወደ ሮም ካመሩት የኢትዮጵያ ተወዳዳሪዎች መካከል ለማራቶን ሩጫ የተመረጡት አበበ ቢቂላ እና አበበ ዋቅጅራ ነበሩ። ይሁን እንጂ ከ83 ሀገራት የተውጣጡ ከአምስት ሺህ በላይ አትሌቶች በተካፈሉበት የሮም ኦሊምፒክ ላይ የዓለም ሕዝብ ትኩረት በአውሮፓውያን አትሌቶች ላይ ነበር። ስለኢትዮጵውያን አትሌቶች በተለይም ስለ አበበ ቢቂላ የሚያውቀው ነገር አልነበረም። አበበ ቢቂላ ወይም ሌላ አፍሪካዊ አትሌት ሊያሸንፍ እንደሚችልም አልተጠበቀም፤ ከዚያ በፊት አንድም አፍሪካዊ በኦሊምፒክ ታሪክ ሜዳሊያ አግኝቶ አያውቅምና።

አሠልጣኙ ኒስካነን የሞሮኮው ራህዲ ቤን አብዴሰላም፣ የኒውዚላንዱ ባሪ ማጊ፣ የሶቭዬት ኅብረቶቹ ኮንስታንቲን ቮሮብዮቭ እና የወቅቱ የማራቶን ክብረ ወሰን ባለቤት የነበረው ሰርጌይ ፖፖቭ (2:15:17.0) እንዲሁም የብሪታንያው ዴኒስ ኦጎርማን የጊዜውን ምርጥ ማራቶን ተወዳዳሪዎች እንደነበሩ ለሁለቱ ኢትዮጵያውያን ሯጮች በጥብቅ ነግረዋቸዋል። ይሁን እንጂ የሞሮኮው ራህዲ ቤን አብዴሰላም ይለብሰዋል የተባለው የመለያ ቁጥሩ 26 የነበረ ቢሆንም የለበሰው መለያ ግን በአስር ሺህ ሜትር ውድድር ላይ ለብሶት የነበረውን መለያ ነበር። ስለሆነም አበበ የሞሮኮው ሯጭ የትኛው እንደሆነ አላወቀም ነበር።

ውድድሩ ተጀመረ። ታላቅ ህልም ያነገበው አበበ ማንም ሳይጠብቀው መሪዎቹን እየተከታተለና በመጨረሻም ቀድሚቸው ውድድሩን በአስደናቂ ብቃት በአሸናፊነት አጠናቀቀ።

አበበ ቢቂላ ውድድሩን በ2:15:16.2 በማጠናቀቅ የዓለምን ክብረ ወሰንን ሰብሮ የወርቅ ሜዳሊያ አገኘ። ራህዲ ሁለተኛ፣ ባሪ ማጊ ደግሞ ሦስተኛ ደረጃን አገኙ። የአበበ ፍላጎትና ሃሳብ ራህዲ እስከሚያጋጥመው ድረስ ጉልበቱን ለመቆጠብ ነበር። በዚህ ምክንያት ባይሆን ኖሮ ክብረ ወሰኑን በተሻለ ውጤት ይሰብር እንደነበር አሠልጣኝ ኒስካነን ጥርጣሬ እንዳልነበራቸው ገልጸዋል።

የሮም ኦሊምፒክ የማራቶን ውድድር ውጤት የዓለምን ታሪክ ቀየረ። ለኢትዮጵያ ብቻ ሳይሆን ለመላው አፍሪካና ለዓለም ጥቁር ሕዝብ ድል ያበሰረ ችቦ አቀጣጠለ። በኦሊምፒክ ታሪክ የሜዳሊያ ባለቤት ለመሆን የቻለ የመጀመሪያው አፍሪካዊ ስፖርተኛ ሆኖ ስሙ በታሪክ መዝገብ ላይ በወርቃማ ቀለም ሰፈረ።

አበበ ቢቂላ የማራቶንን ርቀት ሮጦ ያሸነፈውና ሪከርድ ያስመዘገበው በባዶ እግሩ መሆኑ ደግሞ የመላ ዓለም ስፖርት አፍቃሪዎችን በእጅጉ ያስደነቀ፣ የአበበ ቢቂላን ስምና የኢትዮጵያን ዝና በመላው ዓለም ተቀርፆ እንዲቀር ያደረገ ነበር። ጋዜጠኞች አበበ ለምን ያለ ጫማ በባዶ እግሩ እንደሮጠ ጠይቀውት « ... እኛ ኢትዮጵያውያን ሁሌም የምናሸንፈው በጀግንነትና በወኔ እንደሆነ ለዓለም ሕዝብ ለማሳወቅ በመፈለጌ ነው...» ብሏል።

በውድድሩ ማግሥትም፣ የኢጣሊያ ጋዜጦች በትልልቅ ፊደሎች ጎልቶ የሚታይ ርዕስ በመፃፍ «ሮምን የወረረ ኢትዮጵያዊ» የሚል አዲስ ስም አወጡለት። አበበ የክብር ዘበኛ ወታደር እንደሆነ ጋዜጠኞቹ ስለሚያውቁ «ኢትዮጵያን ለመውረር የኢጣሊያ አገር ወታደር ሁሉ አስፈልጎ ነበር፤ ጣሊያን ኢትዮጵያን ለመውረር ግዙፍ ጦር አዝምቶም ነበር። ኢትዮጵያ ግን አንድ ወታደር ብቻ ልካ ድፍን ሮምን ወረረችው ...» የሚል ጽሑፍ ይዘው ወጡ። ለመጀመሪያ ጊዜ በኦሊምፒክ ውድድር አሸንፎ የወርቅ ሜዳሊያ የወሰደ ጥቁር አፍሪካዊ አበበ ቢቂላ ነው። ይህም አጋጣሚ ብዙ ጥቁር አፍሪካውያን በዓለም አቀፍ ውድድሮች እንዲሳተፉ በር ከፍቷል። የአበበ ቢቂላ ዝናም ከዓለም ጫፍ እስከ ጫፍ ተዳረሰ።

እስከ ጥቅምት 1954 ዓ.ም ድረስ አበበ በግሪክ፣ በጃፓን እና በቼኮዝሎቫኪያ በማራቶን ተወዳድሮ በሁሉም አንደኛ በመውጣት አሸንፏል። ሐምሌ 3 ቀን 1956 ዓ.ም አዲስ አበባ ላይ በተካሄደው የኢትዮጵያ የኦሊምፒክ ማጣሪያ ውድድር የኦሊምፒክ ሜዳሊያና ክብረወሰን ባለቤቱ አበበ ቢቂላ አንደኛ፣ ማሞ ወልዴ እና ደምሴ ወልዴ ደግሞ ሁለተኛና ሦስተኛ በመውጣት አጠናቀቁ፤ ሦስቱም ወደ ቶኪዮ እንደሚጓዙ ሲረጋገጥ ኢትዮጵያ አንድ ብቻ ሳይሆን ሦስት ኃይለኛ ተወዳዳሪዎች እንዳሏት በመላው ዓለም ተሰማ።

የዓለም መገናኛ ብዙኃንም ዝነኛውን አበበ በኦሎምፒክ ማራቶን በድጋሚ ለማየት እንደጓጉ አራት ዓመት አለፉና የቶኪዮ ኦሊምፒክ ደረሰላቸው። ይሁን እንጂ በዚህ የጉጉት ፈንጠዝያ መሐል አስደንጋጭ ወሬ ተሰማ፤ አበበ ታመመ። ኢትዮጵያውያን በድንጋጤና በኀዘን ሲዋጡ፤ ስፖርት አፍቃሪው የዓለም ሕዝብ ግራ ተጋባ። አበበ በትርፍ አንጀት ህመም መሮጥ ተቸግሯል፤ ካልታከመ መኖር አይችልም። የቀዶ ጥገና ህክምና ቢደረግለት የማገገሚያ ጊዜ ያስፈልገዋል። ለኦሊምፒክ የቀረው ጊዜ ደግሞ ከሁለት ወራት ያነሰ ነው። ወከባ ሆነ።

የቶኪዮ ኦሊምፒክ 40 ቀናት ሲቀሩት የቀዶ ህክምና ተደረገለት። በፍጥነት እንደሚያገግም ተስፋ በማድረግ የኦሊምፒክ ቡድን ውስጥ ተካተተ። ገና ጤናው ስላልተመለሰ እያነከሰ ነበር የሚራመደው። በቶኪዮ የተደረገለት ልዩ የአድናቆትና የፍቅር አቀባበል በፍጥነት እንዲያገግም እንዳገዘው ይነገራል። እንዲያም ሆኖ በውድድር ይሳተፋል ተብሎ አልተጠበቀም። በእርግጥ በሮም ኦሊምፒክም ያሸንፋል ተብሎ ሳይጠበቅ ነበር ዓለምን ጉድ ለማሰኘት የበቃው። በቶኪዮም ተመሳሳይ ታሪክ እንዲደገም ተስፋ ያደረጉም ነበሩ።

አበበ ከኢትዮጵያ የኦሊምፒክ ቡድን ጋር አብሮ ወደ ቶኪዮ ሲጓዝ በርትቶ ይወዳደራል ብሎ ያሰበ ብዙ ሰው አልነበረም። አበበ ግን አደረገው። ጥቅምት 11 ቀን 1957 ዓ.ም ከ41 ሀገራት ከተውጣጡ 79 ተወዳዳሪዎችና ከሁለቱ ኢትዮጵያውያን (ማሞ ወልዴና ደምሴ ወልዴ) ጋር ለውድድር ተሰለፈ። ያሸንፋል ብለው ያላሰቡት አድናቂዎቹ በውድድሩ በመሳተፉ ብቻ ፈንድቀዋል።

ከተወዳዳሪዎቹ መካከል ብዙዎች ውድድሩን አቋረጡ። ብዙዎች ጉልበታቸው ዝሎ በየመካከሉ እረፍት ማድረግ ግድ ሆነባቸው። አንዳንዶቹ ተዝለፍልፈው ወደቁ። ማሞ ወልዴ 15 ኪሎ ሜትሮችን ከሮጠ በኋላ አቋረጠ። ቀዶ ጥገና አድርጎ ብዙም ሳይቆይ ወደ ውድድሩ የገባው ልበ ብርቱው ሰዉ አበበ ቢቂላ ግን እንደተለመደው ብቻውን ወደፊት ገሰገሰ። አሯሯጡ ከጥቂት ሳምንታት በፊት ቀዶ ጥገና የተደረገለት አላስመሰለውም። አሯሯጡ የአትሌቲክስ ባለሙያዎችን ያስደነቀም ነበር።

ሞቃታማው የአየር ሁኔታ ሳይበግረው ወደፊት በረረ። ሲሮጥ ለሚመለከተው ከመሬቱ በላይ የሚንሳፈፍ ይመስል ነበር። አበበ ኦሊምፒክ ስታዲዮሙ ውስጥ የገባው ብቻውን ነበር። በዚያም ይጠባበቅ የነበረው 70 ሺህ ተመልካች በከፍተኛ ሁኔታ አድናቆቱን ገለፀለት። በዚህ ውድድር ላይ የራሱን ክብረ ወሰን በድጋሚ በማሻሻልም ማሸነፍ ቻለ። በሁለት የኦሊምፒክ ማራቶን ውድድሮች ላይ አከታትሎ ሁለት የወርቅ ሜዳልያዎችን ማግኘት ቻለ። አበበ ሁለተኛውን ወርቅ ይዞ ወደ ኢትዮጵያ ሲመለስ የአዲስ አበባ ሕዝብ በነቂስ ወጥቶ የጀግና አቀባበል ካደረገለት በኋላ ንጉሠ ነገሥቱ ቀዳማዊ አጼ ኃይለሥላሴ የሻምበልነት ማዕረግ እና አዲስ ቮልስ ዋገን ቢትል መኪና ሸለሙት።

በመቀጠል ወደ ሜክሲኮ ኦሊምፒክ ያመራው ጀግናው አበበ፣ የሜክሲኮ ከፍተኛ የመሬት አቀማመጥ ከአዲስ አበባ ጋር ስለሚቀራረብ እንደሚስማማው ገምቶ ነበር። በተጨማሪም ጥሩ የብቃት ደረጃ ላይ እንደሚገኝ ቀደም ብለው በተደረጉ ውድድሮች አውቋል። ስለሆነም አበበ የሜክሲኮውን ውድድር እንደሚያሸንፍ የበርካቶች እምነት ነበር።

አበበ 15 ኪሎሜትሮችን ከሮጠ በኋላ፤ እንደተፈራው ህመሙ ከአቅም በላይ ሆኖበት ውድድሩን ለማቋረጥ ተገደደ። አበበ ውድድር ሲያቋርጥ፤ የኢትዮጵያውያንና የአፍሪካውያን አሸናፊነት አልተቋረጠም። «ጀግና ጀግናን ያፈራል» ነውና ከአበበ ጋር እየሮጠ የነበረው ኢትዮጵያዊ አትሌት ማሞ ወልዴ፤ ሳይጠበቅ ድል አድርጎ የማራቶንን ክብር ለኢትዮጵያ አጎናፀፈ።

አበበ በ1960 ዓ.ም ከአዲስ አበበ ወጣ ብላ በምትገኘው ሸኖ ከተማ መኪናውን እያሽከረከረ ሳለ የትራፊክ አደጋ ሲደርስበት፤ ዓለም ሁሉ ከኢትዮጵያውያን ጋር ደንግጧል፤ አዝኗል። በሀገር ውስጥና በእንግሊዝ ህክምና ቢደረግለትም በአደጋው የደረሰበት ጉዳት ከፍተኛ ስለነበረ ከወገቡ በታች ያለውን የሰውነት አካሉንና እግሮቹን ማንቀሳቀስ አልቻለም። ነገር ግን የስፖርተኛነት መንፈሱ እንደ ድሮው ብርቱ ስለነበር በተሽከርካሪ ወንበር ላይ ሆኖ አካል ጉዳተኞች በሚሳተፉባቸው ዓለም አቀፍ ውድድሮች ላይ ተሳትፎ ለማሸነፍ በቅቷል። የትራፊክ አደጋ ደርሶበት ሁለት አመት ሳይሞላው በኖርዌይ በተከናወነው የ25 እና የ10 ኪ.ሜ የአካል ጉዳተኞች ውድድሮች ላይ በማሸነፍና ለኢትዮጵያውያን የአካል ጉዳተኞች ስፖርት በግንባር ቀደምትነት የሚጠቀስ በመሆን ፈር ቀዳጅነቱን በድጋሚ አስመስክሯል።

ዓለም በመሰከረለት ጀግንነቱና ብቃቱ ህያውነትን የተቀዳጀው ሻምበል አበበ በቂላ፤ ጥቅምት 15 ቀን 1966 ዓ.ም፣ በ41 ዓመቱ ከዚህ ዓለም በሞት ተለይቷል። ሥርዓተ ቀብሩም ንጉሠ ነገሥቱን ጨምሮ እጅግ በርካታ ሕዝብ በተገኘበት ተፈፅሟል።

ስፖርት እና መዝናኛ

# የዝነኞች ገጽ

# የዜማው ጥምቆራጩ

**ሙሉጌታ ብርሃኑ**



ትናንት በወጡበት የስኬት ከፍታ፣ በወጡበት የብቃት ሰገነት እምቢ! አልወርድ...አሻፈረኝ! ብሎ ዛሬም ድረስ መክረም እንደምን ይቻላል... አስችሎት መቻልን ያሳየ እንቁ ሙዚቀኛ ግን ወዲህ አለ። ብዙዎች ወጡ! ወጡ! ሲባል ከምኔው እንደሆን ወርደው በሚፈርጡበት የሙዚቃ ኢንዱስትሪው ውስጥ የሌላውን ሳይነካ የራሱንም ሳያስነካ፣ ሳያዳልጠውና ዝናው ሳያሰምጠው ደርሶ ዛሬም በሌላ ከፍታ ከፍ ብሎ ታይቷል።

"አንድ ቃል" ድሮም ለሚገባው አንድ ቃል ነው። ተወዳጁ ድምጻዊ ሚካኤል በላይነህ ከሰሞኑ በአንድ ቃል ምርጡን! የአልበም ሥራ ይዞ መጥቷል። እርሱ ይወደዳል። ሥራው ይናፈቃል። እንደተወደደ ሥራውን ለናፈቁ ሁሉ እንደ አዲስ ዓመት ገጸ በረከት ሆኗል። ሙዚቀኛ ነኝ ብሎ ለራሱ እንኳን ሳያምንበት በጀመረውና በሠራው ሥራ አድናቆትና ክብርን ተጎናጽፏል። ለረዥም ጊዜያት በሙዚቃና ሙዚቀኝነት ሲዋልል ኖሯል። ሆኖም የሙዚቃን ጠረን ምገው፣ ሥራውን በመጀመር አድማጭ ከተዋወቃቸው ጊዜ አንስቶ በክብራቸው እንዳሉ አሉ ከሚባሉ ጥቂት በጣት የሚቆጠሩት ጋር ነው። የአድማጩን የሙዚቃ ጥም ያረካ፣ የጥበብን አንጀት ያራስ ድምጻዊ ነው። ደግሞ ድምጻዊ ብቻ ሳይሆን የግጥምና ዜማ ደራሲም ጭምር ነው። ሦስቱ የአልበም ትርንጎዎች በ20 ዓመታት ውስጥ ያፈራቸው የሥራ ፍሬዎቹ ናቸው።

ተወልዶ ያደገው እዚሁ አዲስ አበባ ከተማ ውስጥ ነው። የተወለደው በኮተቤ ቢሆንም ያደገው ግን እዚህ ሰፈር ነው እዚያ ነው ለማለት ሳይከበድ አልቀረም። በልጅነቱ ከቤተሰቡ ጋር አብሮ ለኑሮ ያልዘመተበት ሰፈር አልነበረም። በዚያም ቢሉ በዚህ ቤታቸው ውስጥ የታጨቁ የሙዚቃ ካሴቶች አይጠፉምና ጓደኞችም ጭምር ነበሩ። ሙዚቃ መስማትና መውደድ እንጂ ሙዚቀኛ እሆናለሁ የሚል ሃሳብ እንኳን አልነበረውም። እንዲያው የሙዚቃ አድባር በእጁ ላይ ጣለችው እንጂ እንደ እርሱ ሙከራዎች ቢሆንማ ኖሮ ለሙዚቃው ከፍቅር ሌላ ባልኖረው ነበር። እንዲው የሙዚቃ ህልም አልሞ አያውቅም። ስለመሆን ከተባለ ህልሙ ሀኪም የመሆን ነበር። ግን ሳይሳካለት ቀረና ወደ ባህርዳር ዩኒቨርሲቲ አቅንቶ በኢንዱስትሪያል ኤሌክትሪክ ሲቲ ዲፕሎማን ጨብጦ ወጣ። በዚህም ደስተኛ የሆነ አይመስልም ነበር። ምክንያቱ ደግሞ ቀደም ሲል መሰናዶ ትምህርት ቤት ውስጥ ጀምሮ የተላለፈው አንድ መስመር እንደነበር ውስጡ በደም ነብስ ቢያምንም ለውስጡ ቅሬታ መፍትሄ ሰጥቶ ማስተካከሉ ግን አልመጣለትም።

ካለው ተሰጥኦ አንጻር መሆን የነበረበት የማህበራዊ ሳይንስ ተማሪ ነበር። ሚካኤል መርጦ የገባው ግን የተፈጥሮ ሳይንስን ነው። ፍላጎቱና ድርጊቱ ለየቅል እንደሆነበት ሰው ግራ ተጋባ። ለመውደቅ የሚያበቃ ችሎታ ባይኖረውም ሳያልፍ ቀረ። ወደ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ጎራ ብሎ እንደገና በሌላ ዘርፍ በግሉ በመማር እሱንም አጠናቀቀ። በሁለቱም ዘርፎች እየሠራ፣ በሁለት እግሩ ቆሞ አሻቅቦ የሚመለከተው ግን ሌላ ነገር ነበር። ብዙ ነገሮች እየመጡ ፊቱ ድቅን ይላሉ።

በተለይ የንግዱ ዓለም ጥሪ ሁሌም ከጆሮው እንዳቃጨለ ነው። ማቃጨል ብቻ አይደለም ገብቶም የአቅሙን ያህል ታግሏል። በወሬ ወሬ አንዳንዶች "ሻወርማ (ጣፋጭ የመንገድ ላይ ምግብ) በአዲስ አበባ ከተማ ውስጥ ለመጀመሪያ ጊዜ የጀመረው ሚኪ ነው" ይላሉ። በእርግጥ የመጀመሪያው ስለመሆኑ እርሱም በውል ባያውቀውም አለ ተብሎ ለመናገር በማይቻልበት ጊዜ እንደጀመረ ይናገራል። ደግሞ ቀደም ሲል በመሃል ቦሌ "ፐርፐል" የተሰኘ ካፍቴሪያ ከፍቶ ነበር። ቤቱ ታዋቂ ከሆነ በኋላ በጊዜው አሉ የተባሉ ሙዚቀኞች ሁሉ መገናኛቸው እዚያ ካፍቴሪያ ውስጥ ነው።

እነ ኤሊያስ መልካ፣ ጆኒ ራጋ፣ ላፎንቴና ሌሎችም ከቤቱ እየመጡ ፊት ለፊት ያገኛቸውም ነበር። እንዲያውም በአንድ ቆየት ባለ ቃለ ምልልሱ ውስጥ እንደተናገረው፤ ቴዲ አፍሮ በዚያው በቦሌ በከፈተው የራሱ ሬስቶራንት ውስጥ ይዘፍን እንደነበርና እሱም ከዚያ እንደማይቀር ይናገራል። ሚካኤል ያ ቅር ቅር የሚያሰኘው ነገር ምን እንደነበር አሁን ሳያወቀው አልቀረም። ብዙም ትኩረት ያልሰጠው የሙዚቃ ፍቅሩ ውስጡ ታፍኖ ሲለበልበው የነበረ መሆኑን ተረዳ። ከሚመለከታቸው ነገሮች ጋር ነብስያው አብራ ነጎደች። ተከትሎም ወደ ኮንኮርድ ሆቴል ሄደ። በጊዜው ትልቅ የሙዚቃ ዝግጅቶችና ልምምዶች የሚካሄዱበት ስፍራ ነበር። አስቀድሞ ተግባብቷቸዋልና ከልምምድ ክፍሎች ውስጥ እየገባ ፒያኖውን፣ ጊታሩን...ብቻ ከዓይኑ የገባውንና ቀልቡ የሳበውን ሁሉ እያነሳ ያጫውታቸዋል። የእንግሊዝኛ ሙዚቃ ሽታ ሸው! ያለበትም የዚህን ጊዜ ነበር። በእነ ጂሚ ግሬፍ፣ ጂምሬቭስና ሳምኩክ ሙዚቃዎች በተመስጦ ባህር ይሰምጣል። ደግሞ መለስ ይልና ከሀገር ውስጥ በነ ሰይፉ ዮሐንስ፣ ግርማ በየነና ተሾመ ምትኩ ሙዚቃዎች በስሜት እየዋኘ ተሰጥኦውን በችሎታ ያጎለብተው ጀመረ። "እጅግ ደስ የሚለውን ሕይወት ያሳለፍኩት ኮንኮርድ በነበረኝ ቆይታ ነው" ሲል ይናገራል።

ከዚህ በኋላ ነበር ለሙዚቃ ፍቅር ብቻ ሳይሆን ዕውቀትም ግድ እንደሚለው በማሰብ ወደ ያሬድ ሙዚቃ ትምህርት ቤት በመግባት የፒያኖ ሙዚቃ መጫሪያ መማር ጀመረ። በመሃል ግን ተምሮ ሳይጨርስ ሌላ ዕድል አጋጥሞት ሙዚቃን ሊጫወት አቋርጦ ሄደ። "መዲና ባንድ" በሩን ከፍቶ ጠበቀው። እኚያን የእንግሊዝኛ ሙዚቃዎች መድረክ ላይ መዝፈን ማንጎራጎር የጀመረውም እዚህ ነበር። ለዚህ ሁሉ ዛሬው ያቺ የጅምር ትናንትናው መዲና ነበረች። በዚያው በመዲና መድረክ ላይ እጅግ አንጋፋ ከምንላቸው ጋር በአንድ መድረክ ቆሞ ለመሥራት ችሏል። ከፊት ጥላሁን ገሠሠ ነበር። ማህሙድ አህሙድ፣ ሀመልማል አባተ፣ ምኒልክ ወስናቸውና ሌሎችም ከነበሩበት መድረክ ላይ መታየቱ ለእርሱ ትልቁ ስኬት የነበረ ስለመሆኑ ተናግሮታል።

ያኔ ገና ሙከራን የማይታከተው ሚካኤል የሙዚቃን እጅ ከሳመ በኋላም ወዲህ ወዲያ ማለቱን አላቆመም ነበር። መሆንን አይጠላም። ሁሉንም ሆኖ የማየትና የመሞከር ጉጉቱ እንጥሉ ስር ናት። ብዙ እንዲያማትር ያደረገው ነገሮችን የማወቅ ፍላጎቱ ነበር። "በአንዱ ቦታ ሰንጥቄ እንደምወጣ አውቀው ነበር" እያለም እዚህም እዚያም ሲል ከዳኒ አይሬ ጋር በአይሬ የሬዲዮ ፕሮግራም፣ ቪላቬርዴ... ከሙከራዎቹ ናቸው። እንደገና ከአራት ዓመታት በፊት አንድ የሙዚቃ መተግበሪያን እውን ለማድረግ ተፍ! ተፍ! ሲል በኮቪድ ወረርሺኝ ተይዞ የጉዞ መስመሩን ጠምዝዝዞ ሳያስበው ወደ ማገገሚያ ሆነ። አሁን ላይ ሆኖ ባለፈው ልጅነቱ፤ ብሆን ኖሮ ብለህ የምትመኘው ምንድነው ሲባል "ዕድሉን አግኝቼ ዲያቆን ሆኜ ቢሆን ኖሮ ደስ ይለኝ ነበር" ይላል። የቀረው ይሄው ነው... ምኞት እንደነበረው የገለጸላቸው አንድ አባትም "ልጄ መቼም ላንተ ባይለው ነው" እንዳሉት ያስታውሳል።

ሙዚቃ ከአድማጭ ጆሮ አልፎ፣ ሥርዓተ ውህደቱን በልብ ውስጥ ከውኖ፣ በመላ ደም ስር ውስጥ ገብቶ ሀሴትና ስሜት ሲፈነጥቅ ማለት በርሱ ሙዚቃዎች ውስጥ ነው። በደፈናው ምናልባትም ሁለት ዓይነት የሙዚቃ አድማጮች አሉ። የመጀመሪያዎቹ ከመልዕክቱ ይልቅ የሙዚቃው ምቱ ስልቱ በእንብርክክ የሚያስኬዳቸውና ከዳንስና ቡጊ! ቡጊ! ጋር ዘና እያሉ ከሚነጥር ስሜት ጋር ደስታቸውን በአስረሽ ምቺው ማጣጣም የሚፈልጉ ናቸው። ሁለተኛዎቹ ደግሞ የምን ከበርቻቻ...በማለት እረጋ ሰከን ካለ ስሜት ጋር በግጥምና ዜማው መንፈስ የሚፈሱ ናቸው። መጨፈር ቢያምራቸው እንኳን እንደ ሳልሳ ዳንሳ፣ አለፍ ካለም ፍሰት ያለው ማሪንጌን የሚመርጡ ዓይነት ናቸው፤ ሁለቱንም የሚወዱ ሦስተኛዎቹ እንዳሉ ማለት ነው።

መነሻዬን ስቼ እንዳልጠፋ አነሳሴ የሚካኤል በላይነህ ሙዚቃዎችን በፍቅር እፍ! የሚሉባቸው አድማጮች የትኞቹ ናቸው ለሚለው ነው። መደምደሚያውም ሁለተኛ ላይ ያሉት አድማጮች አብልጠው ሚካኤል በላይነህን ይመርጡታል። እጅግ ሞቅ ያለና ለጭፈራ ስልቱ፣ ለዳንስ ወረድ ወረድ አመቺ መስለው የሚታዩ የሙዚቃ ሥራዎቹ እንኳን ከውጫዊ ይልቅ ውስጣዊ የስሜት ጥልቀት ያላቸው ናቸው። እያደመጧቸው ከምቱ ጋር ብቻ ነሁልለው ግጥምና መልክዕክታቸውን ዘለው የሚያልፏቸው አይደሉም።

ሚካኤል በአንድ ሠርግ ላይ ተገኝቶ ሠርጉን በመታደም ላይ ነበር። ከታዳሚው መሃል ድንገት ከዓይኑ ውስጥ የውበት ቀለም በብርሃን ፈሰሰ። የተመለከታትን ቆንጆ ኮረዳ እንደማረከችው የሚማርክበትን ዘዴ እያሰላሰለ ጠጋ አላት። ኮከብ የገጠመ ዕለት ጥቅሻም ፍቅር ነውና የገባው ነገር ሳይገባት አልቀረም። በኋላ ከተጋቢው መሃል ተግባብተው ሲለያዩ "በትልልቅ ሠርጎች መሃል ትንንሽ ሠርጎች አሉ" የሚለውን የባለዕጣዎችን መፈክር በልባቸው እያሰሙ ይመስላል። ቢሆንም ግን በሰዓቱ ልጅቷ የምትሠራው በውጭ ሀገር ውስጥ ነበር።

ሌላ አስቸጋሪው ነገር ደግሞ ከምትሠራበት "ኢትሀድ" በቅርቡ በዚያው ወደ አሜሪካን ሀገር የመሄድ ህልምና ዕቅድ ነበራት። ከዚያ በፊት ግን ከሚካኤል በላይህ ጋር ቀጠሮ ነበራቸው። እመጣለሁ ብላዋለች። በቀናት መካከል ሲጠብቃት አንድ ቀን ከቤቱ ውስጥ ቁጭ ብሎ ሳለ ድንገት የሆነ የሙዚቃ ሰማይ ተከፈተለት። ከነበረበት ሶፋ ላይ ብድግ ብሎ እንደሄደ ከፒያኖው ፊት ተቀመጠናም የፒያኖውን ቁልፎች እየነካካ እንዲህ አለ፤

"ሰርክ የማይታክተኝ
አለሁሽ ጠባቂ
...
ትመጪ እንደሆን
ትመጪ እንደሆን
አለሁ እኔ ሳላጎል
በፍቅር እንዳለሁ"

የሚለውን ተወዳጅ ዜማ በድንገተኛ የምናብ ጽንስ አምጦ ወለዳት። ፍቅሩንም አበጀባት። ቀደም ሲል የመጀመሪያ ባለቤቱን በሞት ተነጥቆ አስከፊና መራራ ጊዜያቶችን ሲያሳልፍ ቆይቷል። አጋጣሚው ለተሰበረው ልቡ ካሳ ባይሆንም ምናልባትም ግን ሸሮለታል። አዲስ ተስፋና አዲስ ነገን መመልከት ጀምሯል።

ከዚህ ቀደም "አንተ ጎዳና"፣ "ናፍቆትና ፍቅር" በሚሉ በእነዚህ ሁለት አልበሞቹ መወደድና ክብርን ሸምቷል። በአልበሞቹ የአድማጩን ልብ የደስታ ፈንዲሻ አድርጎታል። አሁን ደግሞ ሦስተኛው የሆነውን አልበም "አንድ ቃል" ከሚል መጠሪያ ጋር አቅርቧል። ነሐሴ 17 ቀን 2016ዓ.ም የአልበም ሥራውን በራሱ የዩትዩብ ገጽ ላይ ከቀለቀቀው በኋላ የአድማጩ ልብ በድጋሚ መፍካቱን ቀጥሏል። "ምንም የሚጣል የሌለው ልቅም ያለ ሥራ!" ያሉም ብዙዎች ናቸው።

"እኔ ሱፍ አበባ
አንች የኔ ጸሐይ
በዞርሽበት ሁሉ
እየዞርኩ የምታይ"

ከአዲሱ አልበም ውስጥ "ውስጠ ወይራ" ከሚለው ሙዚቃ የሚቀነጨብ ስንኝ ነው። የግጥሙ ደራሲ ሠለሞን ሳህለ (ያማል) ነው። ራሱ ሚካኤልን ጨምሮ ሌሎች ብርቱዎችም በተሳተፉበት በዚህ አልበሙ ውስጥ እጅግ ጠንከር! ጠንከር! ያሉ የግጥም ሸመሎች ያረፉበት ነው። ከመሃከል አንዱ የሆነው "ውስጠ ወይራ" ርዕሱ እንደሚነግረንም በቀላሉ አንድደው የማይፈጁት የሙዚቃ ሥራ ነው። "ትመጪ እንደሆን..." ከላይ ዜማ ለሸለማት ባለቤቱና የሁለት ልጆቹ እናት አሁን ደግሞ "ጠይም" ብሏታል። አንድ ቃልና ማለዳም የሙዚቃ ጀንበር መውጫ ናቸው። እንዳሉትም ሁሉም ልቅም ያሉ ናቸው።

የግሉ የስሜት ነጎድጓድ ከሆኑ የአልበም ሥራዎቹ ባሻገር ማኅበራዊ አንደምታ ያላቸውን መልዕክት አዘል የፕሮጀክት ሙዚቃዎቹም በርካታ ናቸው። በኤች አይ ቪ ኤድስ፣ በአካባቢ ጥበቃና በአፍሪካ ህብረት ዙሪያ የተዜሙ ዜማዎቹም ተወዳጅ ናቸው። "ማለባበስ ይቅር" የሙዚቃው ግጥምና ዜማ ደራሲ እንዲሁም ፕሮዲዩሰር ራሱ ሚካኤል በላይ ነህ ነው። በመቀጠልም "መላ መላ" ነበር። "መሌ ሀራ" አሊ ቢራ የተሳተፈበት ሌላኛው ሥራው ነው። ቀረብ ባለው ጊዜ ውስጥ ደግሞ በጣም ተወዳጅ የሆነለትን "ከፍ እንበል በሥራ" ስለ ዓባይ በተዜመው ሙዚቃ ከዜማው ጀምሮ ከፍተኛውን ሚና ተጫውቶበታል።

በአንድ ወቅት ሚካኤል ነሸጥ አድርጎት ወደ ቲያትሩም ገባ። አንድ ቲያትር ካዘጋጀ በኋላም በገባበት ሹልክ ብሎ ወጣ። በኋላ ምነው ብለው ቢጠይቁት "አይ...ይኼ የኔ ሰፈሬ አይደለም" ሲል ጥሎ እብስ! አለ። ያደረገው ነገር ትልቅነት ነበር። የራስን ቦታና ተሰጥኦ ማወቅ አውቆም መተገበር የብዙዎች ችግር መሆኑን በግልጽ የምንመለከተው ነው። ይህን ያደረገው የርሱ ትክክለኛው ቦታና ጥሪ የሙዚቃው መንደር መሆኑን በመረዳት ነበር፤ በሰው ሙያው ውስጥ ገብቼ አልፈተፍትም ሲል መለስ ማለቱ።

ሦስት አልበሞችን ያወጣው ሚካኤል በላይነህ ሦስት ጊዜ ሙዚቃ በቃኝ ብሎ ከሙዚቃ ዓለም መንኖ ነበር። ከሙዚቃ መንደር ለማምለጥ ኮርቻና ግላሱን አልብሶ ቼ! ያለው ፈረስ እየወሰደ አንከላውሶ መልሶ ከዚያው ያመጣዋል። አሁንስ በቃኝ ብሎ ሸክፎ የወጣውን ሻንጣ መልሶ ይዞት ይገባል። ሄድ መለስ እያለ ሦስት ጊዜ ፊቱን ቢያዞርም ቆርጦ የሚቆርጥ አንጀት አጣና አንዱም ሳይሳካ ቀረ። በአንድ ጊዜም እንደልማዱ አሁንስ ተገላገልኩት ብሎ ከቤቱ እንዳለ ከዕለታት በአንዱ ቀን ስልኩ አቃጨለ። ሚካኤል ስልኩን አየው ግን የማያውቀው ቁጥር ነበር። እንዳነሳው ሃሎ! ከማለቱ "አዲስ ባንድ ላቋቁም ነበርና እባክህን አብረህ አቋቁመኝ..." የሚል የቀልድ ድምጽ ነበር። ድምጹ የማን እንደሆነ ግን አውቆታል። ኤሊያስ መልካ ነበር። ኤሊያስ መልካን አብዝቶ ይወደዋል። እጅግም ይቀራረቡ ነበር። አንተማ ሙዚቃ ማቆም የለብህም የሚለውን የኤሊያስን ሃሳብና ድምጽ ለመጋፋት አልተቻለውም።

ልቡ አፈንግጦ ሲሄድና ልቡ እየሸፈተ ሲመጣ... አስቀደሰ፣ ቀጠለ፣ በመጨረሻም ሰለሰ! "ሚኪ ተመለስህ መጣህ አይደል" ሲሉት "ምን ላድርግ ሙዚቃ እኮ ልክፍት ነው" ይላል። በእርግጥም ልክፍት እንጂ ሌላ እንዲህ የሚያደርገው ምን ይኖራል። ከነ ልክፍቱ ሙዚቃን እያሳደደ ሳይሆን እያሳደደችውም 20 ዓመታትን ሰነበተ። ከነ ልክፍቱም ሦስት አልበሞችን አስደመጠን። ከ"አንድ ቃል" በኋላ ከሰሞኑ ይህቺን ቃል አለ "ቀደም ሲል በሠራኋቸውም ሆነ በሌሎች ዘንድ አድማጬ በርታ! ጎበዝ ሲል ነበር የማውቃው ከዚህ አልበም መለቀቅ በኋላ የሚወደውሉልኝ አብዛኛዎቹ ሰዎች እናመሠግናለን! ነው የሚሉኝ" አለ። ያሉት ቃል ጠፍቶ አይደለም። ያሉት በምክንያት ነው። እጅግ በተጠማ ሰዓት ጥምን ለቆረጠ "እናመሠግናለን!" እንጂ ሌላ ምን ይባላል...

# ዓለም አቀፍ

## በተሳሳተ የቦምብ ስጋት በረራውን ያቋረጠው አውሮፕላን




**በጋዜጣው ሪፖርተር**

የህንዱ ቪስታራ አየር መንገድ በትናንትናው ዕለት 234 መንገደኞችን አሳፍሮ ከህንዷ የንግድ መዲና ሞምባይ ወደ ጀርመኗ ፍራንክፈርት እየበረረ ነበር፡፡

ይሁንና ይህ አውሮፕላን በጉዞ ላይ እያለ መጸዳጃ ቤት ውስጥ የተጣለ አንድ ወረቀት ሲገኝ ተሳፋሪዎችን አስደንግጧል፡፡

ይህ የተገኘው ወረቀትም በአውሮፕላኑ ውስጥ ቦምብ አብሮ እንደተጫነ የሚገልጽ ሲሆን፤ በበረራ ላይ የነበረው አውሮፕላን ወዲያውኑ ቱርክ ለማረፍ ተገዷል፡፡

የበረራ ቁጥሩ ዩኬ27 የተሰኘው ይህ አውሮፕላን የተሳፋሪዎችን ደህንነት ለመጠበቅ ሲባል ወዲያውኑ በቱርኳ ገጠራማ ከተማ በሆነችው ኢርዙሩም ኤርፖርት አርፏል፡፡

ይሁንና የቱርክ ጸጥታ እና ደህንነት ሰዎች በአውሮፕላኑ ላይ ባደረጉት ፍተሻ የተባለው ቦምብ አልተገኘም ሲል ሮይተርስ ዘግቧል፡፡

ኢርዙሩም ኤርፖርትም ይህ የቪስታራ አየር መንገድ ካረፈ በኋላ ሌሎች አውሮፕላኖች እንዳያርፉ እገዳ ጥሎም ነበር፡፡

13 የበረራ አስተናጋጆችን ጨምሮ 234 መንገደኞችን የጫነው አውሮፕላን ለተጨማሪ ደህንነት በሚል በዚሁ ኤርፖርት ይቆያል የተባለ ሲሆን፤ አየር መንገዱ ተለዋጭ አውሮፕላን ወደ ኡርዙሩም ኤርፖርት እንደሚልክ እና መንገደኞቹ ወደ ፍራንክፈርት እንደሚጓጉዝ አስታውቋል፡፡

ይሁንና እስካሁን ይህን ሐሰተኛ የቦምብ ጥቆማ ማን እንደሰጠው በዘገባው ላይ አልተጠቀሰም፡፡

## አሜሪካ ለዩክሬን ተጨማሪ የ250 ሚሊዮን ዶላር የጦር መሳሪያ ድጋፍ አደረገች

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

አሜሪካ ለዩክሬን ተጨማሪ የ250 ሚሊዮን የጦር መሳሪያ ድጋፍ ማጽደቋን አስታወቀች

በትናንትናው እለት የዩክሬኑ ፕሬዚዳንት ቮላድሚር ዘለንስኪ ከአውሮፓ አጋሮቻቸው እና ከአሜሪካ የመከላከያ ሚኒስትር ጋር በጀርመን ተገናኝተዋል።

በውይይቱ ጦርነቱን ለማስቆም በሩሲያ ላይ ተጨማሪ ጫናዎች እንዲደረጉ ፕሬዚዳንቱ ጠይቀዋል።

በተጨማሪም በሩስያ ውስጥ ጥቃት ለመፈጸም እንዳይውሉ የተከለከሉትን የረጅም ርቀት ተምዘግዛጊ ሚሳኤሎችን ለመጠቀም ጥያቄ አቅርበው ውድቅ ተደርጎባቸዋል።

ፕሬዚዳንቱ በሩስያ ዋና የአየር ማዘዣ ላይ ጥቃት ለመፈጸም ነው በረጅም ርቅት ሚሳኤሎች ላይ የተጣለው ክልከላ እንዲነሳ የጠየቁት።

የአሜሪካው የመከላከያ ሚኒስትር ሎይድ ኦስተን ለዚህ በሰጡት ምላሽ የረጅም ርቀት ሚሳኤሎችን በሩስያ ውስጥ ጥቃት ለመፈጸም ጥቅም ላይ ማዋል የጦርነቱን ውጤት አይቀይረውም ብለዋል።

በሩስያ ውስጥ የሚገኙ ግዙፍ ኢላማዎችን ለማጥቃት ካስፈለገም ዩክሬን የራሷን ድሮኖች መጠቀም ትችላለች ነው ያሉት።

ሚኒስትሩ በዚህ ውግያ በራሱ ወሳኝ የሚሆን የተለየ አቅም የለም የሩስያን ጥቃት ለመመከት የሚያስፈልገው የተቀናጀ ጥቃት እና ስትራቴጂ ነው ሲሉ ተናግረዋል።

ኬቭ በሩስያ ውስጥ ጥቃት ከመሰንዘር ይልቅ በድንበሯ ውስጥ እየገፋ የሚገኘውን የሞስኮ እግረኛ ጦር አቅምን ማሽመድመድ ላይ ብታተኩር መልካም ይሆናል ያሉት የመከላከያ ሚኒስትሩ፤ አሜሪካ ለዚህ ዘመቻ የሚያግዝ ተጨማሪ የ250 ሚሊዮን የጦር መሳሪያ ድጋፍ ማድረጓን አስታውቀዋል።

ከአሜሪካ በተጨማሪ ጀርመን 12 ከባድ መድፎችን የሰጠች ሲሆን፤ ካናዳ 80 ሺህ ከአየር ላይ የሚተኮሱ ሮኬቶችን በመጪዎቹ ወራት ለመስጠት ቃል ገብታለች።




**የአሜሪካ የመከላከያ ሚኒስትርና የዩክሬን ፕሬዚዳንት**

ዩክሬን በምዕራባዊ ሩስያ ከርሰክ ግዛት ድንገተኛ ጥቃት ከፈጸመች በኋላ ወደ ፊት ለመጓዝ ጥረት እያደረገች ሲሆን፤ ሩስያ በበኩሏ በጦርነቱ የዩክሬን ዋነኛ የሎጂስቲክ መተላለፊያ የሆነችውን ፖክሮቭስክ ከተማን መቆጣጠር ላይ ትኩረት አድርጋለች።


# Beeksisa Caal-baasii

Bulchiinsa Magaalaa Shaggar Ku/Ma/La/Xa/La/ Daadhiitti Waajjirri Maallaqaa Aanaa Laga Daadhii Daallee bara baajataa 2017 tiif Kan tajaajilu:

1. Meeshaalee Barreeffamaa
2. Meeshaalee Qulqullinaa
3. Meeshaalee Dhaabbii
4. Meeshaalee elektirooniksii
5. Uffata seeraa Hojjettootaa fi
6. Gommaawwan konkolaataa

Seektaroota Mootummaa Aanicha jalatti argamaniif dorgomsiisee caal-basiidhaan bituu barabaada.

**Ulaagaalee Dorgommichaaf Barbaachisan:-**

1. Heyyamaa Daldalaa haarome kan qabu,
2. Galmaa'aa "VAT" ta'uu isaaf ragaa kan qabu, gibira bara 2016 kan kaffale,
3. Lakkoofsa (TIN) fi tarree dhiyeessitootaa keessa jiraachuu ragaa dhiyeeffachuu Kan danda'u,
4. Dorgomaan kamiyyuu Caal-baasii yoo guutan "VAT" itti ida'uun gatii meeshaalee teechisuu qabu.
5. Dorgomaan kamiyyuu Caal-baasiin erga banamee booda yaada jijjiiruu ykn fooyyesuu fi caal-baasii keessaa of baasuu hin danda'amu.
6. Dorgomaan kamiyyuu kabachisa caalbaasii % 1 Maallaqaan ykn CPO dhan, gatii walii gala tiin herreegee galchuu qaba
7. Caal-baasii burjaajessuu fi dogoggorsuu qaamni yaalii godhe caal-baasii dhaaf gatii qabsiise mootummaaf galii ta'e caal-baasii keessaa haqama. Fuula duras caal-baasii mootummaa irratti akka hin hirmaanne taasifama.
8. Qaamni caal-basii mo'ate xalayaan ykn bilbilaan guyyaa itti himame ykn beeksifame irraa eegalee guyyoota hojii shan keessatti kabachiisa waliigaltee %10 (CPO) dhiyeessuun walii galtee mallatteessuu qabu.
9. Qaamni caalbaasii Mo'ate walii galtee mallateesuuf eeyyamamaa ta'uu yoo baate maallaqni qabsiise mootummaaf galii ta'ee dorgomaa lammaffaaf kennama.
10. Dorgomtooni sanada gatii dorgommii caal-baasii orjinaalaa fi Koppii isaa poostaa adda addaatiin erga saamsanii booda duuba poostaa irratti orjinaalaa fi koppii jechuudhaan erga ibsanii lamaan isaa poostaa tokkoon (mother envelop) fayyadamuun hapheedhaan ykn samiidhaan cuqqaalanii dhiyeessuu qabu,
11. Gatiin kabachiisa caal-baasii qabsiifame qaama mo'atameef battalumatti kan deebi'u yoo ta'u qaamni mo'ate walii galtee mallattessee hanga meesha dhiyeessee xumurutti tura.
12. Dorgomaan kamiyyuu sanadaa haqamaa fi laqamaa kan dhiyeessu yoo ta'e fudhatama hin qabu.
13. Dorgomaan kamiyyuu meeshaa gaafatameen ala yoo dhiyeesse waajjirri kan hin fudhanne ta'uu isaa beekuu qabu.
14. Waajjirichi meeshaalee walii gala bitu keessaa 20% dabaluu ykn hir'isuu ni danda'a.
15. Dorgomtootni kamiyyu sanada caal-baasii qarshii hin deebine 500 (dhibba shan qofa) kaffaluun waajjira Maallaqaa Aanaa Laga Daadhii Daallee kutaa bittaatii bitachuu danda'a.
16. Beeksisni caal-baasii guyyaa beeksisni kun gaazexaa Addis Zaman irratti bahe irraa eegalee guyyoota hojjii 15 kan turu ta'ee gaafa guyyaa 16ffaa sa'aa 8:00 irratti bakka dorgomtootni ykn bakka bu'aan isaanii argamanitti kan banamu ta'a.
17. Waajirichi filannoo fooyya'aa yoo argate caal-baasicha guutummaanis ta'e walakkaadhaan haquu mirga guutuu qaba.

**Odeeffannoo dabalataaf Lakk. Bilbilaa 0920955392 /0910277133**

## Waajjira Maallaqaa Aanaa Laga Daadhii Daallee

# ነፃ ሃሳብ

# ህብራዊነት ዶግማ፤ ህብራዊነት ቀኖና ነው

**ሙሉጌታ ብርሃኑ**

እኛ ማን ነን? ...እኛ ኢትዮጵያውያን ነን! ኢትዮጵያውያን የሆነው ግን "ኢትዮጵያ" ከምትል ሀገር ላይ "...ውያን" የምትል ምዕላድ ስለተቀጠለልን ብቻ ይመስለን ይሆን? አይምሰለን! ምናዊ እንደሆን ብቻ ሳይሆን ማን እንደሆን የሚናገሩ ህልቁ መሳፍርት ቃላት ከስሙ ጋር ተቀጽላ ሆኖው በማይታይ የፊደላት ቅርጽ፣ በውስጠ ታዋቂነት ብቻ የሚነበቡ ማንነቶች አሉ።

ኢትዮጵያዊ ነኝ የሚል ሁሉም እነዚህን በቃላትና በቁጥሮች ብቻ የማይገለጸውን ማንነት ተሸክሟል። የዚህ መሸከሚያ፤ የዚህ ስልቻስ ምን ይሆን ያልን እንደሆን፤ እሱም ለኢትዮጵያና ለኢትዮጵያዊነት ካስማ የሆነው ህብራዊ አንድነታችን ነው። በተናጠል የምንወዳት፣ በተናጠል ቆመን የምንዋጋላት፣ በተናጠል ኖረን በተናጠል የምንታወቅባት፣ በተናጠል ሠርተን በተናጠል የምንበለጽግባት፣ በተናጠል ጠግበን በተናጠል የምንራብባት ኢትዮጵያ የለችም።

የመሰለን ዕለትም ያን ህብራዊ ማንነት አጥተነዋል ማለት ነው። ህብረ ብሔራዊነት ውበት፣ የፍቅር ማሠሪያው አንድነት ነው። ያለ አንድነት የምትሠራ ኢትዮጵያ፣ ያለፍቅር የሚቆም ኢትዮጵያዊነት የለንም። ይህም የኢትዮጵያን መልክ ለያዘ ሁሉ የኢትዮጵያዊነቱ ዶግማና ቀኖና ናቸው። ኢትዮጵያዊ የምንሆነው ኢትዮጵያ ውስጥ ስለተወለድን ብቻ ሳይሆን፤ የኢትዮጵያዊነት ምስጢር ሲገባን ነው። ከሚስጥራቱ አንዱ የሆነውን ህብረ ብሔራዊነትን ከማንነታችን አንገት ላይ እንደ ማህተብ ልናስረው፣ በሄድንበት ሁሉም ከልባችን የማይፋቅ የእምነት ቃል ኪዳናችን አድርገን መታየት ግድ ነው።

**ኢትዮጵያዊ ነኝ የሚል ሁሉም እነዚህን በቃላትና በቁጥሮች ብቻ የማይገለጸውን ማንነት ተሸክሟል። የዚህ መሸከሚያ፤ የዚህ ስልቻስ ምን ይሆን ያልን እንደሆን፤ እሱም ለኢትዮጵያና ለኢትዮጵያዊነት ካስማ የሆነው ህብራዊ አንድነታችን ነው**

ከ2016 መካከል 6 ወጥቶ ሰባት ሊተካ ነው። ይሁንና 2016ዓ.ም ሄዶ 2017ዓ.ም ሊመጣ ነው እንላለን እንጂ ቁጥሩን በተናጠል ለውጠን አንጠራውም። የሚቀየረው 6 በሰባት ብቻ ቢሆንም የአንዱ ለውጥ የሌላውም ለውጥ፣ የአንዱም መነካት የሌላው መነካት መሆኑን በዚህ ስናይ እንዴትስ ኢትዮጵያዊነት ትዝ አይለን...ዛሬ ጳጉሜ አራት ነው። ዛሬ ግን ጳጉሜ 4 ብቻም ሳይሆን ህብራዊ አንድነታችንን ከፍ የምናደርግበት ዕለትም ጭምር ነው።

በህብረ ብሔራዊ አንድነት ተጋንሰን የተወለድን ስለመሆናችን፤ ሁላችንም በሀገር አቀፍ ደረጃ የምናስብበትና የምንተሳሰብበት ነው። ካለፈ የጠለሸ ትዝታ ይልቅ በፍቅር ወደፊት እየፈነጠቅን የነገውን ውጋጋን ሌሊትና የቀኑን ብሩህ ሰማይ የምንመለከትበት ነው። አንድ ሆነን በምንቆምበት ጊዜ የቱ ጋር እንደምንቆምም ጭምር የምናሰላስልበት ነው። ነገር ግን ይኼ የአንድ ቀን ግብራችን አይደለም።

በ365 ቀናት ውስጥ ሁሉ በእያንዳንዱ ደቂቃና ቅጽበት የምንኖረው፣ የሚጠብቀን ሕይወት ነው። የዛሬዋ ጳጉሜም በየትኛውም ዓለም ውስጥ የሌለች ብቸኛው የተፈጥሮ ጸጋችን እና ልዩ የሆንባት ልዩነታችን ናትና እርሷን ለማድመቅ ስንል ልዩ ከሆንባቸው ነገሮች መካከል መርጠን ለልዩ ቀን እንሰጣለን።

እንኳንስ ኢትዮጵያዊው ሰውና ተፈጥሮዋ ራሱ የቆመው በኢትዮጵያዊ ማንነት ነው። ልዩና የዘለዓለም በረከታችን የሆነው ህብረ ብሔራዊ አንድነታችን በተፈጥሮ ውስጥም ትልቁን ሚና ይጫወታል። እኛ ልጆቿ ከዓለም ሕዝቦች ሁሉ ለየት የሚያደርጉን መገለጫዎች እንዳሉን ሁሉ ተፈጥሮዋም ከዓለም ተፈጥሮ ለየት የሚያደርጋቸው ልዩ የጸጋ መገለጫዎች አሏቸው።

ዋናው ኢላማዬ መኖራቸው ላይ ሳይሆን ያላቸው ነገር ከኛ ህብረ ብሔራዊ አንድነት ጋር መሳ ለመሳ የሚሄድ መሆኑ ነው። በኢትዮጵያዊነት ዶግማና ቀኖና ውስጥ ሚስጥራተ ኢትዮጵያዊነትን ጠብቆ የሚኖርን አንድን ግለሰብ፤ ስለኢትዮጵያውያን የሰማ፣ ያነበበ በየትኛውም የዓለም ክፍል ውስጥ ያለ እንዲሁ በደሙ፣ በምግባሩና በግብሩ ለይቶ ያውቀዋል። ቃሉም "ኢትዮጵያዊ መልኩን ነብር ዥንጉርጉርነቱን..." የሚለውስ ለዚሁ አይደል። ልክ እንደዚሁ ሁሉ የሚዳሰሱና የማይዳሰሱትን ጨምሮ ግእዙ ተፈጥሮዋም የኢትዮጵያዊነት መንፈስ የረበባቸውና የራሳቸው ብቻ የሆነ መገለጫዎችን መያዛቸው ነው።

ከዓለም ሁሉ በተለየ መንገድ የ 13 ወር ጸጋ ባለቤት ስንሆን መነሻው ተፈጥሮ መሆኑን መዘንጋት የለብንም። ጠቢባን አባቶቻችን ተጠበው ያገኙት ያንን ኢትዮጵያዊና የኢትዮጵያ ብቻ የሆነውን የተፈጥሮ ቀመር በማስላት ነው። ቀመሩን በአሜሪካን አሊያም በራሺያ ተፈጥሮ ላይ በቀጥታ ብንተገብረው ፈጽሞ ልክ አይመጣም። ምክንያቱም ይህ ቁጥር የተሰጠው ለኢትዮጵያዊው ተፈጥሮ ብቻ ነው። ኢትዮጵያውያን ከተፈጥሮ ጋር ልዩ ስበት የኖረንም በባህሪ ብዙ የሚያመሳስለን ነገር በመኖሩ ነው።

ኢትዮጵያዊነት ከተፈጥሮና ከሰብ ሰብአዊነት ጋር የተዋሃደ መለኮታዊ ቀመር ያለው መሆኑንም ማወቅ ያሻል። ቀናት፣ ወራትና ዓመታት በተፈጥሮ ምህዋር ስር የሚኖሩ ናቸው። እያንዳንዳቸውን በህብር በማስተሳሰር ተፈጥሮ ይዘውራቸዋል። በዚህ ውስጥ ይመሻል፣ ይነጋል፣ ይጨልምና ደግሞ ብርሃን ይሆናል። ደመናማ የጭጋግ ቀን ጸሐያማ ብሩህ ቀን፣ የጽልመት ምሽት፣ ደግሞ የጨረቃ ምሽት ይታያል።

ክረምት፣ በጋና በልግ እንዲሁም ጸደይ በአንዲት ዓመት ውስጥ የሚኖሩ፣ በዘመናት መካከል ያልተቀየሩና የማይቀየሩ የተፈጥሮ ማንነቶች ናቸው። ክረምት ዝናባማ፣ በጋማ ብራ...ይህ ማንነታቸው ነው። ያለክረምት በጋ፣ ያለበጋ ክረምት አይኖርም። ማንም ማንንም አይመስልም ነገር ግን፤ በልዩነት ውስጥ አንድነት አላቸው። ስለዚህ የህብረ ብሔራዊ አንድነትን መገለጫ ይዘዋልና አመክንዮው ልክ ይሆናል። ኢትዮጵያዊ በደም ተፈጥሮዋም በመልክ ተሳስረዋል።

አያድርገውና ለአብነት በጋ አሊያም ክረምት ከሁለት አንዱ 365ቱም ቀናት ይገባኛልና አሻፈረኝ ቢሉ ምን ሊፈጠር እንደሚችል እስኪ ለአፍታ አስቡት... በቀን መውጣት ያለባት ጸሐይ በማታ ካልወጣሁ ብትልስ? ጉዳዩ የብርሃንና የጨለማ ብቻ መስሎ ከታየን በእርግጥም ህብረ ብሔራዊነት አልገባንም። የአንዲት ክረምት ማፈንገጥ ከሰው ልጆች ጀምሮ መላውን ተፈጥሮ ያቃውሳል። የማያባራ እልቂት ተከፍቶ መቋጫው ይጠፋል። ጸሐይም ከጨረቃ ጋር ተነካክታ ብቻ አታቆምም። ጦሱ በምድር ላይ ላለ ሰውና ተፈጥሮ ነው። ይህ ከገባን ህብረ ብሔራዊ አንድነት ማለት ለሀገራችን ምን ማለት እንደሆን እንረዳለን።

ህብረ ብሔራዊነት ለኢትዮጵያ የምርጫ አሊያም የውዴታ ጉዳይ ብቻ አይደለም። ህብረ ብሔራዊነት የመኖርና ያለመኖር፣ በህልውና የመቀጠልና ያለመቀጠል ነው። ህብረ ብሔራዊነት የሚለው ቃል ብዝሃነትን የሚገልጽ ስለሆነ ብቻ አንድነታችንን ለመጠበቅ የግድ በብሔር፣ ቋንቋና ጎሳ ደረጃ መድረስ አይጠበቅብንም። ጎሳንም ሆነ ብሔርን ቀጥሎም ሀገርን የሠራው እያንዳንዱ ግለሰብ ነውና የህብረ ብሔራዊ አንድነታችን መሠረቱ ያለው በግለሰቦች ላይ ነው።

እያንዳንዱ ግለሰብ እላይ በሀገር ደረጃ ከማሰቡ በፊት ከራሱ መጀመር ይኖርበታል። እኛ ማን ነን? ለሚለው ምላሽ ከመፈለጉ በፊት እኔ ማን ነኝ ይቀድማል። እኛነት ደረጃ ላይ ከደረስን በኋላ ወደኋላ ተመልሰን እኔነት የሚያጠቃን አስቀድመን ይህን ባለመከተላችን ነው። አጠገባችን ያለን አንድ የሌላ ብሔር ግለሰብ፤ ነገረ ሥራው ሁሉ የሚያስጠላንና የማይመቸን እንደሆን ከብሔሩ ማንነት ጋር ወስደን የምንለጥፍበት አጋጣሚ ቀላል አይደለም። "እነርሱ እኮ እንዲህ ናቸው...አመላቸው ይኼው ነው...ከራሳቸው ዘር በስተቀር የማያስጠጉ..." ወዘተ ወዘተ...ዐረፍተ ነገሮችን ያላሰማን ወይም ያልሰማን የለንም። ዛሬ ለዚህ ያበቃን አንድም ይኼው የጅምላ ፍረጃችን ነው።

ትልቁ ችግራችን እኛ ውስጥ ያሉትን እነርሱን እንጂ፤ እነርሱ ውስጥ ሆነን ራሳችንን አንመለከትም። ብዙዎችን ይህን ፍርድ የሚፈርዱት ወደዚያ ማኅበረሰብ ሄደው ከማኅበረሰቡ ጋር ኖረው ሳይሆን፤ ከዚያ ማኅበረሰብ ወጥተው በእነርሱ ውስጥ የኖሩትን በጣት የሚቆጠሩትን ዋቢ በማድረግ ነው። እንዲህ ዓይነቱን ጅምላ ፈጅ ንግግር ሲያደርጉ በግሌ ብዙዎችን ሰምቻለሁ።

ነገር ግን፤ በዚያ ከእነርሱ ጋር ኖረው ስለኖሩበት ማኅበረሰብ በክፋት ሲያነሱ የሰማኋቸው እንዳሉ ትዝ አይለኝም። ይህ ማለት በነፈሰብን ንፋስ ሁሉ እንደ ፔንዱለም ዥዋዥዌ የምንጫወት መሆናችንን ያሳያል። እንዲህ ዓይነቱን የጅምላ አመክንዮ የምንከተል ከሆነ በግለሰብ ደረጃ ህብረ ብሔራዊ አንድነታችንን ለመጠበቅ ይከብደናል። ለሞት የመርዝ ጠብታም በቂ ነውና... እያለ ሄዶ የግለሰቦች መመረዝ ሀገርን ያጠፋል። ስለዚህ ህብረ ብሔራዊነት ከአንድ ግለሰብ ዛሬ፣ አሁን ይጀምራል።

ህብረ ብሔራዊነት ዶግማ፣ ህብረ ብሔራዊነት ቀኖና ነው። ያለ ኢትዮጵያ ኢትዮጵያዊነት፣ ያለ ኢትዮጵያዊነት ኢትዮጵያ አይኖሩም። በኢትዮጵያዊነት ውስጥ የምናደርጋቸው የምናገኛቸው ነገሮች ኢትዮጵያን ይሠሯታል። ኢትዮጵያዊነት አንድም በተግባር ሥርዓት ይገለጣል። ሁለትም በልባዊ እምነት እያጸኑ በስጋና በደም ከማይታይ መንፈስ ጋር ይረብባል።

ፍቅር፣ አንድነት፣ መተሳሰብ፣ መደጋገፍ፣ መከባበር... የሚሉ ነገሮች ሁሉ ሚስጥራተ ኢትዮጵያዊነት ናቸው። እኔ ኢትዮጵያውያን ነኝ! ስንልም ከዶግማና ቆኖናው መካከል የሆነውን ህብረ ብሔራዊ አንድነትን እየጠራን ነውና አሳ ያለውሃ ለመኖር በማይቻለው መጠን ኢትዮጵያና ኢትዮጵያዊም ከዚህ ዶግማ፣ ከዚህ ቀኖና በላይም በታችም ሆነው መኖር እንደማይችሉ ማወቅ ሀገር አድን ዕውቀት ነው።

ዶግማውን ያላወቀ ዜጋ፣ ቀኖናውን ያላጤነ ትውልድ ከወንዝ ውስጥ እንደጣሉት መርፌ ማለት ነው። መቼ እንደሚወጋ፣ መቼ የት እንደሚገኝ አይታወቅም። ኢትዮጵያዊነት በደም ብቻ የሚገኝ አይደለም። ኢትዮጵያዊነት በልብና በሥራ የሚገለጽ የተፈጥሮና የሠብዓዊነት ድምር ውጤት ነው። ሀገራችን በብዙ ልዩነቶች መካከል አንዲት ህብር አጽንታ ዛሬም ድረስ ለመኖሯ ምክንያት፤ በየዘመናቱ የነበሩ ሁሉ ለዚህ ዶግማና ቆኖና ተገዝተውና አክብረው በመኖራቸው ነው። ኢትዮጵያ በህብራዊ አንድነት ተጽና የተወለደች፣ በአንድነት ቢከፋትም ቢደላትም በአንድነት ኖራ በአንድነት አደባባይ ቆማ የታየች ሀገር ናትና ከዚህ ወዲያም ያለዚህ ህላዊ እስትንፋስ አይኖራትም።

እኛ በጥቁር ሕዝቦች ግንባር የታተመን አርማ ነን። እኛ የነጻነት አውድማ፣ የፍቅር ሐይቅ ጀልባ፣ የሰላም ውቅያኖስ መርከቦች ነን። ያለምንም የቀለም ጠብታ የጥበብን ካስማ አቁመን ዓለምን ሁሉ ያስከተልን፣ ያለምንም ቀለም ሠብዓዊነትን ከተፈጥሮ የተቸርን፣ ብዙ ሆነን እንደ አንድ የተፋቀርን፣ አንድ ሆነን እንደ ብዙ የተፋጀን፣ ለወደደን ልባችንን ለጠላን ክንዳችን ስንሰጥ ሁሉ የዚህ ምስጢራዊ ሃይል፤ ህብረ ብሔራዊ አንድነታችን ነበር። ዓድዋ ላይ እንኳን ታንክ ነበራቸው እንጂ አነበረንም። መድፍ ነበራቸው እንጂ እኛ አልነበረንም።

እኛ የነበረን እነርሱ ያልነበራቸው ነገር ቢኖር ያ ብሔራዊ አንድነታችን ነው። ሰሜን ከደቡብ፣ ምሥራቅ ከምዕራብ የቆመው ለአንዲት እናት ሀገሩ፣ አንድ ሆኖ ብቻ ነበር። "አንድነት ሃይል ነው!" ያለው ለምን ይመስልሃል? ምላሹ ለቀባሪ መርዶ እንደማርዳት ነው።

ታዲያ ዛሬስ እንዴት ነን? በ2016 የዳኝነት ሸንጎ ቆመን፣ በ2017 የታዛቢነት ሠገነት ላይ አሻቅበን እየተመለከትን እስቲ ራሳችንን እንጠይቀው። እስቲ ጥቂት እናስብ። እስቲ ጥቂት እናሰላስል። አንድ ሆነን አንድ ምድራዊ ባቢሎን የገነባን ሕዝቦች ነበርን። አብረን ተነስተን አብረን ስንሠራ ምን ያህል ብርቱና ጠቢባን እንደነበርን የዓለም ሕዝብ ሁሉ ምስክር ነው። ግን መቼ? እንዴትና የቱ ጋር ነው ያ ባቢሎናችን የፍርስራሽ ክምር የሆነው? እኛው የሠራነውን የአንድነት ባቢሎን እኛው እያፈረስነው መሆኑ እርግጥ ነው።

ፍቅርና ነገር በዓይን እርግብግቢት የሚገባን ሰዎች ቋንቋችን ተደበላልቆ፤ ከመግባባትም መስማማት የጠፋን እንዴት ይሆን? አዎን...ይህ ሁሉ የሚከተለው ህብረ ብሔራዊነት የራቀ ዕለት ነው። አዎን...ይህን የምናመጣው ለአንዲት ሀገር አንድ ሆኖ በአንድነት መታየት ባስጠላን ቅጽበት ነው። በዚያን ማግስት የአሞራ የኑስ ዝናብ ይዘንባል። ከምድር በላይ አውሎንፋስ፣ ከምድር ላይ ሱናሚ ይነሳል። የውቅያኖሱ ማዕበል እየተቀሰቀሰ የባህሩ ሞገድ በወጀብ ያናውጣል።

ማንም በውሃው ላይ ሃይል አይኖረውምና ብቻውን ዋኝቶ ለማምለጥ አይቻለውም። ከመርከቦች ቀድመው ጀልባዎች ይሰምጣሉ። ከትናንሾች ይልቅ ትላልቆች ሃይል አላቸው። ሞገዱም ሆነ አውሎንፋሱ አስቀድመው በቀላሉ ሊያጠፉት የሚችሉት ትንሽ ሆኖ ለብቻው ያገኙትን ነው። በታሪክ ብቻውን ቆሞ ብቻውን የጀገነ፣ አንድነትን ገፍቶ አንድ ለራሱ የነገሠባት ማንም የለም። አንዱ ወጀብ፣ አንዱ ሱናሚ የተነሳ ዕለት ነጥሎ የሚመታው ማንም የለምና አንዱ ዳፋው ለሁሉም ነው። ህብረ ብሔራዊነታችን ለማንም ብለን ሳይሆን ራሳችንን ለማዳን የምንሠራት የኖህ መርከብ ናት።

አሁን ዛሬ እየሄደ፣ ነገ እየመጣ ነው። ከታዘብናቸው ጋር በሃሳብ ወርደን በላ! ልበልሃ! ከምንባባል፤ ህብር ባፈካ የፍቅር ቅላጼ ልባቸውን እናቅልጠው። የቀለጠን ነገር ማቃናት እዳው ገብስ ነውና። ሁሌም ካለፈው ለሚመጣው መማርን እንልመድ። ሕይወት ደግሞ ሁሌም የትምህርት ናትና። 2016ዓ.ም የሚል አንድ ደብተር ጽፈንና ሞልተን ልናልፍ ነው። የምናልፈው በፈተና ቢሆን ኖሮ ስንቶቻችን እንደምናልፈው ግን እንጃ...ይሁንና 2017 ዓ.ም የሚል ቀጣዩ አዲስ ደብተር ቀርቧል።

የአዲሱ ሕይወት ትምህርት ቤት ሊከፈት ተቃርቧል። እና ገና በመጀመሪያው የመስከረም 1 ቀን 2017 ዓ.ም፣ በመጀመሪያው ገጽ ላይ የምንጽፈው ነገር ምን ይሆን? መቼም ታጥቦ ጭቃ መስለን ከአምናው ደብተር ላይ መገልበጥ ከጀመርን ወደኋላ ፊደል መቁጠር ሊያስፈልገን ነው። የምንሰርዘው አሊያም የምንደልዘው ታሪክ ባይኖርም የምንደግመው መጥፎ ታሪክ ግን አይኑረን። መድገም የሰነፎችና የወደቁት ነው። ሀገር ወዳድ ኢትዮጵያዊ፣ ጎበዝ የሕይወት ተማሪ ሁሌም ዶግማና ቀኖናውን አይረሳምና አይወድቅም። ሁሌም እያስታወስን ህብረ ብሔራዊ አንድነታችንን በእምነት፣ በተስፋ፣ በፍቅርና በቅንነት አጽንተን እንኑር!!

# ስፖርት



# የፓሪስ ፓራሊምፒክ ዛሬ ይጠናቀቃል

**ብርሃን ፈይሳ**

አካል ጉዳተኛ ስፖርተኞችን ባለፉት ቀናት ሲያወዳድር የቆየው የፓሪስ 2024 ፓራሊምፒክ ዛሬ ማጠቃለያውን የሚያገኝ ይሆናል። ከመላው ዓለም በተፈጥሮም ሆነ ሰው ሰራሽ አደጋ አካላቸው ላይ ጉዳት የደረሰባቸው ስፖርተኞች ተወጣጥተው እርስ በእርስ የአሸናፊነት ፉክክር የሚያደርጉበት ይህ መድረክ ከኦሊምፒክ መካሄድ በኋላ የሚጀመር ነው። ዛሬ በሚጠናቀቀው 17ኛው የፓራሊምፒክ ውድድር ላይም ከ170 ሀገራት የተወጣጡ 4ሺ400 የሚሆኑ ስፖርተኞች በ22 የስፖርት ዓይነቶች የሀገራቸውን ሰንደቅ በማውለብለብ የታላቁን መድረክ ሜዳሊያ ለማጥለቅ ሲፋለሙ ቆይተዋል።

በሁለተኛው የዓለም ጦርነት ተሳትፈው አካላዊ ጉዳት በገጠማቸው ጥቂት የቀድሞ ወታደሮች እአአ በ1948 የተጀመረው ይህ ስፖርት ዓይነት እንደጊዜው እያደገና እየተጠናከረ በመሄድ በሮም አዘጋጅነት የተካሄደውን የ1960 ኦሊምፒክ ተከትሎ የፓራሊምፒክ ውድድር ለመጀመሪያ ጊዜ መደረጉን ታሪክ ያወሳል። በወቅቱ ውድድሩ ላይ የተካፈሉት አትሌቶች 400 ብቻ ሲሆኑ ከ64 ዓመታት በኋላ ቁጥሩ በከፍተኛ መጠን ማሻቀቡን ለመረዳት ይቻላል። ፈረንሳይ በታሪኳ ኦሊምፒክን ዘንድሮ ለሶስተኛ ጊዜ ያሰናዳች ቢሆንም የፓራሊምፒክ ውድድርን በሀገሯ ስታካሂድ ግን ይህ ለመጀመሪያ ጊዜ ነው።

ዛሬ 12ኛ ቀኑን ያስቆጠረው ፓራሊምፒክ የመክፈቻ መርሀ ግብሩን በደማቋ የፓሪስ ከተማ ትልቁ አደባባይ የተከናወነ ሲሆን፤ በኦሊምፒኩ ላይ ከታየውና በብዙዎች ከተተቸው በተለየ ደማቅ ሊባል የሚችል ነበር። 500 የሚሆኑ ዳንሰኞችን ጨምሮ በርካታ የጥበብ ሰዎች ስራዎቻቸውን ባሳዩበት መድረክ የሆንግ ኮንግ ተወላጅና በፊልም ዓለም እጅግ ተወዳጅ የሆነው አክተር ጃኪ ቻን የፓራሊምፒክ ችቦውን ለኩሷል። የዛሬው የመዝጊያ መርሀ ግብርም ከ77ሺ ሰው በላይ የመያዝ አቅም ባለውና የፓራሊምፒክ የመምና ሜዳ ተግባራት ውድድሮች ሲደረጉ በቆዩበት ግዙፉ የፈረንሳይ ስታዲየም ውስጥ የሚከናወን ይሆናል።

አሜሪካ፣ ቻይና እና ጃፓን የሜዳሊያ ሰንጠረዡን እየመሩ ያሉበት የዘንድሮው ፓራሊምፒክ፤ ኢትዮጵያን ጨምሮ 91 ሀገራት የሜዳሊያ ሽሚያውን ተቀላቅለዋል። 64 ሜዳሊያዎችን መሰብሰብ የቻለችው አዘጋጇ ሀገር ፈረንሳይ 5ኛ ደረጃ ላይ መቀመጥ ችላለች። እጅግ ጠንካራ ፉክክር የታየበት ውድድሩ 20 በሚጠጉ ውድድሮች የዓለም ክብረወሰን የተሰበረበት ሊሆን ችሏል። በመድረኩ ከተሻሻሉ ክብረወሰኖች መካከል አንዱ በሴቶች 1ሺ500 ሜትር ርቀት (T11) የተወዳደረችው ኢትዮጵያዊቷ ያየሽ ጌቴ አንዷ ናት። አትሌቷ በራሷ ሀገሯን በድል ባስጠራችበት ውድድር ያስመዘገበችው ክብረወሰን በራሷ ተይዞ የቆየውን ሰዓት ከ4 ሰከንድ በላይ በማሻሻልም ነው።

በርካታ አስገራሚና አስደናቂ ክስተቶች በታዩበት በዚህ ውድድር የስደተኞች ቡድንም ለመጀመሪያ ጊዜ በመድረኩ ሜዳሊያ ሊያስመዘግብ ችሏል። በተለያዩ ተፈጥሯዊና ሰው ሰራሽ ችግሮች ሳቢያ የትውልድ ሀገራቸውን ጥለው ለስደት የተዳረጉ ስፖርተኞች በዓለም አቀፉ የኦሊምፒክ ኮሚቴ ባንዲራ ተወክለው በታላቁ የስፖርት ውድድር እንዲሳተፉ እንደሚደረግ ይታወቃል። በፓራሊምፒክ ውድድርም በተመሳሳይ የአካል ጉዳት ያለባቸው ስደተኞች የሚካፈሉ ሲሆን፤




በታሪክ የመጀመሪያው ሜዳሊያ ፓሪስ ላይ ተገኝቷል። ይኸውም በዛኪያ ኩዳዳዲ የሴቶች 47 ኪሎ ግራም የቴኳንዶ ውድድር የተገኘ የነሀስ ሜዳሊያ ነው። በሴቶች የባድሜንተን ውድድር ደግሞ የ7 ወር ነፍሰጡር የሆነችው ተወዳዳሪ የወርቅ ሜዳሊያ በማግኘት አነጋጋሪ ልትሆን ችላለች። እንግሊዛዊቷ የቀስት ተወዳዳሪ ጆዲ ግሪንሃም በግሏ የነሀስ ሜዳሊያ ስታገኝ፤ በቡድን ደግሞ የወርቅ ሜዳሊያ በማጥለቅ በፓራሊምፒክ ውድድር የመጀመሪያ ሴት አትሌት ልትሰኝ ችላለች።

ሌላኛው አሜሪካዊ ሮድሪክ ታውንሴንድ ደግሞ በከፍታ ዝላይ በተከታታይ ሶስት የፓራሊምፒክ መድረኮች ላይ በማሸነፍ አድናቆትን ሊያተርፍ ችሏል። ይህ አትሌት የአካል ጉዳት ካላገደው ብቃቱ ባለፈ በተለያዩ ቀለማት ባደመቀው ጸጉሩ እንዲሁም በራፕ የሙዚቃ ስልት በሚያደርገው እንቅስቃሴ የውድድሩ ድምቀት ለመሆንም ችሏል። የፍቅር ከተማ የምትሰኘው ፓሪስ ላለፉት ሳምንታት ስፖርታዊ ውድድር ላይ ብትሆንም ታዋቂው የኤፍል ማማ እና ውብ ጎዳናዎቿ ግን በርካታ የፓራሊምፒክ ተወዳዳሪ ጥንዶች ወደ ትዳር ለመሸጋገር የ‹‹እንጋባ›› ጥያቄዎችን ሲያስተናግዱም ነበር።

## አማራ ክልል

1ኛ ለአቶ ጥበቡ በላይ 2ኛ አቶ የሻምበል በቀለ ባሉበት በከሳሽ የጃቢጠህናን ወረዳ ፍ/ቤት እና በተከሳሽ እርስዎ መካከል ባለው የኦዲት ጉድለት ገንዘብ ክስ ጉዳይ መከሰስዎን አውቀው ለጥቅምት 04 ቀን 2017 ዓ.ም በ4፡00 ሰዓት የምዕ/ጎጃም ከፍተኛ ፍ/ቤት ፍ/ሰላም እንዲቀርቡ ባይቀርቡ ግን ጉዳዩ በሌሉበት የሚታይ መሆኑን ፍ/ቤቱ አዟል፡፡

**በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ጠ/ፍ/ቤት የምዕ/ጎጃም ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ፍ/ሔር**

## አዲስ አበባ አስተዳደር

በከሳሽ፡- ወ/ሮ ነፃነት በድቀ እና በተከሳሽ፡- አቶ አወሉ አብሽሩ መካከል ስላለው የፍ/ብሔር ክርክር ጉዳይ ፍ/ቤቱ በሰጠው ትዕዛዝ ተከሳሽ በአዲስ አበባ ከተማ የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ጉለሌ ምድብ 3ኛ የፍ/ብሔር ችሎት እየታየ መሆኑን አውቀው መልስዎን በፅሑፍ ለ08/01/2017ዓ.ም በ4፡00 ሰዓት እንዲያቀርቡ ካልቀረቡ ጉዳዩ በሌሉበት ታይቶ የሚወሰን መሆኑን አውቀው እንዲያቀርብ ታዟል፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድደ ቤት የጉለሌ ምድብ ችሎት**

በከሳሽ አዋሽ ኢንሹራንስ አ/ማ እና በተከሳሽ አቶ ዮሐንስ ታደሰ መካከል ስላለው የፍትሐብሔር ክርክር ጉዳይ ከሳሽ ፍ/ቤቱ በሰጠው ትዕዛዝ ተከሳሽ በፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት ንግድና ኢንቨስትመንት ምድብ 2ኛ ባ/ኢንሹራንስ ችሎት እየታየ መሆኑን በዚህ ጋዜጣ ማስታወቂያ ጥሪ አውቀው መልሱን በፅሁፍ በ22/02/2017 ዓ.ም በ3፡50 ሰዓት በሬጅስትራር በኩል እንዲያቀርቡ እና ክስ ለመስማት በ25/02/2017 ዓ.ም በ4፡30 ሰዓት ይዘው እንዲቀርቡ ፍ/ቤቱ አዟል፡፡

**የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ንግድና ኢንቨስትመንት ምድብ ችሎት**

ይግባኝ ባይ አዋሽ ኢንሹራንስ እና መ/ሰጪ እነ ካሳና ልጆቹ ኮንስትራክሽን መካከል ስላለው የፍትሐብሔር ክርክር ጉዳይ 1ኛ መልስ ሰጪ ይግባኝ መጠየቁን አውቀው ለ12/02/2017 ዓ.ም 4፡00 ሰዓት የተቀጠረ መሆኑን አውቀው በፌ/ከ/ፍ/ቤት ልደታ ምድብ ተስፋኮከብ ት/ቤት አካባቢ 6ኛ ይግባኝ ፍትሐብሔር ችሎት እንዲቀርቡ ፍ/ቤቱ አዟል፡፡ የማይቀርቡ ቢሆን ጉዳዩ በሌሉበት ታይቶ የሚወሰን መሆኑን እንገልፃለን፡፡

**የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት**

በከሳሽ አራሚስ የጨው እና የጨው ኬሚካል ኢንዱስትሪ ሀ/የተ/የግ/ማ
በተከሳሾች እነ ኖሻድ አሊ

1. አቶ ቴዎድሮስ ሀ/ስላሴ
2. አቶ አብደላ አብዱሰላም
3. አቶ አሊ አሚን
4. ወ/ሮ ዘሀራ መሀመድ

መካከል ስላለው የፍ/ብሄር ክርክር ጉዳይ ተከሳሾች መከሰሳቸውን አውቀው ለ07/01/2017 ዓ.ም በ4፡00 ሰዓት የተቀጠረ መሆኑን አውቃችሁ በፌ/ከ/ፍ/ቤት ልደታ ምድብ 1ኛ ንግድ ፍ/ብሔር ቀጥታ ክስ ችሎት እንዲቀርቡ ፍ/ቤቱ አዟል፡፡ የማይቀርቡ ከሆነ ጉዳዩ በሌሉበት ታይቶ የሚወሰን መሆኑን እንገልፃለን፡፡

**የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት**

በይግባኝ ባይ ወ/ሪት ፌቨን ፍትዊ እና መልስ ሰጭ ወ/ሮ እቴነሽ አበበ መካከል ባለው የፍ/ብሔር ይግባኝ ክርክር ጉዳይ መልስ ሰጭ በጋዜጣ እንዲጠሩ ፍ/ቤቱ በ24/12/2016ዓ.ም በዋለው ችሎት ትእዛዝ የሰጠበት በመሆኑ መልስ ሰጭ ወ/ሮ እቴነሽ አበበ ለ13/01/2017ዓ.ም በ4፡00 ሰዓት ለሆነው ቀጠሮ በፌ/ከ/ፍ/ቤት ቃሊቲ ምድብ 1ኛ ፍ/ብሔር ችሎት ድረስ ምላሻቸውን ይዘው እንዲቀርቡ አዟል፡፡ካልቀረቡ ጉዳያቸው በሌሉበት የሚታይ ይሆናል፡፡

**የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የቃሊቲ ምድብ ችሎት**

አመልካች አቶ ተሾመ ዉዱ እና 1ኛ ወ/ሪት በላይነሽ ዉዱ መለሰ 2ኛ. ወ/ሪት ሻሺቱ ዉዱ መለሰ 3ኛ ወ/ሪት ወርቅነሽ ዉዱ መለሰ 4ኛ አቶ ግርማ ዉዱ መለሰ የመጥፋት ውሳኔ ይሰጥልኝ ሲሉ አመልክተዋል፡፡ ስለሆነም ያሉበትን የሚያውቅ ወይም ራሳቸው ካሉ መስከረም 10/2017 ዓ.ም በ4፡00 ሰዓት ለሆነው ቀጠሮ አዲስ አበባ ከተማ የመ/ደ/ፍ/ቤት የካ ምድብ ችሎት እንዲቀርቡ ፍ/ቤቱ አዟል፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የየካ ምድብ ችሎት**

አመልካች ሲስተር እልባት ለገሰ ተጠሪ አቶ ጌታቸው ጩማሩ ተጠሪ ከ2014 ዓ.ም ጀምሮ የጠፉ ስለሆነ የመጥፋት ውሳኔ ይሰጥልኝ ሲሉ አመልክተዋል፡፡ ስለሆነም አቶ ጌታቸው ጩማሩ ያሉበትን የሚያውቅ ወይም ራሳቸው ካሉ ለ08/01/2017 ዓ.ም በ3፡30 ሰዓት ለሆነው ቀጠሮ አ/አ/ከ የመ/ደ/ፍ/ቤት ቂርቆስ ምድብ ችሎት እንዲቀርቡ ፍ/ቤቱ አዟል፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የቂርቆስ ምድብ ችሎት**

በአመልካች ወ/ሮ አለምፀሀይ ትኩ እና በተከሳሽ ወ/ሮ ሲኞራ ሳቢና ሴልቪስትሪ ሳቢና መካከል ስላለው ክስ ተጠሪ ክስ የቀረበባቸው መሆኑን አውቀው ለ06/01/2017 ዓ.ም በ4፡00 ሰዓት አ/አ/ከ የመ/ደ/ፍቤት ቦሌ ምድብ 2ኛ ፍ/ብሄር ችሎት እንዲቀርቡ ፍ/ቤቱ አዟል፡፡ ተጠሪ ባይቀርቡ መልስ በጽሁፍ የማቅረብ መብታቸው እንደሚታለፍ ፍ/ቤቱ አዟል፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ቦሌ ምድብ ችሎት**

አመልካች እነ ንጋቱ አማረ ተጠሪ አቶ አማረ ሰይፉ ከሐምሌ 7/2014 ዓ.ም ጀምሮ የጠፉ ስለሆነ የመጥፋት ውሳኔ ይሰጥልኝ ሲሉ አመልክተዋል፡፡ ስለሆነም አቶ አማረ ሰይፉ ያሉበትን የሚያውቅ ወይም ራሳቸው ካሉ ለ06/01/2017 ዓ.ም በ4፡00 ሰዓት ለሆነው ቀጠሮ አ/አ/ከ የመ/ደ/ፍ/ቤት አዲስ ከተማ ምድብ ችሎት እንዲቀርቡ ፍ/ቤቱ አዟል፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የአዲስ ከተማ ምድብ ችሎት**

የባለንብረት ስም ራሄል በለጠ ገብሬ የሠሌዳ ቁጥር አአ 02-01-A02914 የተሽከርካሪው ዓይነት አውቶሞቢል የሻንሲ ቁጥር JT1EOEE8000068064 ሞዴል EE80L EEkDSW የሞተር ቁጥር 2E-0222887 የሊብሬ ቁጥር 169198 ከላይ የተጠቀሰው የተሽከርካሪ ባለንብረት የባለቤትነት ማረጋገጫ ደብተር/ሊብሬ ጠፋብኝ ብለው በ28/12/2016 ዓ.ም አመልክተዋል፡፡ የባለቤትነት መታወቂያ ደብተሩን ወድቆ ያገኘ ወይንም በሌላ ምክንያት ይዤዋለሁ የሚል ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ በ15 ቀን ውስጥ የፍ/ቤት ማሳገጃ ትዕዛዝ እንዲያቀርቡ እያስታወቅን ፣ በተባለው ጊዜ ገደብ ውስጥ ካልቀረቡ ለአመልካች ተለዋጭ ሊብሬ ወይንም መታወቂያ ደብተር የምንሰጥ መሆኑን እንገልጻለን፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የአሽከርካሪና ተሽከርካሪ ፈቃድና ቁጥጥር ባለሥልጣን የአቃቂ ቃሊቲ ቅ/ጽ/ቤት**

የባለንብረት ስም ነፃነት ደምሴ አሞኘ የሠሌዳ ቁጥር አአ 02-01-B05224 የተሽከርካሪው ዓይነት አውቶሞቢል የሻንሲ ቁጥር SCP11-0029505 ሞዴል TA-SCP11-BEPNK-L የሞተር ቁጥር 1SZ-0535922 የሊብሬ ቁጥር 032743 ከላይ የተጠቀሰው የተሽከርካሪ ባለንብረት የባለቤትነት ማረጋገጫ ደብተር/ሊብሬ ጠፋብኝ ብለው በ28/12/2016 ዓ.ም አመልክተዋል፡፡ የባለቤትነት መታወቂያ ደብተሩን ወድቆ ያገኘ ወይንም በሌላ ምክንያት ይዤዋለሁ የሚል ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ በ15 ቀን ውስጥ የፍ/ቤት ማሳገጃ ትዕዛዝ እንዲያቀርቡ እያስታወቅን ፣ በተባለው ጊዜ ገደብ ውስጥ ካልቀረቡ ለአመልካች ተለዋጭ ሊብሬ ወይንም መታወቂያ ደብተር የምንሰጥ መሆኑን እንገልጻለን፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የአሽከርካሪና ተሽከርካሪ ፈቃድና ቁጥጥር ባለሥልጣን ጉለሌ ቅ/ጽ/ቤት**